አዛውንቷ
ሎተሪ አዟሪ



ገጽ 16

ዜጎች የሙያ ባለቤት
እንዲሆኑ መደላድል
የፈጠሩ ትላልቅ
ፕሮጀክቶች



ገጽ 14




አዲስ ዘመን
ኢፕድ
82ኛ ዓመት ቁጥር 217 ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር እና የሶማሊያ

## ፕሬዚዳንት ለይፋዊ የስራ ጉብኝት አዲስ አበባ ገቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ እና የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀሙድ በኢትዮጵያ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ ትናንት አዲስ አበባ ገብተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አቀባበል አድርገውላቸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ፥ “የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ ለሁለት ቀን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ እንኳን ደኅና መጡ” ሲሉ ገልጸዋል።

ጉብኝቱ የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር አጋዥ መሆኑንም ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያመለከቱት።

ጆርጂያ ሜሎኒ በኢትዮጵያ በሚኖራቸው የሁለት ቀናት ቆይታ ከመንግስትና ከአፍሪካ ሕብረት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ይወያያሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የጠቅላይ ሚኒስትሯ ጉብኝት ጣሊያን ለኢትዮጵያ የምታደርገውን ሰብዓዊና የልማት ድጋፍ ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመምከር እንደሚሆንም ተጠቁሟል። ጉብኝቱ የኢትዮጵያ እና የጣሊያንን አጋርነት ለማጠናከር ያለመ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ ኢትዮጵያና ጣሊያን በሚጋሯቸው ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት እንደሚያደርጉም ተጠቅሷል።

በተመሳሳይም የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀሙድ ለይፋዊ የስራ ጉብኝት ትናንት ከሰዓት በኋላ አዲስ አበባ ገብተዋል።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሀሙድ አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱም የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ፕሬዚዳንቱ በኢትዮጵያ የሁለት ቀናት ቆይታ እንደሚኖረውም ተጠቅሷል።



# የኦሮሚያ ልዩ ኃይልን

## መልሶ የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የክልሉ አስተዳደርና ጸጥታ ቢሮ ገለጸ

### - አባላቱ ወደ ካምፕ እየገቡ መሆኑንም አስታውቋል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል እንደ ሌሎች ክልሎች ሁሉ የልዩ ኃይሉን መልሶ የማደራጀት ሥራ እየተሰራ መሆኑን የክልሉ አስተዳደርና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ኮሚሽነር ጀነራል አራርሳ መርዳሳ አስታወቁ፡፡ የልዩ ኃይል አባላቱ ወደካምፕ እየገቡ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ኮሚሽነር ጀነራል አራርሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

የኦሮሚያ ልዩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “የቀደሙትን የመከባበርና የመቻቻል እሴቶች በማስቀጠል የሀገራችንን የግዛትና ህዝባዊ አንድነት ልናስቀጥል ይገባል”

- መልአከ ምህረት አማረ አበበ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- እንደሃገር የቀደሙትን የመከባበርና የመቻቻል እሴቶች በማስቀጠል ልዩነቶችን መፍታትና የግዛትና ህዝባዊ አንድነታችንን ልናስቀጥል እንደሚገባ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በየረር በር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ መልአከ ምህረት አማረ አበበ አስታወቁ፡፡

የቀደሙትን የመከባበርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ግዛቸው ሙሉነህ

# በአማራ ክልል የፀጥታ ችግሮች የነበሩባቸው አካባቢዎች ወደ ቀደመው መረጋጋት ተመልሰዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከልዩ ኃይል መልሶ ማደራጀት ጋር በተያያዘ በአማራ ክልል የፀጥታ ችግሮች የነበሩባቸው አካባቢዎች ወደ ቀደመው መረጋጋት መመለሳቸውን የአማራ ክልል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ገለጹ።

የቢሮ ኃላፊው ወቅታዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ የክልል ልዩ ኃይል መልሶ ማደራጀትን በተመለከተ የመረጃ ክፍተት

በአማራ ክልል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





አቶ ቢኒያም በለጠ

# የፋሲካ በዓል ከ20 በላይ በሆኑ ቅርንጫፎቹ እንደሚከበር መቄዶንያ አስታወቀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የፋሲካ በዓል ከ20 በላይ በሆኑ ቅርንጫፎቹ ከአረጋውያንና አቅመ ደካሞች ጋር እንደሚከበር የመቄዶንያ የአእምሮ ህሙማንና የአረጋውያን መርጃ ማዕከል አስታወቀ፡፡

የማህበሩ መስራች አቶ ቢኒያም በለጠ እንዳስታወቁት፤ መቄዶንያ አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሉ ባሉት ከ20 በላይ ቅርንጫፎችና ማዕከሎች ከሰባት ሺህ አምስት መቶ በላይ አባላት አሉት፡፡

በማዕከልና በቅርንጫፎቹ የፋሲካን በዓል በተለያዩ ዝግጅቶች ለማክበር የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ያሉት አቶ ቢኒያም፣ በዓሉ በአባቶች ምርቃት፣ አረጋውያንን እንዲሁም አቅመ ደካሞችን በሚያሳትፉ የተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል ብለዋል።

በአዲስ አበባ፣ በደሴ፣ ጋምቤላ፣ ኢሉባቦር፣ ጎሬ፣ አድዋ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ አምቦ፣ ጅማ፣ እና ሌሎችም ከተሞች በሚገኙ የመቄዶኒያ ቅርንጫፎች ውስጥ ካሉ አረጋውያንና የአእምሮ ህመምተኞች ጋር በዓሉን አብረው እንደሚያከብሩ ተናግረዋል።

በጎ ነገር ማድረግ ዋጋ ባያስከፍልም በዋጋ ሊተመን የማይችል የመልካምነት ስራ ለማከናወን ዋነኛው መሳሪያ ነው ያሉት አቶ ቢንያም፤ በሁሉም እምነቶች ለበጎነትና መልካምነት ተገቢውን ቦታ የሚሰጡ በመሆናቸው በዓሉን በጋራ ለማክበር የሚፈልጉ ሁሉ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በበዓል ወቅት የተቸገሩትን መርዳት፣ መጎብኘት ታላቅ ደስታን የሚፈጥር እና ማህበራዊ ኃላፊነት ጭምር መሆኑን የገለጹት አቶ ቢኒያም፣ በተጨማሪም አልባሳትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ከመለገስ ባለፈ የሰርግ፣ የልደት፣ የሙት ዓመትና የሰደቃ ዝግጅታቸውን በመቄዶንያ ማከናወን እንደሚቻል አስረድተዋል።

ለማዕከሉ ድጋፍ ማድረግ የሚፈልጉም አጭር የጽሁፍ መልዕክት ቁጥር በ8161 ላይ ok ብለው በመላክ እንዲሁም በንግድ ባንክ የማዕከሉ አካውንት በኩል ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

የመቄዶንያ በጎ አድራጎት ማህበር ስራ አስኪያጅና የአቶ ቢኒያም በለጠ ልዩ ረዳት አቶ ራጂ ዲንሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ወቅቱ የፋሲካ በዓል የሚከበርበት በመሆኑ በማዕከሉ የሚደገፉ ሰዎችን በመጎብኘት በዓሉን በጋራ እንዲያሳልፉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በጎ አድራጊዎች እና እንግዶች በግ፣ ዶሮ፣ በሬ እያመጡ በመሆኑ አመስግነው፤ በርካታ የሚደገፉ አካላት እንደመኖራቸው መጠን በርካታ ድጋፍ የሚፈልጉ ሰዎች በማዕከሉ መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

በጎ ፈቃደኛ ሂሳብ ሰራተኞች፣ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ ሹፌሮች ባላቸው ሙያ እንዲሁም መብላት የማይችሉትን በማጉረስና የጽዳት ስራ በማከናወን ጭምር በጉልበታቸውና በዕውቀታቸው ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

ለተለያዩ አገልግሎቶችም 8131 ላይ በመደወልም ማንኛውንም መረጃ መጠየቅ የሚቻል መሆኑን ጠቁመዋል።

በፈጣን ዕድገት ላይ የሚገኘው ማዕከሉ 14 ተጨማሪ ቅርንጫፎችና ማዕከሎች በተለያዩ ከተሞች እያስፋፋ ሲሆን፤ የተገልጋዮችን ቁጥርም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ 20 ሺህ ለማድረስ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማዕከሉ ለሆስፒታል አገልግሎት የሚሆንና ከ10 ሺህ በላይ ሰዎችን ማኖር የሚያስችል ባለሁለት ቤዝመንትና ከመሬት ወለል በላይ ባለ 15 ህንጻ ግንባታ እያከናወነ ይገኛል።

ግንባታው 70 በመቶ የደረሰ መሆኑን ገልጸው፤ ቀጣይ ቀሪ ስራዎች እንዲጠናቀቁም ህዝቡ ድጋፉን እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

መቄዶንያ "ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው" በሚል ተነሳሽነት አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማንን በተለይም የአልጋ ቁራኛ የሆኑትን ዜጎች ከጎዳና ላይ በማንሳት ከ11 ዓመት በፊት የተመሰረተ ማዕከል ነው።

# ኤግዚቢሽንና ባዛሮቹ ገበያን ለማረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ :- የ2015 ዓ.ም የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ኤግዚቢሽንና ባዛር የተለያዩ ምርቶችን በአንድ ቦታ ለማግኘት እና ገበያውን ለማረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ሸማቾች ገለፁ።

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽንና ባዛር የበአል ሸመታ ላይ ያገኘናት አርቲስት ወለላ አሰፋ እንደገለጸችው፤ በባዛሩ ላይ የተለያዩ አቅርቦቶች በአንድ ቦታ የሚገኝ ሲሆን፤ ዋጋው ቅናሽ ባይኖረውም ካለው ነባራዊ የገበያ ሁኔታ አንጻር ተመጣጣኝ ነው። ለበአሉም ሁሉም እንደየአቅሙ የፍላጎቱን እየሸመተ ይሄዳል፤ ሻጩም ምርቶቹን በስፋት ለሻጭ ያቀርባል፤ ይሸጣል።

"እንደዚህ አይነት የባዛር ዝግጅቶች መዘጋጀቱ ያለውን የዋጋ ንረት በማረጋጋት ሸማቹ የሚፈልገውን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ አንድ ቦታ ለማግኘት ይረዳል፤ ለሻጭም ምርቶቹን ለማስተዋወቅ እና ለመሸጥ ይጠቅማል" ያለችው አርቲስት ወለላ ፤ አሁን ላይ ያለውን የዋጋ ውድነት ለማረጋጋት እንዲሁም የምርት አቅርቦትን በስፋት ለማግኘትና የበአል ግብይትን ቀላል በማድረግ ጉልህ አስተዋጽ አለው ብላለች።

ሌላዋ ሸማች ወይዘሮ ትግስት ቦጋለ እንደተናገሩት፤ የዘንድሮ የፋሲካ ባዛር ከገና ባዛር ጋር ሲነጻጸር ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ አነስተኛ ግብይት ይስተዋላል፡፡ በምርቶቹ ላይ ብዙም ዋጋ ልዩነት ባይኖረውም አቅርቦትን አንድ ቦታ ለማግኘት እና አማርጦ ለመግዛት ይጠቅማል ብለዋል።



ኑንያት ፍቅሬ



አርቲስት ወለላ አሰፋ



ወይዘሮ ትግስት ቦጋለ

በዚህ ባዛር ላይ የጨርቃጨርቅ አልባሳት አምራችና ሽያጭ ንግድ ላይ የተሰማራችው ወይዘሮ ኑንያት ፍቅሬ፤ እንደዚህ አይነት ባዛር መዘጋጀቱ የንግድ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ ከደንበኛ ጋር ቀጥታ ያገናኘናል፤ እራሳችንን ከሸማች ጋር በቀጥታ እንድናስተዋውቅና ለቀጣይም ደንበኞች እንድናፈራ ይጠቅመናል ስትል ገልጻለች።

የሚያቀርቧቸው ምርቶች የሀገር ውስጥ ሲሆን፤ ዋጋውም ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተመጣጣኝ ነው። ይህም ትርፍ የሚገኘው በብዛት ሲሆን አንድ ሸማች ከአንድ በላይ ምርቶችን በሚገዛበት ወቅት ነው ስትል ገልጻለች።

የዘንድሮ የአዲስ አበባ ኤግዚቢሽንና ባዛር አዘጋጅ ሴንቸሪ ፕሮሞሽን ማርኬቲንግ ማናጀር የሆኑት ወይዘሮ የአብወርቅ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ ከመጋቢት 16 እስከ ሚያዚያ 7 የተዘጋጀው ይህ የፋሲካ ባዛር ከአራት መቶ በላይ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ሻጮችን በማሳተፍ በተለያዩ ምርቶችን እያቀረቡ ሲሆን በቀን በአማካኝ ከ7500 በላይ ሸማቾች እንደሚጎበኙ ተናግረዋል።

ወይዘሮ የአብ ወርቅ የተዘጋጀው ባዛር አምራች እና ሻጭ በቀጥታ የሚገናኙበት ሲሆን፤ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በቀጥታ የሚገበያዩበት እና አምራቾችና ነጋዴዎች ምርቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበት ፤ ሸማቾች ብዙ አማራጭ የሚፈልጉበት እንዲሁም የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ነው ብለዋል።

ምርቶቻቸውን የሚያቀርቡት ሻጮች ዋጋቸው ተመጣጣኝ እንዲሆን አወዳድረው እንደሚያሳትፉ ገልጸው፣ የክትትልና የቁጥጥር ስራ እንደሚሰሩ ተናግረዋል። ለቀጣይም በተሻለ ሁኔታ እንደሚያዘጋጁ ገልጸዋል።



# "በበዓላት የሚደረጉ የማዕድ ማጋራት ሥራዎች በዓልን በደስታ እንድናከብር ያደርገናል"

## - አቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በበዓላት ወቅት የሚደረጉ የማዕድ ማጋራት መርሃግብሮች በዓልን በደስታ እንድናከብር ያደርገናል ሲሉ በአዲስ አበባ የሚገኙ አቅመ ድካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ተናገሩ።

የንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ሎሚ ጣፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትንሳኤና የኢድ አልፈጥር በዓልን ምክንያት በማድረግ ዶሮ፣ ዱቄትና ዘይት ሰጥቶኛል። ይህም በዓሉን ከሌሎች ሰዎች እኩል ሳልቸገር በደስታ እንዳከብር ያደርገኛል ብለዋል።

በበዓላት የከተማ አስተዳደሩ ለአቅመ ደካሞች እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የሚያደርገው የማዕድ ማጋራት ተግባር ለብዙዎች እፎይታን የሚሰጥ ነው ያሉት ወይዘሮ ሎሚ፤ ኢትዮጵያ ለድሆች የሚያስቡ አመራሮች፣ ባለሃብቶች እና በጎ ፍቃደኞች ወጣቶች እያፈራች በመሆኑ ኮርቻለሁ ብለዋል።

አሁን አቅመ ደካማ በመሆኔ ስራ መስራት አልችልም ያሉት ወይዘሮ ሎሚ፤ ሁሉም በየአካባቢው ልክ እንደዚሁ እየተረዳዳና እርስ በእርስ እየተከባበረ ጊዜውን ቢያሳልፍ ችግር አይኖርም። ወገን ዘመድ የለኝም ብለው የሚጨነቁ አረጋውያንና አቅመ ደካሞችም ተገቢውን ፍቅርና እንክብካቤ ስለሚያገኙ ቀሪው ዘመናቸውን ደስተኛ ሁነው እንዲያሳልፉ ያደርጋል። "ድጋፍ አድራጊዎች ሳናስበው እንዳሰቡን እግዚዓብሄር ያስባቸው"ም ብለዋል።


የቦሌ ክፍለከተማ ነዋሪ አቶ ሳሙኤል አሰፋ በበኩላቸው፤ እግሬ ላይ በደረሰብኝ የአካል ጉዳት የተነሳ እንደልቤ መንቀሳቀስ አልችልም። በዚህ የተነሳ እንደፈለኩት ተሯሩጬ የግል ስራዬን መስራት ስለማልችል ኑሮዬን የምመራው ሰዎች በሚደግፉኝ ልክ ነው። በተለይ ከተማ አስተዳደሩ የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ ማዕድ ሲያጋራኝ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል ብለዋል።

ማዕድ ማጋራቱ እንደቀላል ነገር ሊታይ ይችላል። ነገር ግን ለአቅመ ደካሞች፣ ለችግር ለተጋለጡ ቤተሰቦች፣ ለሀገር ባለውለታዎች እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ትልቅ ደስታን እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።

የየካ ክፍለከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ጣይቱ አብዶ በበኩላቸው፤ አብሮ መብላት መጠጣት እና ማዕድ ማጋራት አኩሪ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ከመሆኑ በላይ ለመደጋገፍና ለመተጋገዝ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤ አንድነትን ያጠናክራል። የማዕድ ማጋራቱ ተግባር ዘላቂ ችግርን በሚፈታ መልኩ፤ በጥናት ላይ ተመርኩዞ በቋሚነት መታገዝ የሚገባቸውን ዜጎች በመለየት፣ ዜጎችን በማስተባበር ቢሠራ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም መንግሥት ብቻውን መወጣት ስለማይችል አቅም ያላቸው ባለሃብቶች እና በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይኖርባቸዋል ያሉት ወይዘሮ ጣይቱ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለድሀ ዜጎች የማዕድ ማጋራት መደረጋቸው ሁሉም በበጎ ሊመለከተው ብቻ ሳይሆን በአቅሙ ተግባራዊ ሊያደርገው የሚገባ በጎ ተግባር ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትንሳኤ እና የኢድ አልፈጥር በዓላትን ምክንያት በማድረግ ለ256 ሺህ ለሚሆኑ አቅመ ደካሞች፣ ለችግር ለተጋለጡ፣ ለአገር ባለውለታዎች እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ አጋርቷል።



# በዕርድ ወቅት ለቆዳና ሌጦ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ በዓላት ወቅት እርድ በሚፈፀምበት ጊዜ ለቆዳና ሌጦ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማእከል ተወካይ ስራ አስኪያጅ አቶ መሃመድ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ የበዓላት ወቅት በስፋት ጥሬ ቆዳ የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለሆነ ዕርድ ሲከናወን ለቆዳና ሌጦ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

በዓመት ሁለት ሚሊዮን የበሬ፣ 10 ሚሊዮን የበግ ሌጦ እንዲሁም ስምንት ሚሊዮን የፍየል ቆዳ በአጠቃላይ 20 ሚሊዮን ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ ተሰብስቦ ለቆዳ ኢንዱስትሪዎች የሚቀረብ መሆኑን የተናገሩት አቶ መሃመድ፤አብዛኛው የቆዳ ውጤት የሚሰበሰበው በበዓል ወቅት በመሆኑ በዕርድ ጊዜ ለቆዳው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮ የፋሲካ በዓልም ሁለት ሚሊዮን ቆዳና ሌጦዎች ይሰባሰባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ በዕርድ ወቅት በቆዳው ላይ ጉዳት እንዳያጋጥም ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ ከህዝቡ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በተለይእንስሳውሲታረድደምተሚጦያለመውጣት፣ የቅርጽ ብልሽት፣ በአሰነዛዘር ወቅት የተፈጥሮ መስመርን ተከትሎ ያለመሰንዘር እና ነጋዴዎችም ቆዳውን ሲሰበስቡ ጥንቃቄ ባለማድረግ በቆዳው ላይ ጉዳት እንደሚደርስ አመልክተው፤ ከእርድ በኋላ መሬት ላይ መጎተት፣ አንድ ቦታ ላይ ሰብስቦ ማበስበስ፣ ማቆሸሽ፣ መሬት ላይ ማድረቅ እና ሌሎች የቆዳውን ጥራት እንደሚጎዱ አብራርተዋል፡፡

የቆዳና ሌጦ ጥራት እንዳይጎዳም ለእርድ የሚቀርበውን እንስሳ በዱላ አለመምታት፣ እንስሳው ለእርድ ሲጣል ከመሬት ጋር አለማጋጨት፣ እንስሳው የሚታረድበትን ቦታ ንፁህ ማድረግ፣ እንስሳው ሲታረድ ደም ተሚጦ እንዲወጣ ማድረግ፣ ቆዳው ሲገፈፍ ቅርፅን መጠበቅና በአሰነዛዘር ወቅት የተፈጥሮ መስመርን ተከትሎ መሰንዘር ይገባል ነው ያሉት፡፡

እንዲሁም ቆዳው ሲገፈፍ በቢላዋ እንዳይበሳ መጠንቀቅ፣ ቆዳው ሲሰበሰብ መሬት ላይ አለመጎተት፣ እንዳይበሰብስ መጠበቅ፣ መሬት ላይ አለማድረቅ የቆዳና ሌጦ ጥራት እንዳይጎዳ ከሚያደርጉ መፍትሄዎች ዋንኞቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በአጠቃላይ የትንሳኤ እና ሌሎች በዓላትን ምክንያት በማድረግ እርድ በሚፈፀምበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን ለቆዳው ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በጥንቃቄ ካልተሰበሰበ ወደ አምራች ኢንዱስትሪው የሚቀርበው ቆዳ ጥራት የተጓደለ ይሆናል ያሉት አቶ መሀመድ፤ይህም አገሪቱ ከቆዳ ኢንዱስትሪው ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ ከመቀነስ ባለፈ በቆዳ ኢንዱስትሪዎች ላይ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ትልቅ ተግዳሮት እንደሚፈጥር አስታውቀዋል፡፡

ህብረተሰቡ የቆዳ ምርት ውጤቶች ለሀገር እድገት ብሎም ለዜጎች የስራ ዕድል ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት በጥንቃቄ እርድ ማከናወን አለበት ብለዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው የኦዲት ግኝትና የበጀት አስተዳደር ጉድለቱን እንዲያስተካክል ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የኦዲት ግኝትና የበጀት አስተዳደር ጉድለቱን እንዲያስተካክል የመንግስት የወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በ2013 ዓ.ም በተከናወነ የሂሳብ ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርት ላይ በትናንትናው ዕለት ግምገማ አድርጓል።


የመንግስት የወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ እንደተናገሩት፤ በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጉድለቶች አሉ።

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የተፈቀደለትን በጀት 10 በመቶ መጠቀሙንና ባጠቃቀሙም ላይ የተለያዩ የኦዲት ጉድለቶች መኖራቸውን የገለጹት ሰብሳቢዋ፤ ከ2008 ጀምሮ ያልተቀረፉ የበጀት አጠቃቀም ጉድለቶች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

በ2013/14 የበጀት ዓመት ብቻ ከ16 የኦዲት ጉድለቶች መካከል ለስድስቱ ብቻ ዩኒቨርሲቲው ማስተካከያ መስጠት መቻሉን አብራርተዋል።

ምክትል ሰብሳቢዋ ዩኒቨርሲቲው የኦዲት ግኝቶቹን ለማስተካከል እያከናወነ ያለው ተግባር አበረታች መሆኑን ጠቁመው፤ ግኝቶቹ የህዝብና የሀገርን ሀብት ላልተገባ ብክነት የሚዳርጉ መሆኑ ታውቆ አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አሳስበዋል።

ከግንዛቤ ማነስ፣ ከአሠራር ብልሹነትና መመሪያን ካለመከተል የመነጩት ክፍተቶች በቀላሉ የማይታዩ



አቶ ኡቻን ኡኬሎ



አቶ ቢሆን ገለታ



ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ

መሆናቸውን ጠቁመው፤ ተመላሽ ያልተደረጉ ሂሳቦችም በአፋጣኝ ተመላሽ እንዲደረጉና የኒቨርሲቲውም ሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ክትትል በማድረግ በግኝቶቹ ላይ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበዋል።

አክለውም ዩኒቨርሲቲው የማሻሻያ የድርጊት መርሀ ግብሩን በመቅረጽ እስከ ሚያዚያ 20 ቀን 2015 ድረስ ለቋሚ ኮሚቴው፣ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሪፖርት እንዲያደርግ ትዕዛዝ አስተላልፈዋል።

የሚመለከታቸው ባለድርሻዎችም በክትትሉና እርምጃ አወሳሰዱ ላይ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አቅጣጫ በማስቀመጥ ቋሚ ኮሚቴውም የእርምጃ አወሳሰድ ሂደቱን በቅርበት እንደሚከታተል ተናግረዋል።

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ኡቻን ኡኬሎ በሰጡት ምላሽ፤ በቋሚ ኮሚቴው የተሰጡ አስተያየቶችን ለማስተካከል እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

በዩኒቨርሲቲው አሰራር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች እንዳሉም ጠቅሰው፤ ከ2008 ጀምሮ የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ በህግ የሚታዩ ጉዳዮችንም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እርምጃ ለመውሰድ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የፋይናንስ ቡድን መሪ አቶ ቢሆን ገለታ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽ፤ የሰው ሃይል አስተዳደሩ ለፋይናንስ መረጃ ባለማቅረቡ የቤት አበል ክፍያ ያለ አግባብ ለተከፈላቸው የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ከደሞዛቸው ተቀናሽ ተደርጎ እየተመለሰ እንደሆነ ተናግረዋል።

ከ2007/2008ዓ.ም ጀምሮ የነበሩ የሁለት የገንዘብ ያዥ ጉድለት ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር እንደነበር ጠቅሰው፤ ነገር ግን ይህ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዳልነበረ አስረድተዋል።

ጉድለቱ በአግባቡ የሰነድ አያያዝ ባለመኖሩ የተፈጠረ መሆኑን ያብራሩት ኃላፊው፤ አሁን ላይ ሰነዶችን በማደራጀት የነበረውን ጉድለት ወደ 800 ሺህ ገደማ ማድረስ መቻሉን አትተዋል።

# በበዓላት ወቅት ለጤና እክል ከሆኑ የአመጋገብ ሥርዓቶች መቆጠብ ይገባል

**ሄለን ወንድምነውና ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ማህበረሰቡ በበዓላት ወቅት ለጤና እክል ከሚሆኑ የአመጋገብ ሥርዓቶች መቆጠብ እንዳለበት የጤና ሚኒስቴር አሳሰበ። ከበዓል ጋር ተያይዞ ጤናቸው የተረጋገጡ እንስሳትን ብቻ ለእርድ የማቅረብ ተግባር ዋነኛ ትኩረት ሊሆን እንደሚገባም አስታውቋል።

በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ ምግብ አማካሪ አቶ ቢራራ መለሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበዓል ወቅት ከወትሮው የተለየና ቅባታማ ምግቦችን እንዲሁም የአልኮል መጠጦች በስፋት ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች መውሰድ ከጤና አንጻር የማይመከርና ለከፋ ችግር የሚያጋልጥ ነው ያሉት አማካሪው፤ የአልኮል መጠጥ አጠቃቀምን የተመጠነ ማድረግና አመጋገብን ማስተካከል ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከበዓላት በፊት ቅባት ያልበዛባቸውን ምግቦች እየወሰዱ የቆዩ ሰዎች ልክ የበዓል ዕለት በአንድ ጊዜ ቅባታማ ምግቦችን በብዛት ሲወስዱ፤ ለምግብ አለመፈጨት ችግር፣ ለተቅማጥ በሽታና ለሌሎች የሆድ ህመሞች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ እንደሚሆን አስታውቀዋል።


ችግሩን ለመከላከል በበዓል ቀን ቅባትና በርበሬ የበዛባቸውን ምግቦች በብዛት ከመውሰድ መቆጠብና በአንድ ጊዜ በርካታ መጠን ያለው ምግብ አለመመገብ ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ሁሉም ማህበረሰብ በበዓል ወቅት በይበልጥ ስለጤናው ጥንቃቄ ማድረግ ቀዳሚው ትኩረቱ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ቢራራ፤ በአጋጣሚ ችግሩ ቢፈጠር የጤና ባለሙያ ማማከርና ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ተገቢውን ሕክምና ማግኘት እንዳለበት ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ በበዓልም ሆነ ከበዓል ቀናት ውጪ የአካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እና የተመጣጠነ ምግብ



አቶ ቢራራ መለሰ



አቶ ታደሰ ሆርዶፋ

በመመገብ ጤናን የመጠበቅ ልምድ ሊዳብር እንደሚገባ የስርዓተ ምግብ አማካሪው አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብና ጤና ነክ ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክተር አቶ ታደሰ ሆርዶፋ በበኩላቸው፤ ህብረተሰቡ እንስሳትን በሚገዛበት እንዲሁም እርድ በሚያከናውንበት ወቅት የእንስሳቱን ጤና ማረጋገጥ ዋነኛ ትኩረቱ ሊሆን ይገባል።

በየመንደሩ ከሚከናወኑ ዕርዶች ይልቅ በቄራዎች ድርጅት አማካኝነት የሚከናወነው ዕርድ አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ ነው። በመሆኑም በቄራዎች አማካኝነት ጤናቸው የተመረመሩ እንስሳትን ስጋ በመመገብ እራስን ከአደጋ መጠበቅ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለፃ፤ የአዲስ አበባ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በህገወጥ መንገድ የሚዘጋጁ የእንስሳት ውጤቶች ላይ ድንገተኛ ምርመራ ያደርጋል።

በመሆኑም ማንኛውም ልኳንዳና ምግብ አቅራቢ ድርጅት ጤናው የተጠበቀ የስጋ ምርት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንደሚገባው ጠቁመዋል።

ህብረተሰቡ የእንስሳት ተዋጽኦ ምግቦችን በሚጠቀምበት ወቅት ጊዜያቸው ያላለፈና ባዕድ ነገር ያልተቀላቀለባቸው ስለመሆኑ ማጣራትና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ገልጸዋል።

በተጨማሪ ተጠቃሚው ማህብረሰብ ከበዓል ወቅት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የጤና እክሎችን ለማስቀረት የሚረዳ ጤናማ የአመጋገብ ስርዓትን መከተል ይኖርበታል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ዜና

# ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸው ምግቦች ተወግደዋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የጤና እክል የሚፈጥሩ ግምታዊ ዋጋቸው ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ምግቦችና መጠጦች ማስወገዱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ምግብ፣ መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትዕግስት በዳዳ እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ ህብረተሰቡ ቢሰራጩ የጤና እክል የሚፈጥሩ ምግቦችና መጠጦች እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡

በዚህም ግምታዊ ዋጋቸው ከ15 ሚሊዮን 710 ሺህ ብር በላይ የሚሆኑ ምግቦች፣ መጠጦች እና ቁሳቁሶችን ማስወገዱን ገልጸው፤ የተወገዱት ምግብና መጠጦች ወደ ህብረተሰቡ ቢሰራጩ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሱ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡

በዘጠኝ ወር ውስጥ ግምታዊ ዋጋቸው አራት ሚሊዮን 760 ሺህ ብር የሚሆን 42 ሺህ 700 ኪሎ ግራም ምግቦች መወገዳቸውን ያስረዱት ወይዘሮ ትዕግስት፤ በተመሳሳይ ግምታዊ ዋጋቸው 10 ሚሊዮን 938 ሺህ



ትዕግስት በዳዳ

ብር የሚሆኑ 52 ሺህ 478 ሊትር መጠጦች ተወግደዋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ግምታዊ ዋጋቸው 12 ሺህ 500 ብር የሆኑ ቁሳቁሶች መወገዳውን ጠቁመው፤ እነዚህም የምግብ ማብሰያ፣ ማቅረቢያና ማሸጊያ መሳሪያዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወር ውስጥ ከሰራቸው አንኳር ስራዎች አንዱ የምግብና መጠጥ ቁጥጥር ነው ያሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ በዚህም ለ24 ሺህ 785 ነባር የምግብ ማምረቻ ማከፋፈያ አገልግሎት መስጫ እና ችርቻሮ ተቋማት ቁጥጥር ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ 24 ሺህ 804 ላይ ቁጥጥር መደረጉን ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ትዕግስት ገለጻ፤ በቁጥጥር ሂደቱ በተቋሞች እየታዩ ያሉ ክፍተቶች ዋና ዋናዎቹ የብቃት ማረጋገጫ ያለማደስ፣ የጤና ምርመራ ካርድ አለመኖር፣ ጊዜ ያለፈበት እና የተበላሸ የምግብና መጠጥ ምርቶች ማከማቸት እንዲሁም ህገወጥ እርድና በአንዳንድ ተቋማት ምግብን ከበአድ ነገር ጋር መቀላቀል መሆናቸው ለመለየት ተችሏል፡፡

በዚሁ መሰረት በምግብ ማምረቻ፣ ማከፋፈያ፣ አገልግሎት መስጫ እና ችርቻሮ ተቋማት ላይ በተደረገው ቁጥጥር ጉድለት በተገኘባቸው 4 ሺህ 571 በሚሆኑት ተቋማት እርምጃ ተወስዷል ያሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ እርምጃው በአራት ሺህ 382 የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እና 189 ተቋማት ላይ የማሸግ እርምጃ ነው ብለዋል፡፡

## የኦሮሚያ ልዩ ኃይልን ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደገለጹት፣ የክልሉን ሰላም የሚያውኩ ሸኔና ጽንፈኛ ኃይሎች መኖራቸው እሙን ቢሆንም የክልሉ ልዩ ኃይል ሪፎርም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በአንጻሩ የክልሉ ሰላም እንደማንኛውም ክልል በክልሉ ሚሊሻና መደበኛ ፖሊስ የሚጠበቅ ሲሆን ከሚሊሻና መደበኛ ፖሊስ አቅም በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመ ደግሞ መከላከያ በቅርበት የሚከታተል ይሆናል ብለዋል፡፡

አንዳንዶቹ በሕዝቡ ዘንድ ጥርጣሬ ለመፍጠር ኦሮሚያ የልዩ ኃይል ሪፎርም እንደማያደርግ በሬ ወለደ ወሬ እየነዙ መሆናቸውን የተናገሩት ኮሚሽነር ጀነራሉ፤ ዳኑ ግን በሌሎች ክልሎች ተግባራዊ የሚደረግ የፌዴራል መንግሥት አቅጣጫ በኦሮሚያ ተግባራዊ የማይደረግበት ምንም ምክንያት እንደሌለና ነገ በተግባር የሚታይ ነገር በመሆኑ ንትርኩ እምብዛም ጠቃሚ አይደለም ብለዋል፡፡

መጀመሪያውኑ የልዩ ኃይል አደረጃጀት በአንዳንድ ክልሎች ለተፈጠሩት የጸጥታ ችግሮች ጊዜያዊ እልባት ለመስጠት መጀመሩን ያወሱት ኃላፊው፤ በሂደት እንደ አገር የተስተዋለውን የጸጥታ ችግር ለመግታት ሁሉም ክልሎች ከመደበኛ ፖሊስ በተጨማሪ ልዩ ሀይል ማደራጀታቸዉን ተናግረዋል፡፡

መከላከያና መደበኛ ፖሊስ እያለ በአንድ ሀገር ውስጥ መከላከያን የሚያክል ልዩ ኃይል መኖር ስጋት መሆኑ የህብረተሰቡ ጥያቄ በተደጋጋሚ ሲነሳ መቆየቱን ያስታወሱት ኮሚሽነር ጀነራል፤ ነገር ግን ከሕዝቡ ጋር ጥያቄ ሲያነሱ የነበሩ ኃይሎች መንግሥት ልዩ ኃይሉን በስታንዳርድ መሰረት ማደራጀት ሲጀምር "መንግሥት ልዩ ኃይልን እያፈረሰ ነው" በሚል ውዥንብር ሲፈጥሩ ማየት የሚያሳዝን ነው ብለዋል፡፡

ሕዝቡ፣እነዚህ ኃይሎች ፍጹም የትኛውንም ሕዝብ የማይወክሉ ሥራቸው ብጥብጥ መፍጠርና አገር ማፍረስ መሆኑን በመገንዘብ ክፉ ሃሳባቸውን እንዳይሸምት ጠይቀዋል፡፡

እንደ ጀነራል አራርሳ ማብራሪያ፣ ሸኔና ጽንፈኞች በሕዝቦች መካከል መተማመን እንዳይኖር ብሎም ኦሮሚያ ሰላም እንዳትሆን በተደጋጋሚ ችግር እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ መንግስት ለሸኔ የሰላም ጥሪ ማቅረቡን ተከትሎ ሸኔ የሰላም ጥሪውን ተቀብሎ ወደ ሰላም ቢመለስ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ካልሆነ ግን መንግሥት ሰላም ማስከበር ስለሚጠበቅበት እርምጃ መውሰዱ ይቀጥላል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ጽንፈኞች በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬና ጥላቻ እንዲፈጠር በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ጊዜያት ዜጎች ላይ ጥቃት መፈጸማቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ እነዚህ ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት ተጠያቂ ከማድረግ ባሻገር ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመሆን ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይፈጸም እንደሚሰራ አመልክተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ችግር እየፈጠሩ መኖር የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ዘለቄታ እንደሌለው የተናገሩት ኃላፊው፤ ማንም ዜጋ ለእኩልነትና ለአንድነት ተገዥ ሆኖ ሌላው ጋር በሰላም የመኖር ባህል ማዳበር ግዴታው ነው ብለዋል፡፡

መንግስት ከሶስት አመታት በፊት ባስቀመጠው አቅጣጫና በምርጫውም ወቅት ቃል በገባው መሰረት የአጠቃላይ የጸጥታ መዋቅሩ የሪፎርም አንዱ አካል የሆነውን የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራ ሰሞኑን ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ይታወሳል፡፡

መልሶ ማደራጀቱ በአንድ በኩል በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ዘላቂ ሰላምን ለማጽናትና በክልሎች መካከል የሚታዩ አላስፈላጊ የኃይል ፉክክሮችን ለመግታትና ክልሎች ትኩረታቸውን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያደርጉ ለማድረግ የታለመ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ ህብረብሄራዊ የመከላከያና የፖሊስ ሰራዊትን ለመገንባት ትልቅ እርምጃ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ክልሎችን ለልዩ ኃይሎች ከሚያወጡት አላስፈላጊ ወጪ በመታደግ በጀታቸውን ለልማትና ለህዝብ ልማት እንዲያውሉ እድል የሚሰጥ እንደሆነ መገለጹ ይታወሳል፡፡

## በአማራ ክልል የፀጥታ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በመፈጠሩ እና አጀንዳው በተሳሳተ መንገድ በመራገቡ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የፀጥታ ችግሮች ተፈጥረው ነበር ብለዋል።

አሁን ላይ ግን የክልሉ ሁሉም አካባቢዎች ወደ ወትሯዊ ሁኔታቸው መመለሳቸውን ገልጸዋል።

ተዘግተው የነበሩ መንገዶች ተከፍተው ኅብረተሰቡ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴው መግባቱንም ጠቁመዋል።

የአማራ ክልል መንግሥት የክልሉን ሕዝብ ጥቅም አሳልፎ አይሰጥም ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ይህንን ሕዝቡ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

ተፈጥሮ በነበረው የፀጥታ ችግር የሰው ሕይወት መጥፋቱን እና የአካል ጉዳት መድረሱንም አንስተዋል። በነበረው የመንገድ መዘጋት የምርቶች ዝውውር ላይ እክል ፈጥሮ ቆይቷልም ብለዋል።

የገጠመውን ችግር መልሶ ለማረጋጋት በጥበብ መሠራቱን የጠቆሙት ቢሮ ኃላፊው፤ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከወጣቶች እና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተደረገው ምክክር ወደ ከፋ ቀውስ እንዳይቀየር መቆጣጠር መቻሉንም ገልጸዋል።

ጥያቄዎች ሕጋዊ በሆነ መንገዶች ብቻ እንዲመለሱ ማድረግ እንጂ በአመፅ መንገድ መራመድ በቀዳሚነት የሚጎዳው ክልሉን ነው ብለዋል።

የልዩ ኃይል መልሶ ማደራጀት ላይ ገጥሞ የነበረውን የመረጃ ክፍተት በተወሰነ ደረጃ በልዩ ኃይሉም ሆነ በሕዝቡ ውስጥ መደናገር ፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፤ አሁን ላይ ግን ልዩ ኃይልን መልሶ ማደራጀት ጠንካራ ሀገራዊ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት ያለመ መሆኑን መተማመን ላይ እየተደረሰ ነው ብለዋል።

በዚህም አሁን ላይ የልዩ ኃይል አባላት በቀረቡላቸው አማራጮች ገብተው አስፈላጊው መልሶ ማደራጀት ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

ወደ ወረዳዎች ተበትነው የነበሩ የልዩ ኃይል አባላትም ተመልሰው ሪፖርት እያደረጉ ስለ መሆኑም ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ በማኅበራዊ ሚዲያ አፍራሽ ተልዕኮ ባላቸው አካላት የሚሠራጩ መረጃዎችን ከመቀበል እንዲቆጠብም አሳስበዋል።

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ የታቀዱ የልማት ተግባራትን በውጤታማነት ለማሳካት ርብርብ እየተደረገ ስለመሆኑ ተናግረዋል። የክልሉን ኢኮኖሚ በተሻለ መልኩ በማሳደግ ችግሮችን የመቋቋም እና ፈተናዎችን የመሻገር አቅሙን ማጎልበት ያስፈልጋልም ብለዋል።

የምክር ዝግጅት ሥራዎችን በአግባቡ ለመከወን ሁሉም የየድርሻውን በትክክል እንዲወጣም ጠይቀዋል።

ለወጣቶች የሥራ ዕድል የመፍጠር ጉዳይም ተጠናክሮ መቀጠል አለበትም ብለዋል።

በቀጣይ ቀናት በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚከበሩ በዓላትን በሰላም ለማሳለፍ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉንም አቶ ግዛቸው ተናግረዋል ሲል የዘገበው ኢቢሲ ነው።

ኅብረተሰቡ እንደተለመደው በሰላም እና በፍቅር እርስ በእርስ በመረዳዳት በዓሉን እንዲያከብርም ጥሪ አቅርበዋል።

## "የቀደሙትን የመከባበርና...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መልአከ ምህረት አማረ አበበ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ በታሪኳ ምንም እንኳን በውስጥና በውጭ ጠላት ስትፈተን የቆየች ሃገር ብትሆንም የቀደሙት አባቶች እርስ በርስ በመከባበርና በመቻቻል ውስጣዊ ችግሮችን በመፍታት የሃገሪቱን የግዛትና ህዝባዊ አንድነት አስቀጥለዋል። አሁንም ያለው ትውልድ በየአካበቢው የማያግባቡና ለግጭቶች ምክንያት የሆኑ ልዩነቶችን ቁጭ ብሎ በመነጋገር፤ በመደማመጥ ፤ በመከባበር እና በመቻቻል ሊፈታው ይገባል።

‹‹ሀገራችን ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር የተመረጠችና የፈጣሪን ትዕዛዝ ተቀብለው የሚተግብሩ ፅኑ አማኞች ያሏት ሃገር ናት። ይህች ሃገር ብዝሃ-ቋንቋ፤ ሃይማኖትና ማንነት ያሉባት ብትሆንም የፈጣሪ ጥዕዛዝ የሆኑትን የመከባበር፤ የመቻቻል፤ የመረዳዳት ትዕዛዞችን በማስጠበቅ በአለም ላይ ስሟ ገኖ ነው የሚገኘው›› ያሉት አስተዳዳሪው፤ያ እሴት ባይሆን ኖር እንደህዝብም ሆነ እንደአንድ ሃገር መቀጠል አዳጋች እንደነበር አንስተዋል። እስከዛሬ ባለው ሂደት ህዝቡ ተከባብሮ እና ተቻችሎ ሃገሪቱን የማስቀጠል ግዴታ ስላለበት ይነስም፤ ይብዛ ይህንን እሴት ይዞ መቆየቱን ተናግረዋል።

ለበርካታ ዓመታት ኢትዮጵያ በብዙ ችግርና ጫና ውስጥ መቆየቷን አስታውሰው፤ ‹‹ይሁንና ያንን ክፉ ጊዜ ማለፍ የቻልነው የውስጣችንን ችግር በውስጣችን በመያዝ፤ ተቻችለንና ተከባብረን ስለኖርን ነው። አሁንም መቀጠል ያለበት እሱ ነው›› ብለዋል። አክለውም ‹‹አሁን ላይ የእምነት ተቋማትንም ሆነ ሃገርን ለምንመራ አካላት እነዚህን ትልልቅ እሴቶች ከአባቶቻችን በመውረሳችን እና ኃላፊነቱን ስለተቀበልን ነው ሃገርን ለማስቀጠል እየተጋን ያለነው››ሲሉ አስረድተዋል።

አንዳንድ ሰዎች አሁን ላይ እነዚህ የቀደሙት መልካም እሴቶቻችን ጠፍተዋል ብለው እንደሚያምኑ የተናገሩት መልአከ ምህረት አማረ፣ ነገር ግን እይታቸው ሊለያይ ይችላል እንጂ ሙሉ ለሙሉ ጠፍቷል ተብሎ እንደማይታሰብ እምነታቸውን ተናግረዋል።

‹‹አሁንም በሀገራችን መደማመጥ፤ መከባበርና መቻቻሉ አለ። ይህንን ስል ግን ከዚያ ተቃራኒ የሆነ እና ፅንፍ የወጣ ነገር ፈፅሞ የለም እያልኩኝ አይደለም›› ያሉት መልአከ ምህረት አማረ፤ እዚህ እዚያም ብቅ ብቅ የሚሉ ከኢትዮጵያዊነት ስነ-ምግባር ያፈነገጡ፤ ህዝባዊ አንድነትን የሚሸረሽሩ ተግባራት የሚታዩ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በመሆኑም እነዚህ እሴቶቻችን መቀጠል እንዲችሉ ከተፈለገ የሃይማኖት አባቶች ፤ የፖለቲካ ተዋናዮች፤ እያንዳንዱ ዜጋ የመከባበርም፤ የመደማመጥም ባህል የግድ ማዳበር እንደሚገባው አስገንዝበዋል። ‹‹በመካከላችን አለመግባባት እና ልዩነቶች ማጥበብ የሚቻለው፤ ዝም ብሎ በመመልከት አልያም በማባባስ ሳይሆን በመከባበርና በመደማመጥ መነጋገር ሲቻል ነው›› ብለዋል። ለዚያ ደግሞ እንደሃገር ዋጋ እያስከፈሉ የሚገኙ ፤ ፅንፍ የወጡና የማያግባቡ ልዩነቶቻችንን ማስወገድ ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል።

‹‹አሁንም ቢሆን ይህንን ችግር ማስተካከል የሚቻልበት እድል አለ፤ አልረፈደም። በተለይ ይህ ችግር በሁሉም ቦታ የሚታይ ባለመሆኑ የቀደሙት የመቻቻል፤ የመከባበር እሴቶቻችን የሚስፋፉበት ሁኔታ መፍጠር መቻል አለብን›› በማለት አሳስበዋል። በተለይ የእምነት አባቶችና መንግስት እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍል በየስራ ድርሻው ሚናውን በመወጣት የቀደሙትን እሴቶቻችንን ማስቀጠል እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹ይህንን ማድረግ ካልቻልን በታሪክም፤ ባለንበት የስራ መስክም ተወቃሽ ነው የምንሆነው›› ብለዋል።

እንደ አስተዳዳሪው ገለፃ፤ እሴቶችን የማስቀጠልም ሆነ ልዩነቶችን የመፍታቱ ጉዳይ የአንድ አካል የስራ ድርሻ ብቻ ሊሆን አይገባም፤ ሁሉም የየራሱን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል። በተለይ ትናንት አባቶች ያስረከቡትን የታፈረችና የተከበረች ሃገር ዛሬም ባለው ትውልድ እንድትቀጥል የላቀ ትጋት ይጠበቃል። ለዚህ ደግሞ ወጣቱንና የነገ ሃገር ተረካቢ ትውልድን ሁሉም ሳይሰለች ማስተማር ቀዳሚ ስራው መሆን አለበት።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት



ዜጎች የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ መደላድል የፈጠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች

ገጽ 14



## ‹‹የትንሳኤውን በዓል ስናከብር የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን ይገባል››

**መልአከ ምህረት አማረ አበበ**
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በየረር በር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ

ገጽ 6



አዛውንቷ ሎተሪ አዟሪ

ገጽ 16

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪካዊቷ መልህቅ

# የአዲስ አበባ የቱሪዝም መስያ ተምሳሌት

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

አዲስ አበባ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ፤ ከኒውዮርክ ከጄኔቭ ከተማ ቀጥሎ የብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ኤምባሲዎች ያለባት ነች:: የኢትዮጵያ አየር መንገድ መነሻ መሆኗም ብዙ ተሰብሳቢዎች እና ትራንዚት የሚያደርጉ ማለትም (አርፈው በማግስቱ በሁለት ቀን ወይ በሦስት ቀን ወደ ሌላ ሀገር ከተማ) የሚሄዱ ሰዎች ይመጡባታል:: ቱሪስቶች መዲናዋን ባላቸው በአጭር ጊዜ ለማስጎብኘት፣ገፅታዋን ለመገንባት፤ በሆቴሎቹ ተዝናንተው እንዲወጡ የሚያስችሉ ተስፋ ሰጪ ጅማሬዎች በቢሮው እየታዩ ነው::

ቱሪስቶችም በመዲናችን ተዝናንተው ዶላራቸውን አፍሰው ሊሄዱ የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸት መረባረብ ይገባል:: አየር መንገዱን ጨምሮ ሆቴሎች፣ የአርት ጋለሪዎች ፣ ቤተ መዘክሮች ፣ባህላዊ ምግብ ቤቶችና ዘፈንና ውዝዋዜ ቤቶች፣ ባህላዊ አልባሳት መሸጫ እና የፋሽን ባለሙያዎች ተነቃቅተው በጋራ ሊሠሩ የሚችሉበት ነው:: የውጭ ምንዛሪ ይሰባሉ፣ ገቢ ያገኛሉ::

ቢሮው አዲስ አበባን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ከሚያስችለው ሥራ መካከል የDiscover addis Ababa ማለትም አዲስ አበባን ይጎብኙ አርማ አንዱ ነው:: ባለፈው ሳምንት በመዲናዋ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙዚየም በተካሄደ የግማሽ ቀን ዐውደ ጥናት የተወሰነውን ማቅረባችን ይታወሳል:: ለዛሬ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአለፈለገ ሰላም የስዕል ትምህርት ቤት የዲዛይን ዲፓርትመንት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን ታፈሰ አርማውን አስመልክቶ የሰጡትን ሙያዊ አስተያየት ቀንጭበን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

የአዲስ አበባ ባህል ፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ካካሄዳቸው ጥናቶች ውስጥ ብዙ ውይይት ተደርጎበት «አፍሪካዊቷ መልህቅ» የሚለው ከተማውን ሊመጥን ይችላል ተብሎ ተመረጠ:: ቢሮው «አፍሪካዊቷ መልህቅ» የሚለውን መለያ ቃል ወደ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለፈለገ ሰላም የስዕል ትምህርት ቤት አምጥቶ ወደ ምስል እንዲቀየርላቸው አስበው ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም ሀብት በተለያዩ አካላት ማቀፍ እንዲቻል ሠሩ ::

በከተማው ውስጥ የተለያዩ የቱሪዝም ሀብቶች አሉ:: ቆየት ያሉ ታሪካዊ ህንፃዎች፣ ኪነ ሀብቶች፣ ሙዚየሞች፣ በቅርቡ የተገነቡ ሰፋፊ ፓርኮች አሉ:: የስዕል ትምህርት ቤቱ የዲዛይን ዲፓርትመንት ኃላፊ ተስፋሁን እንደተናገሩት፤ አፍሪካውያን ባይተዋርነት እንዳይሰማቸውና የቤተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው፣ መዲናዋን ከተማችን ናት እንዲሉ፣ ምን ዓይነት መልክ፣ ቅርፅ እንስጠው በሚል ተጠንቶ፤ ስሜቱ፣ ሁሉንም እንዲይዝ አረንጓዴ ተደርጓል:: በተለይ ደግሞ የአፍሪካ ሀገራትን አማካይ ቀለማቸው በማየት፤ የአፍሪካ ኅብረት መለያ ምልክት ከምን ተነስተው እንደሠሩት ተጠንቶ አርማውን ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

አክለውም፤ መዳረሻ መንገዱ (ፓዝ) የአፍሪካዊነት ስሜት እንዲያመጣ የተሳለው ነው:: የመዳረሻ መንገዱን በመዘርጋት ይህንን አፍሪካዊነትን ስሜት እንዲያመጣ የማድረግ ሥራ ነው:: የአፍሪካ ካርታ የሚመስል ጥበብ ነው እንጂ የአፍሪካ ካርታ አይደለም ሲሉ አቶ ተስፋሁን ይናገራሉ::

አደይ አበባው የአፍሪካ ቅርጽ በሚመስል ፓዝ ላይ የተሳለ ነው:: የኢትዮጵያ የተለየ አበባ ነው:: ስምንት ኮከባማ ቅጠል፣ ዘለላ ወይም ዘርፍ አሉት:: አደይ አበባ በተለያዩ ሁኔታዎች የሰው ልብ ውስጥ በትዝታ የሚሰርፅ ነው:: አደይ አበባ አዲስ ዓመት ሲከሰት መስኩን የሚያስውቡት፣ የሚያፈኩት የአዲስ ዘመን ጌጥና ምልክት፣ የምስራች ናቸው:: እናም የአደይ አበባን ምልክት መጠቀሙ ጎብኚዎችንም ለመሳብ ይረዳል በሚል እንደ አርማው የተመረጠ ነው::

የአደይ አበባ በዜጋው ሁሉ ኅሊና ውስጥ ያለ ነው:: በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች፤ በህፃናቱ በአዛውንቱ፣ በተማሩት ባልተማሩት ፣በኮረዳዎቹ በጎረምሶቹ፣ በመበለቱ በባልቴቱ፣ በወታደሩ በወዛደሩ፣ በከተሜው በገጠሬው የተለያየ ፍልስፍና ባለውና በሌለው፣ በድሀውና በሀብታሙም ዘንድ በሙሉ ይታወቃል:: አደይ አበባ ሲነሳ መልካም ዕሳቤ አለ:: ከአሮጌው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን፣ ከክረምት ጨለማ ወደ መጸው ብርሃን የምንሸጋገርበት ምልክት ነው::

ከዛ በተጨማሪ በሀገራችን እንግዶችን ስንቀበል በተለይ ዲፕሎማቶችንና የውጭ ባለሥልጣኖችን ቀይ ምንጣፍ የነበረው የእንግዶች መቀበያ አረንጓዴና አደይ አበባ ምስሎች ያሉበት ምንጣፎች አንጥፈው ሲቀበሉ እየታየ ነው:: ለአደይ አበባ የሰጠነው ክብር እየሰፋ ነው :: መዲናችንም ስሟ አዲስ አበባ ነው:: አደይ አበባ ደግሞ በአዲስ ዘመን የሚበቅል አዲስ አበባ ነው:: ስዕሉ ከመዲናችንም ስም ጋርም አብሮ ይሄዳል:: በየቤቱም ለአዲስ ዓመት አደይ አበባ ከቄጠማዎች ጋር ተደርገው ይጎዘጎዛሉ:: በተጨማሪም አደይ አበባዎች ሰብስቦ አንድ ላይ በማሰር በብርጭቆ ውሃ አድርጎ ለሁለት፣ ለሦስት ቀን የአዲሱ ዓመት የቤት ጌጥ ውበት እንዲሆኑም ይደረጋል:: ከቱሪዝም ጋር የሚመጡ እንግዶችን የሚቀበል ጥሩ ወካይ ምልክት ነው በሚል የተመረጠው ነው::

በአርማው ላይ የአደይ አበባው አቀማመጥ ግማሽ ጐኑ ምሥራቅ አፍሪካ ላይ ሲሆን፤ ቀሪው ደግሞ አፍሪካን ተሻግሮ የሚያልፍ ነው:: ይሄም የቱሪዝም ሀብታችንን ለተለያዩ ዓለማት ፣የመጐብኘት ፍላጐት ላላቸው ኢትዮጵያን መመርመር ለሚፈልጉ አካላት ሁሉ ሦስቱ ኮከቦች ከአፍሪካ ውጭ ፤የአበባዎች ዘለላዎች በሙሉ ወደ ውስጥ አንድ ነጥብ ስር የሚሰባሰቡ ናቸው:: በመሀል ያላውም የአበባው ፍሬ ወይም እምብርት መነሻ የኢትዮጵያ የቱሪዝም መለያ The Land Of Origin ላንድ ኦፍ ኦሪጅን (ምድረ ቀደምት) የሚለውን ይወክላል:: አደይ አበባዋ ከዚህ ወካይ ምስል መካከል አንዷ ናት::

## የዘመን እንግዳ

# ‹‹የትንሳኤውን በዓል ስናከብር የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን ይገባል››

*- መልአከ ምህረት አማረ አበበ*
*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በየረር በር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ*

ማህሌት አብዱል

ለአገር ሰላምም ሆነ ሕዝባዊ አንድነት መረጋገጥ የእምነት ተቋማት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው እሙን ነው። በእስካሁን የኢትዮጵያ ታሪክም የአገር ግዛታዊ አንድነት እንዲጠበቅ፤ በመቻቻል የተመሠረተ ሕዝባዊ አንድነት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል። በተለይም አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ አማኝ መሆኑ የእምነት አባቶች አስተምህሮ ተቀብሎ የአገሪቱ የመከባበርና የመቻቻል እሴቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ምክንያት እንደሆነ ይነሳል። አገሪቱ የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች በፅናት እንድታልፈውና የአንዱ ቤተ- እምነት ተከታይ ከሌላው እምነት ተከታይ ጋር በመደጋገፍ፤ ከውጭ የሚቃጣውን ሴራ ማክሸፍ የተቻለውም ተቋማቱ ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ነው።

ባለፉት አምስት ዓመታትም ኢትዮጵያ ከውስጥም ሆነ ከውጭ አጋጥሟት የነበረውን ብርቱ ፈተና እንደቀድሞው ሁሉ በፅናት ማለፍ የቻለችው በእነዚሁ የእምነት ተቋማት የላቀ ርብርብ እንደሆነ በተጨባጭ ታይቷል። በተለይም አማኙን ሕዝብ ለሰላም በማስተባበር፤ በፆምና በጸሎት ፈጣሪውን እንዲማፀን በማድረግ ረገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሠርተዋል፤ በዚህም አወንታዊ የሆነ ውጤት መታየት ተችሏል። ካለፉት ሁለት ወራት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን፣ እንዲሁም የእስልምና እምነት ተከታዮች በፆምና በብርቱ ጸሎት ለአገራቸው ዘላቂ ሰላም ፈጣሪያቸውን ሲማፀኑ ቆይተዋል፤ በእነዚህ ጊዜያትም የተቸገሩ ወገኖቻቸውን በመደገፍ ኃላፊነታቸውን እየተወጡም ይገኛሉ።

አዲስ ዘመን ጋዜጣም የትንሳኤ በዓል በማስመልከት በበዓሉና በአገራዊ ሰላም እንዲሁም ሕዝባዊ እሴቶች ዙሪያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በየረር በር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ የሆኑትን መልአከ ምህረት አማረ አበበን አነጋግሯቸዋል። መልአከ ምህረት አማረ አበበ ከሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ በነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን፤ ከአድማስ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ ዲፕሎማ እንዲሁም ከጌጅ ኮሌጅ በማኔጅመንት ተጨማሪ ዲግሪ ማግኘት ችለዋል። በደብረሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን በመምህርነት፤ በመጠል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን፣ ሰሚት ደብረኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን፣ ደብረ ኢያሪኮ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅትም በየረር በር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በዋና አስተዳዳሪነት እየሠሩ ይገኛሉ። ከአስተዳዳሪው ጋር ያደረግነውን ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በአብይ ፆም ወቅት የእምነቱ ተከታዮች ከፆም ባሻገር ምን ምን በጎ ምግባራትን ሲያከናውኑ እንደቆዩ ያብራሩልንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**መልዓከ ምህረት አማረ፡-** እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከምግብና መጠጥ ፆም ባሻገር ከአንድ ምዕመን ወይም አማኝ የሚጠበቁ በርካታ በጎ ምግባራት አሉ። ከእነዚህም መካከል በእስከዛሬው ሕይወቱ ሲፈፅማቸው ከነበሩ መጥፎ ተግባራት ተቆጥቦና ንስሃ ገብቶ ፈጣሪ የሚወዳቸውን መልካም ነገሮች መከወን ነው። በዚህ የፆም ወቅት አማኙ በተለይ ከራሱና ከፈጣሪ ጋር ታርቆ በጥሞና የሚያሳልፍበት፤ ከራሱ የሚያልፍ ሰላም ለሕዝብና ለወገኑ ለመስጠት የሚተጋበት ነው። ከዚህ አኳያ ቤተክርስቲያናችን ባለፉት ሁለት ወራት ዋነኛ ተልዕኮዋ የሆነውን ስለሰላም መስበክና ማስተማር ለአገር ሰላም ምዕመኑን ወደ መልካም አቅጣጫ የመመለስ ሚናዋን ስትወጣ ቆይታለች።

ቤተክርስቲያኒቱ ለሰላም ቅድሚያ የምትሰጥበት ዋነኛ ምክንያትም የእምነታችን መሠረት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለሰዎች ልጆች ደህንነትና ሰላምን ለመስጠት በመሆኑ ነው። እንደሚታወቀውም አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ሲወለድና ትንሳኤውን ሲያበስር የመጀመሪያ ሥራው ሰላምን መስበክ ነበር። ከዚህ ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በሞቱ አዝነው ተቀምጠው ለነበሩ ሐዋርያት ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ብሎ ከሙታን መነሳቱን አብስሯቸዋል፤ መፅናናትም ሆኖላቸዋል። ለዚህም ነው ቤተክርስቲያናችን ከሁሉ በላይ ለሰላም ቅድሚያ ሰጥታ በፆም ወቅት ስታስተምርና ምዕመኑን ለአገር ሰላም ስታስተባብር የቆየችው።

በመሠረቱ ዛሬ በዚህች ዓለምም ሆነ ለሰው ልጆች ሁሉ ከምንም በላይ የሚያስፈልገው ሰላም ነው፤ ሰላም ሲኖር ብቻ ነው የምድር ፍጥረት ሁሉ ተረጋግቶ መኖር እና መሥራት የሚችለው። ሰላም ካለ ሁሉም ነገር አለ። ለምዕመናን ህብረት ፤ ለዚህች አገር አንድነት ሰላም ወሳኝ ሚና ነው ያለው። ኢትዮጵያ አገራችን ዛሬ በብርቱ እየተፈተነች ያለችው በሰላም እጦት ነው። በየአካባቢው ሰላም ማስፈን ባለመቻሉ የሰው ልጆች ቀያቸውን ለቀው ለስደት ተዳርገዋል፤ ተርበዋል፤ ተንከራተዋል። አገሪቱም የምታከናውናቸው የልማት ሥራዎች ተስተጓጉለውባታል። ድህነቱም በርትቶባታል። በመሆኑም የመጀመሪያ ሥራችን መሆን ያለበት ሰላም ለቤተክርስቲያን፤ ለምድራችን እንዲሆን መፀለይና ለሰላም መሥራት ነው። ዜጎችም የመጀመሪያ ምርጫቸው መሆን የሚገባው ሰላም ነው።

ከሰላም ባሻገር ግን በእነዚህ ሁለት ወራት መላው የእምነቱ ተከታዮች የተቸገሩትን በመርዳትና የሌላውን ሸክም በመሸከም ክርስቲያናዊ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ነው የቆዩት። መተባበር ያስፈልጋል። በተለይ ደግሞ በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው ግጭት ምክንያት ቤት ንብረታቸውን ጥለው ጎዳና የወጡን በመርዳትና የተለያዩ በጎ ምግባራትን ሲያከናውኑ ነው የቆዩት። ምክንያቱም ፈጣሪ እንደሚያዘው አንዱ ጠግቦ ሌላው ተርቦ ማደር የለበትም። በመሠረቱ የተቸገሩትን ባለን አቅም መደገፍና መርዳት ካልቻልን ጾምና ጸሎት ብቻውን በቂ አይደለም፤ በፈጣሪም ዘንድ ቅቡልነት አይኖረውም። ልክ እንደፆሙ ወቅት ሁሉ የትንሳኤውንም በዓል ስናከብር በብዙ ጭንቅ ውስጥ ያሉ በርካታ ወገኖቻችን በማሰብና ያለንን በማካፈል ፍቅራችንን ልናሳያቸው ይገባል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ከምዕመኑ ምን ምን ሥራዎች ይጠበቃሉ?**


**መልአከ ምህረት አማረ፡-** በአገር ሰላም የሚፈጠረው በመጀመሪያ በግለሰብ ደረጃ ሰላም ሲኖር ነው። ይህም ማለት ማንኛው ግለሰብ የሰላም ሰው መሆንና ከወገኖቹ ጋር በሰላም ለመኖር ፍቃደኛ ሆኖ ሲገኝ ነው። ሌሎችን ‹‹እንዲህ እና እንዲህ አድርጉ›› ከማለት ይልቅ ‹‹እኔ አጠገቤ ላሉ ሰዎች፤ ለቤተክርስቲያኔ፤ ለአገሬ ሰላም ምን ሠራሁ?›› ብሎ ራስን መጠየቅ እና ራሳችንን ማየት ያስፈልጋል ማለት ነው። አንዱ አካል ብቻ በሚሠራው ሥራ ዘላቂ ሰላም ማምጣት አይቻልም። ስለዚህ ሰላም የሁሉም ነው፤ ለአንድ አካል ብቻ የሚተው አይደለም። አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደግሞ የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ ተግባሯም ሆነ ተልዕኮዋ ሰላም ነው። ‹‹ጸሎቷን ስትጀምር ሰላም ለሁሉም›› ብላ ነው የምትጀምረው። ስትጨርስም ‹‹እትሁ ለሰላም›› ብላ ነው የምትጨርሰው። ይሄ ለሰላም የምትሰጠውን ዋጋ እና ታላቅነት የሚያሳይ ነው።

በነገራችን ላይ ሰላም ለአንድ አካል ብቻ የሚተው የቤት ሥራ አይደለም ሲባል ከመንግሥት፤ ከሕዝቡ፤ ከቤተ-እምነቶች ጋር በቅንጅት የሚሠራ በመሆኑ ነው። ልክ አንድ እጅ ብቻውን እንደማያጨበጭበው፤ አንድ እንጨት እንደማይነደው ሁሉ በዚህች አገር ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ከተፈለገ ሁሉም አካል ተባባሪ መሆንና የራሱን አሻራ ለማሳረፍ ፍቃደኛ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም የሰላም ዋጋውም በዚያው ልክ ነው። ደግሞም ሰላም ሲጠፋ ባለስልጣን ነው፤ ድሃ ወይም ሃብታም ነው ብሎ አይመርጥም። ሁሉንም ነው የሚያጠፋው። በተቃራኒው ሰላም ሲመጣ ደግሞ ለተቸገረውም፤ ለተራበውም ሰላም እስካለ ድረስ ልንደርስለት እንችላለን። በአጠቃላይ ዘላቂ ሰላም የሁላችንም አስተዋፅኦ የሚሻ ተግባር ነው ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸው መልካም እሴቶች አሁን ላይ እየተመናመኑ ስለመምጣታቸው ይነገራል፤ እርስዎ በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር የተመረጠችና የፈጣሪን ትዕዛዝ ተቀብለው የሚተግብሩ ፅኑ አማኞች ያሏት አገር ናት። ይህች አገር ብዝሃ-ቋንቋ፤ ሃይማኖትና ማንነት ያሉባት ብትሆንም የፈጣሪ ትዕዛዝ የሆኑትን የመከባበር፤ የመቻቻል፤ የመረዳዳት ትዕዛዞችን በማስጠበቅ በዓለም ላይ ስሟ ገኖ ነው የሚገኘው። ያ እሴት ባይኖረን ኖሮ እንደሕዝብም ሆነ እንደአንድ አገር መቀጠል ባልቻልን ነበር። ሁላችንም ብንሆን ተከባብረን እና ተቻችለን አገራችንን የማስቀጠል ግዴታ ስላለብን ይነስም፤ ይብዛ ይህንን እሴት ይዘን ነው የቆየነው። ለበርካታ ዓመታት ኢትዮጵያ በብዙ ችግርና ጫና ውስጥ ነው የቆየችው። ይሁንና ያንን ክፉ ጊዜ ማለፍ የቻልነው ግን የውስጣችንን ችግር በውስጣችን በመያዝ፤ ተቻችለንና ተከባብረን ስለኖርን ነው። አሁንም መቀጠል ያለበት እሱ ነው ባይ ነኝ።

የቀደሙት አባቶቻችን በትልልቅ እሴት ይታወቃሉ፤ ለአብነት ያህል አገርን በማስከበር፤ በማስቀጠል፤ እርስ በርስ በመደጋገፍ አብሮ በመብላትና በመጠጣት እንዳቆዩልን መጥቀስ ይቻላል። አሁን ላይ የእምነት ተቋማትንም ሆነ አገርን ለምንመራ አካላት እነዚህን ትልልቅ እሴቶች ከአባቶቻችን በመውረሳችን እና ኃላፊነቱን ስለተቀበልን ነው አገርን ለማስቀጠል እየተጋን



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ያለነው።አንቺ እንዳነሳሽው አንዳንድ ሰዎች አሁን ላይ እነዚህ የቀደሙት መልካም እሴቶቻችን ጠፍተዋል ብለው እንደሚያምኑ እረዳለሁ፤ ነገር ግን እይታቸው ሊለያይ ይችላል እንጂ ሙሉ ለሙሉ ጠፍተዋል ብዬ አላምንም።አሁንም በአገራችን መደማመጥ፤ መከባበርና መቻቻሉ አለ።ይህንን ስል ግን ከዚያ ተቃራኒ የሆነ እና ፅንፍ የወጣ ነገር ፈፅሞ የለም እያልኩኝ እንዳልሆነ እንድትረጂልኝ እሻለሁ።እዚህም እዚያም ብቅ ብቅ የሚሉ ከኢትዮጵያዊነት ሥነምግባር ያፈነገጡ፤ ሕዝባዊ አንድነትን የሚሸረሽሩ ተግባራት ይታያሉ።ያ ግን ሙሉ ለሙሉ ጠፍቷል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም።

በመሆኑም እነዚህ እሴቶቻችን መቀጠል እንዲችሉ ከተፈለገ ሁላችንም ማለትም የሃይማኖት አባቶች፤ የፖለቲካ ተዋናዮች፤ እያንዳንዱ ዜጋ የመከባበርም፤ የመደማመጥም ባህል የግድ ማዳበር ይገባናል።በመካከላችን አለመግባባት እና ልዩነቶች ማጥበብ የሚቻለው፤ ዝም ብሎ በመመልከት አልያም በማባባስ ሳይሆን በመከባበርና በመደማመጥ መነጋገር ሲቻል ነው።ለዚያ ደግሞ ፅንፍ የወጡና የማያግባቡንን ልዩነቶቻችን ማስወገድ ይገባናል ብዬ አምናለሁ።እርግጥ ነው አሁን ላይ እንደምናየው የሚያስማሙን ልዩነቶች ሰፍተዋል።ይህ የመነጨው ምንአልባት የፖለቲካው ይዘትም የፈጠረው ሊሆን ይችላል።ነገር ግን አንዱ ሌላውን የሚያይበት እይታ እንደአገር ስናየው ዋጋ እያስከፈለን ነው ያለው።

ያም ቢሆን ይህንን ችግር ማስተካከል የሚቻልበት እድል አሁንም አለ።ይህ ችግር በሁሉም ቦታ የሚታይ ባለመሆኑ የቀደሙት የመቻቻል፤ የመከባበር እሴቶቻችን የሚስፋፉበት ሁኔታ መፍጠር መቻል አለብን።እኛም እንደእምነት አባት ሆንን ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል በየሥራ ድርሻቸው ሚናውን በመወጣት የቀደሙትን እሴቶቻችንን ማስቀጠል ይገባናል።ይህንን ማድረግ ካልቻልን በታሪክም፤ ባለንበት የሥራ መስክም ተወቃሽ ነው የምንሆነው።ቀድሞ እንደገለፅኩት የአንድ አካል የሥራ ድርሻ ብቻ ሊሆን አይገባም፤ ሁላችንም የየራሳችንን ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።በተለይ ትናንት አባቶች ያስረከቡን የታፈረችና የተከበረች አገር ዛሬም ባለው ትውልድ እንድትቀጥል የላቀ ትጋት ይጠበቅብናል።ለዚህ ደግሞ ወጣቱን ትውልድ ሁላችንም ሳንሰለች ማስተማር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ግን ደግሞ በተለይ ወጣቱ ላይ ስሚታየው ኢ-ስነምግባራዊ እና ከኢትዮጵያዊነት ሞራል የወጣ ተግባር በዋናነት የእምነት ተቋማት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ባለመወጣታቸው እንደሆነ ይነሳል። ይህስ ምንያህል ተጨባጭ ነው?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** እውነት ነው! አሁን ያለው ትውልድ ድጋፍ ይፈልጋል።አንቺ እንዳነሳሽው የእምነት አባቶች በተወሰነ ደረጃ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ብዬ አላምንም።የእምነት አባቶች ትውልዱን በሚገባ የመቅረፅ ትልቅ ኃላፊነታቸው ብቻ ሳይሆን ዋነኛ ሥራቸውም ይኸው ነው።ይሁንና ችግሩ በእነሱ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ የሚመለከተው ሁሉ በሚገባ ኃላፊነቱን ተወጥቷል ብዬ አላምንም።ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ መንግሥት ድረስ ሁሉም የቤት ሥራውን በሚገባው ልክ አልሠራም።በተለይም በሉላዊነት ሰበብ እየመጣ ያለው ከባህላችንና ከወጋችን እንዲሁም ከእምነታችን ያፈነገጠ ስልጣኔ በእያንዳንዱ ቤት፤ በእያንዳንዱ ተቋም ላይ ብዙ ጫና አሳድሯል።እርግጥ ነው፤ ሉላዊነት የራሱ ጥሩ ጎን አለው፤ ልንማራቸውና እንደተሞክሮ የምንወስዳቸው ነገሮች አሉ።ግን ደግሞ የማይጠቅመንና ባህላችንን የሚበርዝብንን ነገር ልናስወግደው ነው የሚገባው።

ይህንን አጓጉል የሆነና በስልጣኔ ሰበብ የገባብንን ጎጂ አስተሳሰብ በመከላከልና በማስወገድ ረገድ ቤተ-እምነቶች ኃፊነታችንን ስለመወጣችን በየራሳችን ቤት መፈተሽ ይገባናል።በእኔ እምነት ግን ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል።ወጣቱ ልዩና ትኩስ ኃይል ነው፤ የነገርነውን ለማዳመጥም ሆነ ለመተግበር ዝግጁ ነው።በያዘው ንፁህ አዕምሮ ላይ ንፁህ ነገር እንዲይዝ ማድረግ ከሃይማኖት አባቶች ትልቅ የቤት ሥራ አለብን።በጥቅሉ ቤተእምነቶቹ እስካሁን የተወጡት አለ፤ ነገር ግን ብዙ ነገር ይቀራል።መሥራት ይጠበቅብናል።ብንሠራ ውጤቱን እናየዋለን።አሁን የምናየው ክፍተት ባልሠራንበት አቅጣጫ ነው።በመሆኑም ሁላችንም ወደየራሳችን ቤት ተመልሰን ትውልዱን እየቀረፅንበት ያለበትን መንገድ በአግባቡ መቃኘት ይገባናል የሚል እምነት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በመንግሥታዊ ተቋማት ላይ የሚታዩት ሙሰኝነት፤ ዘረኝነትና ፅንፈኛ ፖለቲከኝነት ችግር በእምነት ተቋማትም በስፋት እየተስተዋለ ይገኛል፤ ይህ ከምን የመነጨ ነው ብለው ያምናሉ?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** ያነሳሻቸው ጉዳዮች በሙሉ ከአስተዳደራዊ ችግር የመነጨ ነው የሚል እምነት ነው ያለኝ።ግን ደግሞ ይህ አስተዳደራዊ ችግር ከእምነቶች ብቻ የመነጨ ነው ብዬ እኔ አልወስደውም።ይህ ጉዳይ ዓለም አቀፍ ችግር ነው።በተለይ በአገራችን የምናየው ችግር የተፈጠረው ከአገሪቱ የፖለቲካ ስሪት አኳያ ይመስለኛል።በእርግጥ ይህ ችግር በእምነት ተቋማቱ አለ፤ የለም የሚለውን ጉዳይ ለመተንተን አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱ ደግሞ እይታችንን ይለያያል፤ ግን ደግሞ በጅምላ መፈረጁም ይከብዳል።በዚያ ውስጥ ወገባቸውን ታጥቀው ስለአገርም፤ ስለቤተክርስቲያንም የቆሙ አባቶች አሉና ነው።በደምሳሳው ችግር የለም አይባልም፤ በአስተዳደር ውስጥ ሰው ነው የሚሠራው፤ ልዩ ፍጡር ወይም መልዓክ አይደለም።እንደሰውኛ ስህተቶች አሉ።ጫፍ የወጡ ነገሮችም ይታያሉ።

ነገር ግን ሁሉም ነው ወይ ያንን የሚያደርገው? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ በዚያ ውስጥ ከኃላፊነታቸውና ከተሰጣቸው ተልዕኮ በላይ የሚሠሩ አባቶች አሉ።ሕይወታቸውን፤ ጊዜያቸውን ሰውተው የሚሠሩ አባቶች አሉ።በተቃራኒው የሰው ኃይል አስተዳደራችንን ስንመለከት በርካታ ችግሮች አሉበት።በዚያ ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች በፍጥነት ካላስወገድናቸው አገርንም ሆነ የእምነት ተቋማቱን ለትውልድ ማስተላለፍ አይደለም አሁን ላሉት ማቆየት ከፍተኛ ስጋት ነው የሚፈጥረው።ያንን ግን በጅምላ ፈርጀን ሊሆን አይገባም።እንደምናውቀው በቤተክርስቲያናችን በኩል የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች አሉ፤ በአገር ደረጃ የሠራቻቸው ትልልቅ ሥራዎች አሉ፤ በአስተዳደር ዙሪያ ደግሞ ስናይ ጉድለቶች አሉባት።በመሠረቱ ሁሉነገር የተዋጣለት አስተዳደር በዓለም ላይም ቢሆን አይኖርም።የእኛን ልዩ የሚያደርገው በመንፈሳዊ ዓለም የምንተዳደር እንደመሆኑ ቤተክርስቲያን ከዚያ አኳያ የሚጠበቅባትን ያህል መሥራት ይጠበቅባታል።

**አዲስ ዘመን፡- በተጨባጭ ሲሠሩ ይገባቸዋል ከሚሉት ሥራዎች መካከል ቢጠቅሱልን?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** በዋናነት ሊሠራ ይገባል የምለው በሰው ሀብት አስተዳደር ላይ ነው።እዚያ አካባቢ የሚታየውን ችግር መሠረቱን መንቀል ያስፈልጋል።የሰው ሀብት አስተዳደራችን ችግሮች አሉበት ሲባል ከአገልጋዮች ባሻገር ምዕመኑንም ጭምር የምንመራበትና የምናስተዳድርበት መንገድ ማለት ነው።ተቸግሮ የመጣ ሰውን ለሌላ ችግር ከመዳረግ ይልቅ ችግሩን ማስወገድ ነው የሚያስፈልገው።ታሞ የመጣ ሰው የሚያስፈልገው መድኃኒት ነው።ምክንያቱም ህመምተኞች ናቸው መድኃኒት የሚሹት።በዚህ ረገድ ሰፊ ክፍተት የሚታየው በሰው ሀብት አስተዳደራችን ዙሪያ ነው።በእምነቱም ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት ረገድ ጎልቶ የሚታይ ችግር የለብንም።በአስተዳደር ዙሪያ ግን በደንብ ሊሠሩ የሚገባቸው ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ ሥራዎች የሰው ኃይል አስተዳደራችን በመሆኑ መፈተሽ ይጠይቃል።የሚታዩትን ጉድለቶች በተቋም፣ በግልም፣ ቡድንም ሆኖ እንዲስተካከል መስራት ይገባል።ይህንን ክፍተታችንን ካላስወገድነው በስተቀር ሌላ ችግር ሆኖ እንዳይቀጥል ስጋት ስላለኝ በአፋጣኝ ማረም ይገባናል የሚል እሳቤ ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ ሙስና ወይም ሌብነትን በሚመለከት የቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ አስተምህሯችሁ ምን ይመስላሉ፤ ከዚያ አኳያስ የሚታየው ክፍተት ምንድን ነው?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** ሙስና የሚለው ቃል በመንፈሳዊ አስተምህሮ ከባድ የሆነ ትርጓሜ ነው የተሰጠው።ሙስና ወይም ሌብነት የሃጥያት ስር እንደሆነ ነው መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚያስተምረው።ያልተገባ ዓለማዊ ጥቅምን ለማጋበስ የሚደረገውን ጉዞ መጨረሻው ጥፋት እንደሚያመጣብን በግልፅ ይነግረናል።ይህ ጥፋት ደግሞ አንድን አካል ወይም ተቋምን ብቻ ነክቶ አይቆምም።እንግዲህ እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ቃሉ ‹‹ጉቦ የዓይናማዎችን ዓይን ያሳውራል›› ይላል።ይህም ማለት መማለጃ አንድ ሰው ከተቀበለ የእይታ ሳይሆን የልቦና እውር ይሆናል ማለት ነው።ስለዚህ ጉቦ የሰውን ሕይወት ያጠፋል።ተቋምንም ያፈርሳል።እውቀት አላቸው የሚባሉ ሰዎች ልቦናቸው በሌብነት አስተሳሰብ ከተማረከ እውቀታቸው ይጠፋል እንደማለት ነው።በመሠረቱ በሙስና ውስጥ ሦስት የሃጥያት መሠረቶች አሉ፤ አንደኛውና ዋነኛው አፍቅሮ



ንዋይ ነው።በአስተዳደራዊ ሥርዓት ውስጥ የሚያገለግል ማንኛውም አካል የገንዘብ ፍቅር ካለበት ከሰው መስመር ወጥቶ ይወድቃል፤ ተቋሙንም ይዞ ይወድቃል።

በመሠረቱ ይህ ጉዳይ አይደለም ሰው በዲያቢሎስ አማካኝነት ክርስቶስ እንኳን ተፈትኖበታል።በተለይ የሰው ልጆች የአምላካቸውን ትክክለኛ ትዕዛዝና መርሆ ማየትና በየለቱ መተግበር ካልቻሉ ለዚህ የዲያቢሎስ አሳሳች መንገድ መውደቃቸው ወይም መፈተናቸው አይቀርም።በሌላ በኩል ሙስና የጉቦ ሰንሰለቱ ረጅም ነው።ሂደቱም ስውር ነው።ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል እንደእግዚአብሔር ቃል ፍፁም የተወገዘና የሃጥያት ምንጭ ተደርጎ ነው የተገለፀው።እንደአማኝ መማለጃ መቀበልም ሆነ ገንዘብ መውደድ ትልቅ ሃጥያት እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ ምንአልባት በዚህ ስህተት ውስጥ የወደቁ ካሉ በአፋጣኝ መመለስ ይገባቸዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ።በተለይ አገልጋዮች ለሌሎች መልካም ምሳሌ በመሆን መገለጥና በንፅህና መመላለስ ይጠበቅባቸዋል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በተመሳሳይ ማንነት ላይ ያተኮረ አድሏዊ አስተሳሰብም በእምነት ተቋማት ስር መስደዱ ይጠቀሳል፤ ይህስ ያመጣው ችግር ምንድን ነው ይላሉ?**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለን ሁላችንም በክርስቶስ ደም የተዋጀን አንድ ሕዝብ ነን።በጎሳ ወይም በቋንቋ ምክንያት የሚፈጠር ልዩነት ሊኖር አይገባም፤ አገራዊ አንድነታችንንም ልንተው አይገባም።በመሠረቱ ዓለም የታመሰበት አንዱ ችግር ቋንቋ ለሰው ልጆች መግባቢያ ከመሆን ባሻገር ለፖለቲካ ግብዓት እንዲውል መደረጉ ነው።ወደ ክርስርስትናውም ብንመጣ ልንግባባበት የተሰጠን ሀብት ሆኖ ሳለ የልዩነት ምንጭ ሊሆን ባልተገባ ነበር።ያም ቢሆን ቋንቋ መግባቢያ እንጂ የምንፀድቅበት መንገድ አይደለም።በመጽሐፍ ቅዱሳችንም አንድም ቦታ የፅድቅ መገለጫ ተደርጎ አልተገለፀም።ፈጣሪ ቋንቋ ለሐዋርያት የተሰጣቸው ሥራ እንዲሠሩበት፤ ያላመኑትን እንዲያሳምኑ፤ ያልተጠመቀውን እንዲያጠምቁ ፤ በሕዝቡ ባህልና በአካባቢው ሁኔታ ገብተው አስተምረው ዓለምን አንድ እንዲያደርጉ ነው።

እንዳልኩሽ ቋንቋ የተሰጠን ለመግባቢያና ለመገልገያ ቢሆንም አሁን የምናየው ሰዎች በቋንቋ ምክንያት የሚገደሉበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።ይሄ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው።እንደአገር ትልቅ ፈተና ነው።አሁን በአገራችን የምንመለከተው ነገር በቋንቋ በጎሳ ባሻገር ወደ ጎጥ ድረስ ወርዶ መንፈሳዊ ተልዕኳችንን እንድንስት አድርጎናል።ይሄ ለአገርም ሆነ ለቤተክርስቲያን አደጋ ነው እየፈጠረ ያለው።ፅንፈኛ ብሔርተኝነት አገር ያፈርሳል።ይሔ በሽታ ደግሞ ማንም አይመርጥም፤ ገዳይ ስለሆነ፤ ትውልድ የሚያጠፋ፤ አገር የሚያፈርስ ስለሆነ ከወዲሁ ይህንን የልዩነት አስተሳሰብ ልናስወግደው ይገባል።በዚህ ረገድ እንደቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ቢሆን አዘውትራ የምትሰብከውና የምታስተምረው ልዩነት በክርስቶስ አለመኖሩን ነው።ደሃ ሆነ ሃብታም፤ ሐጥዕ ሆነ ፃድቅ ሁሉም በክርስቶስ አንድ ማህበር ሆነዋል።ከዚህ የወጣው ግን የክርስቶስም ሊሆን አይችልም።በመሆኑም ቤክርስቲያንም ሆነ መንግሥት በቁርጠኝነት ትውልዱን ካልመከርን ካላስተማርን አደጋው የከፋ ነው የሚሆነው።እንደእምነት ተቋም ይህ ዓይነቱ ነገር መምጣት አይገባውም ነበር፤ ግን ደግሞ ቤተክርስቲያን ከዚህ ፈተና የተሰወረች አለመሆኗን መገንዘብ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ዕድሉን ልስጥዎት?**

**መልዓከ ምህረት አማረ፡-** እንደሚታወቀው መላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ክርስቶስ 40 መዓልት 40 ሌሊት ከምግብም፤ ከመጠጥም ተከልክሎ በፅድቅ አሳልፉ አርአያ ሆኖ እንዳስተማረ ሁሉ እኛም በፆም በጸሎት አሳልፈናል።ከዚሁ ጎን ለጎን በምግባሩም ከክፉ ነገሮች ተጠብቀን ቆይተናል።አሁንም በዓሉን ስናከብር በጭንቅ ውስጥ ያሉትን እያሰብንና እየደገፍን ሊሆን ይገባል።ምክንያቱም ደግሞ አስቀድሜ እንዳልኩሽ ከመልካም ስብዕና ጋር ካልተያያዘ ፆም ብቻውን አያድንም።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደነገረን ፆም ብቻውን ፍሬ ሊሰጠንም ሆነ ሊያድነን አይችልም።ለተራቡትና ለተቸገሩት መድረስ ያስፈልጋል።እናም በዚህ ሃይማኖታዊ መርሆ መሠረት ነው ቤተክርስቲያናችንም ምዕመኖቿን ስታስተምርና ስትመራ የቆየችው፤ ምዕመኑም ይህንኑ ሲተገብር ነው ላለፉት ሁለት ወራት የቆየው።

ከዚሁ ጎን ለጎን በተለይ በሰሞነ ህመማት ሃይማኖቱ በሚያዘው መሠረት ክርስቲያኖች ከፆምና ከጸሎቱ ባሻገር አባቶች የታናናሾችን እግር በማጠብና በስግደትም ክርስቶስ ስለኛ የከፈለውን ዋጋ አስታውሰዋል።ደቀመዛሙርቱ በተጨነቁበት ጊዜ ክርስቶስ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ብሎ እንዳበሰራቸው ሁሉ ዛሬም ብዙ ወገኖቻችን በጭንቅ፤ በችግር ውስጥ በመኖራቸው የተቸገሩበትን ነገር በማገዝ ሰላማቸው እንዲመለስ መሥራት አለብን።የታመሙትን ልንጠይቅና ልንረዳቸው ይገባናል።በመጨረሻም በግሌም ሆነ እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሰላም፤ የበረከት እንዲሆንላችሁ ምኞቴን መግለፅ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡-ስለሰጡን ማብራሪያ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**መልአከ ምህረት አማረ፡-** እኔ በዚህ የትንሳኤ በዓል መልዕክቴን እንዳስተላልፍ ዕድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ጤናማ ግብር ጤናማ ላልሆኑ ምርቶች

**አስናቀ ፀጋዬ**

በኢትዮጵያ ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ ለመጣው ተላላፊ ያልሆነ በሽታ ትምባሆ ማጨስ፣ አልኮል መጠጣት፣ የስኳር መጠናቸው ከፍተኛ የሆኑ ምግቦችንና መጠጦችን መጠቀም እንዲሁም ትራንስ ፋት ያላቸውን ምግቦች አዘውትሮ መመገብ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል።ይህንኑ ታሳቢ በማድረግና ኅብረተሰቡን ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ለመጠበቅ ታዲያ በጤና ላይ ጉዳት በሚያመጡ ምርቶች ላይ የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ፀድቆ ሲሠራበት ቆይቷል።

ይህ ታክስ ጤናማ ባልሆኑ ምርቶች ላይ ሲጣል፤ የችርቻሮ ዋጋን በመጨመር የተጠቃሚ ሰዎችን የመግዛት አቅም በማዳከም የፍጆታ መጠናቸውን እንዲቀንሱ ወይም እንዲያቋርጡ ወይም አማራጭ ጤናማ ምርቶችን እንዲጠቀሙ አበረታቷል።ተላላፊ ላልሆኑ ሕመሞች ተጋላጭነትንም ቀንሷል።ከዚህ ባለፈ ከታክሱ ሀገር ገቢ እንድታገኝ አግዟል።በጤናው ሥርዓት ላይም የሚደርስውን ጫና በመቀነስ ረገድ የበኩሉን አስተዋፅዖ አበርክቷል።

ይሁንና ይኸው አዋጅ አሁን ለምክር ቤት ከተላከው ረቂቅ አዋጅ ጋር ሲነፃፀር በተለይ ኅብረተሰቡን ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ከመጠበቅ አንፃር ጠቀሜታው ዝቅተኛ መሆኑ ተነግሯል።ኤክሳይስ ታክሱ በነዚህ ምርቶች ላይ የሚጥለው የግብር መጠንም ከወቅቱ የገበያ ሁኔታና የሰው የመግዛት አቅም ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ ኅብረተሰቡ እነዚህን ምርቶችን እንዳይጠቀም የሚከለክል እንዳልሆነም ተገልጿል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም የሚጣለው ግብር ጤናማ ያልሆኑ ምርቶችን ዋጋ በግሽበትና በኢኮኖሚ እድገት በሚመጣ ተጽዕኖ ውጤታማ እንዳይሆኑ የማያስችል መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት የጤና ልማትና ፀረ ወባ ማኅበር ጤናማ ያልሆኑ ምርቶች በኅብረተሰቡ ጤና ላይ አሉታዊ ጉዳት እንዳያመጡ በሚያደርግ መጠን የራሱን የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦች አስቀምጧል።

ለአብነትም የሲጋራ ምርቶችን በሚመለከት ማኅበሩ የገንዘብ ሚኒስቴር በሲጋራ ምርቶች ላይ ያቀረበው ረቂቅ የኤክሳይስ ግብር በ2012 ዓ.ም ከወጣው ምንም ሳይለወጥ መቅረቡን ታዝቧል።ማለትም አድ-ቫሎረም 30 ከመቶ እና 20 ሲጋራ በሚይዝ ፓኮ ላይ ቁርጥ ግብር (specific rate) 8 ብር ብቻ መሆኑን አይቷል።ይህ የግብር መጠን በ2013 በሰዎች የሲጋራ ፍጆታ ላይ ያመጣው ውጤት አበረታች የነበረ ቢሆንም ከዚያ ወዲህ ባሉት ዓመታት ያስከተላቸው ውጤቶች በግሽበትና በህብረተሰቡ የመግዛት አቅም መጠንከር የተነሳ እየቀነሰ መጥቷል።

ስለዚህም በጤና ላይ አዎንታዊ የሆነ ውጤት ለማምጣት በረቂቅ አዋጁ ላይ አድ ቫሎረም 30% እና በተጨማሪ 20 ሲጋራ በሚይዝ በእያንዳንዱ ፓኮ ላይ በር 25 ነጥብ 00 ቁርጥ ግብር መጣል እንዳለበት ማኅበሩ ጠቁሟል። ይህ ግብር ከተጣለ የአጫሾችን የሲጋራ ፍጆታ በ 12 ከመቶ የሚቀንስ ሲሆን በትምባሆ ምክንያት ሊመጣ የሚችል የሞት መጠንን በ38 ሺ ሊቀንስ እንደሚችልም ግምቱን አስቀምጧል።በገቢ ረገድ ለመንግስት ተጨማሪ ብር 292 ሚሊዮን እንደሚያስገኝና ይህም መንግስት በ2014 ዓ.ም ከትምባሆ ምርት ካስገባው የግብር ገቢ በ67 ከመቶ የበለጠ እንደሚሆን ተጠቅሷል።

ይህ በዋነኛ አማራጭነት የቀረበው የግብር መጠን ካልተሳካ ማኅበሩ እንደ ሁለተኛ የፖሊሲ አማራጭ ያቀረበው በጤናው ላይ ለውጥ ለማምጣትና አገሪቱ እንደግብ የያዘቻቸውን ለማሳካት በአድ ቫለሮም 30 ከመቶ ላይ 20 ሲጋራ በሚይዘው እያንዳንዱ ፓኮ ላይ የቁርጥ ግብር ከብር 20 ያነሰ ቁርጥ ግበር መጣል እንደሌለበት ነው።

በአልኮል መጠጦች የሚጣለው ግብር መጠኑን የአልኮል ይዘቱን ታሳቢ ያደረገ ነው። በዚሁ መነሻነት ማህበሩ ለቢራ 300 ሚ.ሊ ይዘት ባለው በእያንዳንዱ የቢራ ጠርሙስ ላይ አድ-ቫለሮም 40 ከመቶ ሲደመር ቁርጥ ግብር ብር 25 ብር፤ ለወይን መጠጥ አድ-ቫለሮም 40 ከመቶ ሲደመር በአንድ ሊትር ብር 200 ብር፤ ጠንከር ላሉ የአልኮል መጠጦች (spiritis) በአንድ አድ ቫለሮም 80 ከመቶ ሲደመር ቁርጥ ግብር ብር 400 ብር ቢጣል በጤና ላይ የሚያበረክተው አዎንታዊ ውጤት

**ትምባሆ፣ ጣፋጭነት ያላቸው ምግቦች /ስኳር ያላቸው/፣ ለስላሳ መጠጦችና ትራንስ ፋት የምግብ ምርቶች በጤና ላይ ቀጥተኛ ጉዳት አላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበረሰቡን በተዘዋዋሪ ይጎዳሉ። ከዚህ አኳያ ይህንን ለመቀነስና ለመከላከል እንዲቻል በነዚህ ላይ የተለያዩ ምጣኔ ያላቸው ታክስ ተቀምጧል። ይሁንና ቀደም ሲል የነበረው የሕግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ሲደረግ በነዚህ ምርቶች ላይ የሚጣለው ታክስ ውጤት ማምጣት እንደጀመረ በጥናት ማረጋገጥ ተችሏል። በሂደት ግን አሁን የመጣው የታክስ ማሻሻያ አዋጅ ያንን የሚያስቀጥል እንዳልሆነ ታውቋል**

የተሻለ ይሆናል ብሎ አስቀምጧል።

ከላይ የተጠቀሱት የግብር ድምሮች በጥቅሉ በእውነተኛ (real) ዋጋ ላይ 7 እስከ 9 ከመቶ ጭማሪ ሲያስከትል፤ የተጠቃሚዎችን ፍጆታ ደግሞ ከ9 ነጥብ 7 ከመቶ እስከ 5 ነጥብ 7 ከመቶ እንደሚያስከትሉም ገምቷል።

ከላይ የተጠቀሰው ቀዳሚ አማራጭ ተቀባይነት ካጣ ደግሞ በቢራ ምርት ማለትም 300 ሚሊ ሊትር ይዘት ባለው በእያንዳንዱ ጠርሙስ ቢራ ላይ አድ-ቫለሮም 40 ከመቶ በኤክስ ፋካተሪ ዋጋ ሲደመር ቁርጥ ግብር ብር 15 ብር እንዲሆን፣ ለወይን መጠጥ አድ-ቫለሮም 40 ከመቶ ሲደመር በአንድ ሊትር ብር 120 እንዲሆን ጠንከር ላሉ የአልኮል መጠጦች (spiritis) በአንድ አድ-ቫለሮም 80 ከመቶ ሲደመር ቁርጥ ግብር ብር 200 ቢጣል በጤና ላይ የሚያበረክተው አዎንታዊ ውጤት የተሻለ እንደሚሆን አስቀምጧል።ከላይ የተጠቀሱት የግብር ድምሮች በጥቅሉ በእውነተኛ ዋጋ ላይ ከ1 እስከ 8 ከመቶ ጭማሪ ሲያስከትል፤ በተጠቃሚዎች ፍጆታ ላይ ከ3 ነጥብ 8 ከመቶ እስከ 0 ነጥብ 6 ከመቶ ቅናሽ እንደሚያስከትል ገምቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስኳርና የጣፋጡ መጠጦች ላይ የሚጣለው ግብር በመጠንና (volume) በስኳር ይዘት መጠናቸው መሠረት እንዲሆን ይመከራል።በዚሁ መሠረት ማኅበሩ በ2012 ዓ.ም የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት ስኳር ወይም ጣፋጭ የሌላቸው የውሀ ምርቶች አድ-ቫሎረም 10 ከመቶ፤ የስኳር ወይም ማጣፈጫ ቅመም ባላቸው ለስለሳ መጠጦች ላይ አድ-ቫሎረም 25 ከመቶ ግብር እንዲጣል እንደሚጠቅስ ጠቁሟል።

በጤና ላይ በጎ አስተዋጽኦ እንዲያመጣ ከተፈለገ ግን መጣል ያለበት ቀዳሚ ተመራጭ የፖሊሲ ግብር በሂደት ሊከሰት በሚችለውን ግሽበትና በሰዎች የመግዛት አቅም መጠንከር የማይሸረሽር መሆን እንዳለበት አስታውቋል።በዚሁ መሠረትም በለስላሳ መጠጦች ላይ የሚጣለው ቀዳሚ ተመራጭ ግብር ብር 6 በሊትር እንዲሆን የሚመከር መሆኑንና ይህም የሚተገበረው የስኳር ይዘታቸው በ100 ሚሊ ሊትር ውስጥ ከ4 ግራም የበለጠ ስኳር ባላቸው መጠጦች ላይ መሆኑን ጠቁሟል።

ይህ ታክስ ሥራ ላይ ከዋለ በእውነተኛው ዋጋ ላይ ከ4 ነጥብ 9 እስከ 10 ነጥብ 8 ከመቶ ጭማሪ ሲያስከትል፤ የፍጆታ መጠንን ከ13 ከመቶ እስከ 6 ከመቶ ባለው መጠን እንደሚቀንስ አመልክቷል። ከላይ እንደዋና የፖሊሲ አማራጭ ማኅበሩ ከተጠቀሰው ሌላ አድ-ቫሎረም 25 ሲደመር ብር 3 በሊትር ቢጣል በእውነተኛ ዋጋ ላይ ከ2 ነጥብ 2 እስከ 5 ነጥብ 2 ከመቶ ጭማሪ ሲያስከትል፤ በፍጆታ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ ከ6 ከመቶ እስከ 3 ከመቶ እንደሚገመትም በሁለተኛ አማራጭነት አስቀምጧል።

ትራንስ ፋትን በሚመለከት ደግሞ በኢንዱስትሪ በከፊል የሚመረት የትራንስ ፋት መጠን በሁሉም ምግቦች በ100 ግራም ውስጥ ከሚገኝ የጠቅላላ ስብ ምርቶች ላይ ወይም በሀገር ውስጥ በሚመረት ወይም በከፊል ሃይድሮጅን ተጨምሮባቸው የሚመረቱ ዘይቶች ላይ አስገዳጅ የሆነ የ2 ግራም ገደብ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ መውጣት እንዳለበት አስቀምጧል።

አቶ ደምዝ አማን በኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የሕግ ባለሙያ ናቸው።እርሳቸው እንደሚሉት የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186 በ2012 ዓ.ም የወጣ የሕግ ማዕቀፍ ሲሆን በውስጡ ጤናን በሚጎዱ የተለያዩ ምርቶች ላይ ከመጠኑ ጀምሮ ኤክሳይስ ታክስ ይጥላል።የአዋጁ ዋነኛ ዓላማ አንደኛው በኅብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት በሚያደርሱና የማኅበረሰብ ችግር በሚፈጥሩ ምርቶች ላይ ታክስ መጣል ነው።ይህም የምርቶቹ ዋጋ ሲጨምር ተጠቃሚነቱ እንዲቀንስ ማድረግ ማለት ነው።

ሁለተኛው ደግሞ የምርቶቹ ተጠቃሚነት የማይቀነስ እንኳን ቢሆን መንግሥት በነዚህ ጤናን በሚጎዱ ምርቶች ምክንያት የሚመጣውን ጉዳት ለማከም የሚያወጣውን ወጪ በምርቶቹ በሚወጣው ወጪ ምርቶቹ ላይ ታክስ በመጣል ከታክሱ በሚገኘው ገቢ መሸፈን ነው። ይህም የምርቱ ገዢዎች በሚያወጡት ወጪ የሚመጣውን ጉዳት በራሳቸው እንዲያፀዱት ማድረግ ነው።

አልኮል፣ ትምባሆ፣ ጣፋጭነት ያላቸው ምግቦች /ስኳር ያላቸው/፣ ለስላሳ መጠጦችና ትራንስ ፋት የምግብ ምርቶች በጤና ላይ ቀጥተኛ ጉዳት አላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበረሰቡን በተዘዋዋሪ ይጎዳሉ። ከዚህ አኳያ ይህንን ለመቀነስና ለመከላከል እንዲቻል በነዚህ ላይ የተለያዩ ምጣኔ ያላቸው ታክስ ተቀምጧል። ይሁንና ቀደም ሲል የነበረው የሕግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ሲደረግ በነዚህ ምርቶች ላይ የሚጣለው ታክስ ውጤት ማምጣት እንደጀመረ በጥናት ማረጋገጥ ተችሏል። በሂደት ግን አሁን የመጣው የታክስ ማሻሻያ አዋጅ ያንን የሚያስቀጥል እንዳልሆነ ታውቋል።

ይህ የተባለበትም ምክንያት አዋጅ ቁጥር 1186/2012 በምርቶቹ ላይ የነበረው ተፅዕኖ ወይም ውጤት የዋጋ ግሽበትንና የገንዘብ መግዛት አቅም መዳከምን ተከትሎ ሊቀንስ በመቻሉ ነው። ከዚህ አኳያ ቀደም ሲል የነበረው ውጤትና ተፅዕኖ እየቀነሰ በመጣ ቁጥር በምርቶቹ ላይ የሚጣለው የታክስ መጠን የበለጠ መሻሻል ሲገባው ጭራሽ ሲቀንስ ተስተውሏል።ባለበት መጠን እንዲቀጥሉ የተደረጉ የታክስ መጠኖችም አሉ። የታክስ መጠናቸው እንዲቀንስ ብሎም እንዲወጡ የተደረጉም ምርቶች አሉ። ይህም የኤክሳይስ ታክስ ከሚጣልበት ዓላማ አንፃር የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት የሚችል እንዳልሆነ ተረጋግጧል።

እንደ ሕግ ባለሞያው ገለፃ የኤክሳይስ ታክስ አንዱ ዓላማ የኅብረተሰቡን ጤና የሚጎዱና ማህበረሰባዊ ችግር የሚፈጥሩ ምርቶች ፍጆታቸው እንዲቀንስና ፍጆታቸው እንኳን ባይቀንስ በዚያ ምክንያት የሚመጣውን ችግር ወይም የጤና እክል ራሱ ምርቱን የሚጠቀመው ሰው ወይም የሚያመርተው አካል ወጪውን እንዲችል ለማድረግ ነው። ከዚህ አንፃር አሁን የተቀመጠው የታክስ መጠን ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም አንፃር መሻሻል አለበት። ያንን ዓላማ ሊያሳካ የሚችል የታክስ መጠንም መቀመጥ ይኖርበታል።

ይህ ብቻ ሳይሆን አዲሱ ረቂቅ አዋጅ በበፊቱ አዋጅ ያልነበሩ አዲስ ይዟቸው የመጡ ጤናን የሚጎዱ ምርቶች ለምሳሌ የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ፣ የሺሻ ፓይፕና ሚጨስ ትምባሆ ተብሎ ምትክ የሚመስል ምርቶች በመኖራቸው መካተት የለባቸውም።በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ቀደም የተቀነሱ መጠኖች አሉ።ለምሳሌ ስኳር ከ20 በመቶ ወደ 10 ከመቶ ዝቅ እንዲል ተደርጓል።እነ ቼኮሌት፣ ከረሜላዎችና የጣፋጭ ይዘት ያላቸው የምግብ ምርቶች ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ዋነኛ መንስኤ በመሆናቸው ፍጆታቸው እንዲቀንስ መደረግ ይኖርበታል አልያ ደግሞ ተጠቃሚው በነዚህ ምርቶች ፍጆታ ምክንያት የሚወጣውን የሕክምና ወጪ መሸፈን ይጠበቅበታል። እነዚህም ነገሮች በአዋጁ የተቀነሱ በመሆናቸው አሁን ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም አንፃር የታክስ መጠኑ መስተካከል አለበት።

ሳቹሬትድ ፋትን በተመለከተም ተፈፃሚ ለማድረግ ችግር በመፍጠሩ ከአዋጁ ለጊዜው መውጣት ይኖርበታል። በዚህም ሳቹሬትድ ምግቦች ላይ ተጥሎ የነበረው ኤክሳይስ ታክስ ከአዋጁ እንዲወጣ ተደርጓል። ነገር ግን ይህ ዳግም መመለስ ይኖርበታል። ምክንያቱም እንዲህ አይነት ምግቦችን ለማስመዝገብ የሕጉ ማዕቀፍ በራሱ ስልቶችን አስቀምጧል።አንደኛው ስልት አንድ ምርት በውስጡ ምን ያህል ሳቹሬትድ ፋት ወይም ትራንስ ፋት አለው የሚለውን በተመለከተ በምርቱ ገላጭ ጽሑፍ ላይ ማስቀመጥ ነው።ለምሳሌ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራምና ከዛ በላይ ሳቹሬትድ ፋት ካለው መታሸግ እንዳለበት አስቀምጧል።ይህም በምርቱ ገላጭ ጽሑፍ ላይ ነው የሚገኘው። ስለዚህ ያንን ገላጭ ጽሑፍ መሠረት አድርጎ ማስፈፀም ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በምርቱ ላይ ገላጭ ጽሑፍ ከሌለ የሕጉ ማዕቀፍ ምርቱ ከ40 ከመቶ በላይ ሳቹሬትድ ፋት እንዳለው ግምት ተወስዶ ታክሱ ተፈፃሚ እንደሚሆን አስቀምጧል። ምን አልባት ለማስፈፀም አስቸጋሪ የሚሆነው ምርቱ ከ40 ከመቶ በላይ ሳቹሬትድ ፋት ይኑረው አይኑረው ማረጋገጡ ነው።ያም ሆኖ ግን ምርቱን የሚያመጣው ወይም የሚያመርተው አካል እንዲያስመረምር ማድረግ ይቻላል። ከዚህ አንፃር ለማስፈፀም አይቻልም የተባለበት አግባብ ምክንያታዊ አይደለም። ምክንያቱም ይህን የማስፈፀም ሥልጣን ያለው ታክስ ሰብሳቢው አካል በመሆኑ ነው።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "የፋሲካ ልጆች አሳዛኝ ፍጻሜ"

**የመንደርደሪያችን መደላድል፤**

በዚህ ሳምንት ውስጥ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በጾምና በፀሎት ሲታወሱ የሰነበቱት ቀናት ሰሙነ ሕማማት በመባል ሲጠሩ የዛሬው ዕለትም ቀዳሚት/ቅዳም ሥዑር (በተለምዶ ቅዳሜ ሹር ወይንም የተሻረው ቅዳሜ) ተብሎ ተለይቷል። በነገው ዕለተ ፋሲካም "ጌታችን ተመረመረ ዲያቢሎስ ተወገረ፤ የምሥራች ቄጤማ ተቀበሉ" በሚሉ ካህናት የመልካም ምኞት መግለጫ ክርስቶስ ሞትን ድል የነሳበት የትንሣኤው ብሥራት ይበሰራል። የክርስትና እምነት ዋና መልሕቅ የሆነው ይህ በዓል በእምነቱ ቤተሰቦች ዘንድ እጅግ ላቅ ያለ መንፈሳዊ ትርጉምና ከበሬታ ያለው ነው። እንኳን ለበዓለ ፋሲካ በሰላም አደረሰን።

ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመዝለቃችን አስቀድሞ መብራራት የሚገባቸውን አንዳንድ አጠቃላይ ሃሳቦችን አፍታትተን እንለፍ። እግዚአብሔር አምላክ ከሰኞ እስከ ዐርብ ፍጥረታትን በሙሉ እና ክቡሩን የሰው ልጅ በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረ በኋላ ያረፈበት ዕለት ቅዳሜ እንደሆነ ይታመናል። ቅዱስ መጽሐፍ ታሪኩን እንደሚከተለው ያብራራዋል፤ "ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ። በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፏልና" (ዘፍጥረት 2፡1-3)። የቅዳሜ ዕለት ታላቁ ሰንበት (ሰንበት ዐቢይ) በመባልም ይታወቃል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር አርፎ የዋለበት ዕለት በመሆኑም በልዩ ሁኔታ ይዘከራል።

ስለ ፋሲካ ጥንተ አመጣጥ ጥቂት እናስታውስ። ፋሲካ እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበት ዕለት ነው። የአወጣጣቸው ታሪክም እንደሚከተለው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተተርኳል። "እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በግብፅ ምድር በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ከፈርዖን የበኩር ልጅ ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኩር ድረስ በግብፅ ምድር የተገኘውን በኩር ሁሉ፣ የእንስሳቱንም በኩሮች ሁሉ ቀሰፋቸው። ፈርዖንም ባሪያዎቹም ሁሉ ግብፃውያንም ሁሉ በሌሊት ተነሡ፤ የሞተ የሌለበት ቤት አልነበረምና በግብፅ ምድር ታላቅ ለቅሶ ሆነ። ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት ጠርቶ፡- እናንተ የእስራኤልም ልጆች ተነሡ ከሕዝቤ መካከል ውጡ፤ ሂዱም አላቸው፤፡"

"በእስራኤላውያን ቤት ግን የሞት መቅሰፍቱ በሚያልፍበት ጊዜ የቤታቸው ጉበንና መቃን የጠቦት ደም ተቀብቶ ስለነበር ቀሳፊው ሞት ወደ ቤታቸው ዘልቆ በመግባት እንዳይገድላቸው ተከልክሎ ነበር"። እስራኤላውያን ከ430 ዓመታት የባርነት ሕይወት ነፃ ወጥተው ማርና ወተት ታፈሳለች ወደ ተባለችው የተስፋ ምድራቸው ወደ ከንዓን ጉዞ የጀመሩት በዚያ ታሪካዊ አስደንጋጭ ምሽትና ከዚያ ቀናት ቀደም ብሎ በተፈጸሙ በአጠቃላይ አሥር በሚያህሉ እጅግ ዘግናኝ ተዓምራት ደንዳናው የፈርዖን ልብ ከተሰባበረ በኋላ ነበር። እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ ለመውጣት ጉዞ የጀመሩበት ዕለትን በተመለከተ በአንዳንድ የሥነ መለኮት ማብራሪያዎች ውስጥ ዘመኑ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በግምት ከ1500 ዓ.ም ገደማ በፊት እንደነበረ ይገመታል። የዘመኑ ስሌት ዛሬም ድረስ በብዙ የዘርፉ ተመራማሪዎች ዘንድ ወደ ጋራ መግባባት አልተደረሰበትም።

ይህ የአይሁዳዊያን የፋሲካ በዓል (Pesach) በአንድ ወቅት ብቻ ተከብሮ የሚያበቃ ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ጭምር መለኮታዊ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል። "እግዚአብሔር በኃያል ክንዱ ከግብፅ ምድር አውጥቷችኋልና ይህንን ሥርዓት በተወሰነው ጊዜ በየዓመቱ ጠብቁት/ አክብሩት።" በዚህም አምልካዊ ትዕዛዝ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁድ እምነት እንደ አንድ ዐቢይ በዓል ተደርጎ በዝርዝር የተደነገጉ ሥርዓቶች ሳይጓደሉ መከበሩን ቀጥሏል። በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ዘንድ ግን "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶልናል" (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡7) ተብሎ በተጻፈው መሠረት የፋሲካ ማዕከላዊ ትኩረት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች የኃጢአት ሥርየት ደሙን ያፈሰሰበት፣ የሞተበት፣ የተቀበረበትና በትንሣኤው ሞትን ድል ነስቶ ታላቅ የማዳን ተግባር የፈጸመበት ፍቅሩ እየታወሰ በዓሉ በየዓመቱ በታላቅ መንፈሳዊ ድባብና ድምቀት ይከበራል።

**ተስፋቸውን ያመከኑ —የፋሲካ ልጆች"፤**

በአንዳንድ የሥነ መለኮት ምሑራን የፋሲካ ልጆች (Children of Passover) በሚል ቅጽል የሚጠሩት እስራኤላውያን የግብፃውያንን የባርነት ቀንበር ሰባብረው ነፃ እንዲወጡ ምክንያት የሆናቸው ዋናው ጀግና መሪያቸው ሙሴ ነበር። "ማርና ወተት" ወደምታፈሰው የተስፋ ምድራቸው ለመድረስ 40 ዓመታት በፈጀ የምድረ በዳ ጉዞ የተፈተኑት እስራኤላውያን ተግዳሮታቸው ምድረ በዳው ብቻ ሳይሆን ከሠላሳ በላይ በሆኑ ነገሥታት በርካታ ጦርነቶች ተከፍቶባቸውም እያሸነፉ ጭምር ነበር ሲጓዙ የነበረው።

ሕዝቡ በምድረ በዳው ጉዞ ሲዝልና በጦርነቱ ብዛት ሲመረር፣ ከተጓዦች መካከል በሚያፈነግጡ አመፀኞችና አድመኞች ሕዝቡ ሲታመስ፣ ፈተናው ተደራርቦ ሲያይሉና ሲጨነቁም "ስለምን እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር እንድንወጣ ፈቀደ" እያሉ ግራ ሲያጋቡት- "እባክህ አምላኬ ሆይ ይህንን ሕዝብ ተቆጥተህ ከምታጠፋና ቅዱስ ስምህ ከሚሰደብ እኔን ሙሴን ቀድመህ ግደለኝ" በማለት ራሱን ለሕዝቡ የኃጢያት ማስተሰርያ መስዋዕት አድርጎ ማቅረቡንም የሙሴ ግለ ታሪክ በግላጭ ይነግረናል።

"እግዚአብሔር ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር" የተባለለት ሙሴ፣ ራሱ እግዚአብሔርም፡- "ከባሪያዬ ከሙሴ ጋር እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እነጋገራለሁ፤ በምሳሌም አይደለም" (ዘኁልቁ 12፡6 - 8) ተብሎ የተመሰከረለት እና "በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበር" (ዘኁልቁ 12፡2) የሚል አድናቆት የተቸረው ሙሴ ፍጻሜው ያማረ አልነበረም። ያ ታላቅ የሕዝበ እስራኤል አባት፣ የጦር መሪ፣ ነብይ፣ የምሕረት አማላጅ፣ አስተማሪ፣ ሕግ ተርጓሚ፣ ፈራጅ ዳኛና የጥበብ መጋቢው "የፋሲካ ልጆች" አለቃው ሙሴ ታሪኩ የተጠናቀቀው በዕልልታና በሆታ በታጀበ ድል ሳይሆን በኀዘን ነበር።

"አይዟችሁ ወደ ተስፋችን ሀገር እየደረስን ነው፤ እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ርስት በድል አድራጊነት እንወርሳለን" እያለ ሕዝቡን እያጀገነ እንዳልመራ ሁሉ በአንድ ቅጽበታዊ ስህተት ምክንያት የተስፋው ምድር ዳርቻ ላይ ከደረሰ በኋላ እግሩ ምድሩን እንደማይረግጥ የሚከተለው መለኮታዊ ትዕዛዝ ወጣበት፡- "እግዚአብሔርም ሙሴም አለው፡- ለዘርህ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማልሁላቸው ምድር ትታይሃለች ያቻትልህ፤ በዐይንህ እንድታያት አደረግሁ፤ ነገር ግን ወደዚያች አትሻገርም አለው" (ዘዳግም 34፡4)። እጅግ ያሳዝናል።

የጓጓለትን ምድር በዐይኑ ብቻ አይቶ "አትገባበትም" የተባለው ሙሴ፡- "በምድረበዳ ሞተ፤ መቃብሩም የት እንደሆነ እንኳን እስከ ዛሬ ማንም አያውቅም" (ዘዳግም 34፡6)። የዚህ ሁሉ አሳዛኝ ፍጻሜ መንስዔው ትሑቱ ሙሴ በአንድ አጋጣሚ የእግዚአብሔርን ሥራ ለራሱና ለአሮን በመስጠት "ከዚህ ድንጋይ ውሃ አወጣንላችሁ" በማለቱ ለፈጣሪ ይገባ የነበረውን ክብር ለራሱና ለወንድሙ በመውሰዱና "እኔ ሙሴ!" በማለት ስለታበየ ነበር። እነሆ! የተላለፈበት የፍርድ ቃል እንዲህ ይነበባል፡- "በእስራኤል ልጆች መካከል በጺን ምድረ በዳ በቃዴስ ባለው በመሪባ ውሃ ስለ በደላችሁኝ፣ በእስራኤልም መካከል ስላልቀደሳችሁኝ፣ ምድሪቱን ፊት ለፊት ታያታለህ እንጂ ወደዚያች እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣት ምድር አትገባም።"

ተስፋው መክኖበት በምድረ በዳ ወድቆ የቀረው ሙሴ ብቻ አልነበረም። የሕጻናቱን ቁጥርና ሌሎች እስራኤላውያንን በፈቃዳቸው የተከተሏቸውን ባዕዳን ሳይጨምር ከግብፅ ከወጡት 601,730 ያህል እስራኤላውያን መካከል የተስፋቸውን ምድር የወረሱት ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ። ባለመታዘዛቸውና በአመጻቸው ምክንያት ሁሉም እንደ ትቢያ በንነውና እንደ በጋ ቅጠል ረግፈው የቀሩት በምድረ በዳ ውስጥ ነው። ተስፋቸው እውን ሆኖ የከንዓንን ምድር የወረሱት በምድረ በዳ የተወለዱትና የተዋለዱት ልጆች ብቻ ነበሩ። እንደ ዘርፉ ጠበብት ግምታዊ አኃዝ ከሆነ የተስፋ ሀገራቸው የደረሱት አንድ ሚሊዮን የሚገመቱት "የምድረ በዳ ትውልዶች" ብቻ ናቸው። በድል ጀምሮ በሽንፈት ማጠናቀቅ ይሏል እንዲህ ነው።

**ዘመናን በሙሉ "በሰሙነ ሕማማት ገመምተኛነት" የምናውቃት ኢትዮጵያ፤**

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የሰሙነ ሕማማት ዜና መዋዕል ታሪክ በዓመት አንድ ወቅት ብቻ የሚታሰብ ሳይሆን የእኛ ብቻ ስጦታ ሆኖ እስኪቆጠር ድረስ ሁሌም አብሮን እንደኖረ ነው። ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከሆሳዕና እስከ ቀዳሚት ሥዑር ያሉት ደመናማ ቀናት ኢየሱስ ክርስቶስን ለመያዝ አይሁድ ክፋት የጎነጎኑበት፣ ምክራቸውን በመሐላ ኪዳን በማጽናትም ጻድቁን ጌታ ይዘው የገረፉበት፣ የሾህ አክሊል በመጫን የተሳለቁበት፣ ወደ ቀራኒዮ እያጣደፉ ወስደው በመስቀል ላይ የቸነከሩበት፣ ገድለው የቀበሩበት... ምኑ ተዘርዝሮ ይዘለቃል፤ ብቻ ከሰኞ እስከ ቀዳሚት ሥዑር ባሉት ቀናት በክርስቶስ ጌታ ላይ የግፍ ወጀብ የዘነበበት የሰሙነ ሕመማት ዕለታት ነበሩ። ይህንኑ የመከራ ሣምንታት ለማስታወስ ነው የእኛም "ሀገራዊ አየር" እስከ ዛሬዪቱ ዕለት ድረስ በሃሌሉያ ዝማሬ ሳይሆን በኪርያላይሶ የምሕረት ምልጃና "በኤሎሄ" መቃተት ሕዝበ ክርስቲያኑ ወደ ፈጣሪው እግዚኦ ሲል የሰነበተው።

ለማስታወስ ያህል፡- "የሰሙነ ሕማማት ሀገራዊ ታሪካችንን" በወፍ በረረ ቅኝት መለስ ብለን በመቃኘት ራሳችንን እንፈትሽ። በኢትዮጵያ የረዢም ዘመናት ታሪክ ውስጥ ኪርያላይሶና የኤሎሄ የጣር ጩኸት ሳይደመጥ ያለፉ ሥርዓተ መንግሥታት ይኖሩ ይሆን? በግሌ እርግጠኛ ለመሆን እቸገራለሁ። ከመጻሕፍት ንባብ ይልቅ በሕይወት ያለፍንባቸውንና እየኖርንበት ያለውን ወቅት እንኳን ልብ ብለን ጠልቀን ብንመረምር "የሰሙነ ሕማማት" መከራችን ይህ ልኩ ተብሎ የሚቆጠርም "የሚመዘንም" እንዳልሆነ እንረዳለን።

ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ደርግ የተደረገው ሽግግርና የወታደራዊው መንግሥት አገዛዝ የተጠናቀቀው ሀገሪቱ ከሰሙነ ሕማማት ድንጋጤና ኃዘን ሳትወጣ የኃዘን ጨርቅ በመልበስ እንደተቆራመደች ነበር። በሙሴ የመሰልናቸውና "ፋኖ ተሠማራ! ፋኖ ተሰማራ! እንደነ ሆችሚኒ እንደ ቼኩቬራ" እያለን "ቼ! በለው በማለት የፈከርንላቸው" የወቅቱ ሳይሞቅ ፈላ አብዮታውያን ወጣቶቻችን ታሪካቸውን የደመደሙት በፈርዖን ለሚመሰለው ለጨካኙ የጁንታ መንግሥት አሳልፈው በመስጠት ነበር። ሀገሪቱን በ"ሰሙነ ሕማማት ውስጥ ጥለው" እነርሱም እንደ እስራኤላውያን ልጆች በምድረ በዳ ወድቀው የቀሩት ምክንያት አልባ በሆነ የእርስ በእርስ ፋክክር እየተገዳደሉና በጨካኙ ልበ ደንዳና ወታደራዊ በትር እየረገፉ ጭምር ነበር።

እንኳን ኢትዮጵያን ለመታደግ ቀርቶ ለራሳቸውም ቢሆን "የወረደባቸውን መቅሰፍት" ለመቋቋም አቅምም ሆነ ብቃት አልነበራቸውም። "ሙሴዎቻችን" ብለን ያንቆለጳጰስናቸውም ተስፋ ወደ ገቡልን "የሕልም ዓለም" ሊያሻግሩን ቀርቶ ሀገሪቱ ባለችበት ቆማ ለመርገጥ እንኳን ባለመቻሏ ልጆቿን ለማኖር የተገደደችው ከሲዖል በማይተናነስ ፍዳ ውስጥ እንደተዘፈቁ ነበር።

ከደርግ ወደ ሕወሓት/ኢሕአዴግ፣ ከዚያም ወደ ብልጽግና የተደረጉት የሥርዓተ መንግሥታት ሽግግሮችም በስንት ጉዳዮች ሀገራችንን "ሰሙነ ሕማማት ላይ" እንደጣሏት በዝርዝር ማስታወሱ የትናንታችን ለዛና ወዙ ገና ጠፈፍ ስላላለ እንዲህና እንዲህ ነበር ብሎ መተረኩ እጅግም ላያስፈልግ ይችል ይሆናል። የለውጥ መሪዎቹ "በሙሴ"፣ ያስወገዱት ሥርዓት በፈርዖን፣ ሕዝቡም በእስራኤል ልጆች እየተመሰለ ሲተረክ ቢኖርም የዜጎች ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ ሲያሽቆለቁል እንጂ "በመና" የሚመሰል የሕይወት ለውጥ ማየት አልተቻለም።

"ሙት ወቃሽነቱን" ለጊዜው አቆይተን የዛሬያችንን ውሎ አምሽቶ ብቻ ብንፈትሽ እንኳን "ከሰሙነ ሕማማት" ነፃ ወጥተን ወደ "ትንሣኤ" እየተቃረብን ነው እንዳንል ብዙ ጉዳዮች አፋችንን ያሲዙናል። በተግባር ሲፈጸሙ የምናስተውላቸው፣ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናሸታቸው፣ እያንዳንዳችን ላይ ተፈጽመው ምስክር የሆንባቸው መከራዎቻችን ይህ ልኩ የሚባሉ ዓይነት አይደሉም።

ከሃይማኖት ዶግማ እስከ ፖለቲካ "ኤሎሄያችን" ለጥጠን ለመነካካት የሞከርናቸው ጉዳዮቻችን እንዲህ እንደ ዋዛ በድምድማት የሚቋጩ አይደሉም። ያልተመለሱልን ሀገራዊ ጉዳዮቻችን እጅግ ብዙዎች ናቸው። ከዳቦ ረሃብ እስከ ፖለቲካ ቀውስ የተጫኑብን "የባርነት ቀንበሮች" እንኳን ከጫንቃችን ላይ ሊፈቱ ቀርቶ እንዲያውም ክብደቱ በርትቶብን በማስጎንበስ በእንብርክክ እያስኬደን እንዳለ አፋችንን አፍነን የምንቃትትበት የሲቃ ድምጻችን ምስክር ነው።

እስከ መቼ ኢትዮጵያ የሾህ አክሊል እንደ ደፋች ትኖራለች? እስከ መቼስ ቀራኒዮ ላይ ተቸንክራ "ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ" እንዳለች ውላ ታድራለች? "የንጹሐንን የደም ግብር" የምንከፍልባቸው ሀገራዊ "ትምክህቶቻችን" መቼ ነው የሚለዝቡት? "አቤቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ተዋርደው ኑሯቸው ሰሙነ ሕማማት ከሚሆን ለሰላም ስል እኔ ዝቅ ብዬ እግር እስከማጠብ በመድረስ የክርስቶስን አርአያነት እከተላለሁ" የሚሉ ሙሴዎች መቼ ነው ወደ አደባባይ የሚወጡትና "ወደ ተስፋችን" የሚያፈልሱን? እስከ መቼስ ነው ከሰሙነ ሕማማት ቀጥሎ የሚመጣው ትንሣኤ ርቆብን ተስፋችን እንደመከነ የምንኖረው። ኢትዮጵያ ሆይ የትንሣኤ ጌታ ትንሣኤሽን ያፋጥንልሽ፤ እናም ነገ ትንሣኤ ይሆናል በይን። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ። ሰላም ይሁን!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## አከራካሪው ማሽን



ክፍለዮሐንስ አንበርብር

### የችሎቱ ድባብ

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም የሰነድ መለያ ቁጥር 72189 መዝገብ በችሎቱ ፊት ቀርቦ የመጨረሻ የተባለው የዳኞች ቃል ያርፍበታል። ሰበር በውሳኔው አንዳች የመጨረሻ ቃል ይናገራል። በዚህች ዕለት የመጨረሻ የተባለችውን ቃል ተመካክረው ለመስጠት ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች በሰዓቱ ተገኝተዋል። በወቅቱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ተገኔ ጌታነህን ጨምሮ አምስት ዳኞች ከመንበሩ ተሰይመዋል። ጉዳዩም ከረር ያለ ነው።

አመልካች አቶ ካሳዬ ያደቴ ከጠበቃ ኮሎኔል መላኩ ካሣዬ ጋር ቀርበዋል። ተጠሪ ደግሞ የውጭ ዜጋ ናቸው። ሲኞር ፈራንችስኮ ቬንሲያን ይሰኛሉ። በተጠሪ በኩል ግን ችሎቱ ዘንድ የቀረበ የለም። ሆኖም መዝገቡን መርምሮ ውሳኔውን ከመስጠት ችሎቱን ያገደ አልነበረም። መዝገቡ ተመረመረ፤ የመጨረሻ ብይንም ተሰጠ። ከእንግዲህ ፍርድም የጸና ይሆናል። ምንም እንኳ ሲኞር ፈራንችስኮ ቬንሲያን ከችሎቱ ቀርበው ምን ተባለ ብለው አስተርጓሚያቸውን ባይጠይቁም። ዳኑ ግን ውሳኔው ይደርሳቸዋልና ዛሬ የቁርጥ ቀን የመጨረሻ ውሳኔ ይሰማሉ-ሲኞር ፈራንችስኮ ቬንሲያን። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች በሚል ዋና ርዕስ የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያው ኅዳር 2005 ዓ.ም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች በሚለው ቅፅ ለታሪክና መመሪያ ይሆን ዘንድም ይህንን የችሎት ውሎ ቅፅ 13 ብሎ ሰንዶታል።

### ጉዳዩ ምን ነበር?

መሠረታዊ የመከራከሪያ ጉዳይ የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ነው። ታዲያ የዚህ ማሽን ጉዳይ እስከ ሰበር ችሎት ድረስ የደረሰው እንዲሁ በዋዛ አይደለም። በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር አንቀፅ ምዕራፍ ተጠቅሶ፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤትም ብይን ቢሰጥም ከሁለቱም ወገን ማለትም ከአመልካችም ሆነ ተጠሪ በኩል በፍርድ ሂደቱ የረካ አልነበረም። ጉዳዩም አመልካች ከፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በአደራ የተረከባቸውን የተጠሪ ንብረቶች አልመለሰም በሚል ተጠሪ የንብረቶቹን ዝርዝር እና ግምት በመጥቀስ ባቀረበው ክስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረ ሆኖ አሁን የሚያከራክረው መቆፈሪያ ማሽን በተመለከተ ሲሆን ይሄው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማሽኑ ተገምቶ ፍርድ እንዲሰጥበት በወሰነው መሠረት አመልካች ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመቻሉ ከዚህ ቀደም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አሁንም ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በመወሰኑ እና ይሄው ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጽናቱ የተፈጸመው መሠረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው።

### አመልካች ምን አሉ?

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሏቸውን ነጥቦች በማንሳት ያቀረቡ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፤ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማሽኑ ተገምቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት ወደ ታች ፍርድ ቤት መልሶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይሄንን ሳያከብሩ አሁንም በድጋሚ በብር ውሣኔ መስጠታቸው ተቀባይነት ያለው አካሄድ አይደለም የሚል ነው።

አመልካች በበታች ፍርድ ቤትም ሆነ በተለያዩ አካላት ባቀረበው አቤቱታ ሌሎች ዕቃዎችን እንጂ የመቆፈሪያ ማሽን ያልተረከበ ስለመሆኑ ተከራክሮ እያለ እና ሌሎቹን የተረከባቸውን ደግሞ በብር 8,000 (ስምንት ሺህ ብር) መሸጣቸውን የተከራከሩ በመሆኑ፣ በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረብናቸውም ሰዎች ብረታ ብረት መግዛታቸውን እና መቆፈሪያ ማሽን ያልገዙ ስለመሆኑ እና ይሄንንም የገዙትን እቃ ብር 400(አራት መቶ ብር) በማትረፍ የሸጡ ስለመሆኑ ይናገራሉ። በመሆኑም ተጠሪ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ክሱ ውድቅ መሆን ሲገባው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው ተከራክረዋል።

ጉዳዩ ያስቀርባል በመባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ በእርግጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሌሎቹ እቃዎች ላይ በበታች ፍርድ የተላለፈው ፍርድ አግባብ ስለመሆኑ በማመልከት ያጸናው ሆኖ የዚህ አከራካሪ ማሽን ግን ዓይነቱ ሊታወቅ እና በባለሙያ ያልተገመተ መሆኑ እየታወቀ ይህ ሳይደረግ መታለፉ እና በብር መወሰኑ አግባብነት የሌለው ነው ተብሎ ወደ ታች መመለሱ ግልጽ ቢሆንም አመልካች ማሽኑን የገዛውን ሰው ማቅረብም ሆነ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመቻላቸው፣ ያቀረቡትም ሰው ስለማሽኑ ሲጠየቁ ማሽን እንዳልገዙ ሆኖም ግን ብረታ ብረት ስለመግዛታቸው ብቻ በመግለጻቸው ታልፎ የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ እና ንብረቶቹን ስለመረከቡ ደግሞ ፈርሞ የተረከበበት ሰነድ ስለሌለ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል። አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታቸውን በማጠናከር በራሱ መንገድ ክርክሩን ማቀጣጠሉን ተያያዘው።

### ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ሲመለከት

ግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል። እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን የመቆፈሪያ ማሽን ግምት በተመለከተ ወደ ድምዳሜ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት የተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሆኖ ተገኘ።

በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የመቆፈሪያ ማሽኖቹን በተመለከተ አመልካች አልተረከብኩም የሚል ክርክር በዚህ ደረጃ እያነሳ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል። ሆኖም ግን ኃላፊነትን በተመለከተ ከዚህ በፊት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገ ክርክር እልባት ያገኘ እና የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 50776 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመለስ አሁን የሚያከራክረውን ማሽን ግምት በብር በመወሰን በባለሙያ በማስገመት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚቻል በመሆኑ ይሄው ሥርዓት ሊፈጸም ይገባል በሚል ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል።

በመሆኑም አመልካች የመቆፈሪያ ማሽኑን አልተረከብኩም በማለት ያነሳው ክርክር ቀደም ሲል በውሣኔ በተቋጨ ጉዳይ ላይ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 5/1/ መሠረት ተቀባይነት ያለው አይሆንም። ሆኖም ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት አከራካሪውን ማሽን ለማስገመት ተገቢውን ትጋት አድርጓል ወይ? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል ይላል ፍርድ ቤቱ በምርመራው።

ጉዳዩ ወደታች ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ ፍርድ ቤቱ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ወይም የገዛውን ሰው እንዲያቀርብ የተጠየቀ ሲሆን አመልካችም ማሽኑን እንደቀድሞ ሁሉ እንዳልተረከበ የተከራከረ ሲሆን የገዛውንም ሰው እንዲያቀርብ ታዞ አመልካች ያቀረበው ሰው ማሽን እንዳልገዛ እና ብረታ ብረት እንደገዛ የገዛውንም ብረታ ብረት ብር 400 (አራት መቶ ብር) በማትረፍ እንደሸጠ ገልጿል።

ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤቱም ይሄንኑ ምክንያት በማድረግ ቀድሞ በጥሬ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ተብሎ የተወሰነውን ውሣኔ በድጋሚ በመቀበል ወስኗል። ሆኖም ግን አንድ ጉዳይ በበላይ ፍርድ ቤት በነጥብ ሲመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በመጣራት ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተገቢውን ትጋት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 343/1/ ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል ይላል። ይህ አከራካሪው የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እስከታወቀ ድረስ ፍርድ ቤቱ ዓይነቱን በተመለከተ ከግራ ቀኙ ወይም በመዝገቡ ውስጥ ካሉት ሰነዶች በመመልከት እና በመግለጽ አግባብነት ባለው ባለሙያ እንዲገመት በማድረግ ቢያንስ በብር ለሚሰጠውም ውሣኔ መነሻ ነገር ማስቀረብ እየተቻለ እንደዚህ ዓይነት እና ተመሳሳይ ጥረት ሳይደረግ በደፈናው በብር ቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ በድጋሚ በመቀበሉ ውሣኔ መስጠቱ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠውን ጉዳዩ የሚጣራበትን አግባብ ያልተከተለ በመሆኑ አግባብነት ያለው የክርክር አመራር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል ነው የበየነው።

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ቀደም ሲል ከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን መመሪያ ሳይከተል እና ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ የደረሱበት ድምዳሜ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ይላል። በመሆኑም ቀጣዩ ውሣኔ መስጠቱን ችሎቱ ያስገነዝባል።

### ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 67129 ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 65277 በቀን 24/5/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል።

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እና ሌሎች ስለማሽኑ ከመዝገቡ እና ከክርክሩ የተገኙትን ነጥቦች የሚመለከተው ባለሙያ በመግለጽ በወቅቱ የነበረው ዋጋ ሙያዊ ግምት እንዲቀርብ በማድረግ እና በማስገመት ቀደም ሲል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል ብሎ ከበየነ በኋላ መዝገቡን ዘግቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ‹‹ ቢቀር ዳቦ ድፌ - ጠላ ጥመቂ ነው ››

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

መቼም ዘንድሮ ይህ ማህበራዊ ሚዲያ ይሉት ጉዳይ አያሳየን የለም።ሰሞኑን ከአንዲት ወዳጄ ገጽ ደርሶ ያየሁት አንድ ወሬ በእጅጉ ሲያስደንቀኝ ከረመ። ነገሩ እንዲህ ነው። አንድ ከፍ ያለ ባለ ክሬም ኬክ ዙሪያው በቀለማት ደምቆ ከመሀሉ ጉልህ ቃል ሰፍሮበታል። መልዕክቱ የተጻፈው በእንግሊዝኛ ነው ‹‹ዲቮርስ›› ይላል። የጋብቻ ፍቺ እንደማለት፡፡

ጉድ ፈላ።‹‹ፍቺ›› ይሉት ቃል እኮ ትርጉሙ በጎ አይደለም።የትዳር፣ የጋብቻን መፍረስ የሚያረዳ ነው። ምን ያሻው ነው ጃል! እንዲህ አሽሞንሙኖ፣ አሳምሮ ‹‹እዩልኝ›› የሚለው? ነገሩ እያስደነቀኝ የሚያምረውን ትልቅ ኬክ በጥርጣሬ በዓይኔ ጫፍ ገረመምኩት።ልክ ነበርኩ። በጉልህ የተጻፈው ‹‹ዲቮርስ›› ይሉት ቃል መልሶ አፈጠጠብኝ፡፡

አስገራሚው ጉዳይ ይህ ብቻ አይደለም። በኬኩ ዙሪያ በአማርኛ የተጻፈው መልዕክት በእጅጉ ያመራምራል። የጽሑፉን ሙሉ ሀሳብ በቀላሉ አምኖ ለመቀበል ይቸግራልና የአፍታ ጊዜን ልወስድ ግድ ነው። እንዲያም ሆኖ ጽሑፉን ከነትዝብቱ መቀበሌ አልቀረም ።‹‹ዲቮርስ›› ከሚለው ጽሑፍ በታች በአማርኛ የተጻፈውን ቃል አንድ በአንድ አነበብኩት ። ‹‹እንኳንም ቀረብሽ ፣ ቢቀር ዳቦ ድፌ ፣ጠላ ጥመቂ ነው›› ይላል፡፡

ወዳጆቼ ! እናንተም ይህን መሰል ጽሑፍ አይታችሁ፣ ታዝባችሁ ይሆናል። በእኔ በኩል ግን ግርምታው እስካሁን በውስጤ እንዳለ ነው። በአጭሩ የኬኩ ላይ መልዕክት የባልና ሚስቱ ፍቺ በመጽደቁ የሌሎች ሰዎችን የደስታ ስሜት ለማሳየት የተገለጸ ነው። ይህ መልዕክት ለብቻው ምንአልባት የሴቷን (የሚስቲቱን) ባልንጀሮች ስሜት ያንጸበራቅራል ባይ ነኝ፡፡

መቼም አብዛኞቻችን ጊዜውን ማማረርና በጊዜው ማሳበብ ልምዳችን ሆኗል።ለዚህ አስገራሚ ጉዳይ ድንገት አስተያየት ብንጠየቅ ‹‹አይ! ጊዜ፣ ጊዜ አያሳየን፣ አያሰማን የለ ›› እያልን ልናማርር እንችላለን። ለጊዜው በጊዜ ማሳበቡን እንተወውና ወዳነሳነው ሀሳብ እንመለስ።

እኔ አሁንም በሀሳብ በኬኩ ዙሪያ ነኝ።በዚህ ማህበራዊ ገጽ ላይ የተለጠፈውን ጉደኛ ኬክ በዓይኔ ህሊናዬ እየሳልኩ። የእናንተን አላውቅም እንጂ እኔ በኬኩ መቁረስ ጀርባ ይኖራሉ ያልኳቸውን እውነታዎች በምናብ እንዲህ እየገመትኩ ነው፡፡

ፍቺ የፈጸመችው ወይዘሮ ይቅርታ፡- ወይዘሪት። ከፍርድቤት መልስ ለየት ባለ ልብስ ተውባ ከአናቷ ላይ የክብር አክሊል ደፍታ ትታየኛለች።በእርግጠኝነት እንደ እሷው ባለባበስ የደመቁ ሴቶች ዙሪያዋን ከበው ባለመደማመጥ ይንጫጫሉ።አብዛኞቹ የጥንዶቹን የቀደመ ታሪክ እያወሱ የሚሳሳቁ ናቸው።ጥቂቶቹ በባልንጀራቸው ትዳር መፍረስ አምነው ይሁንታው ላይ የሚያወጉ ይመስላል፡፡

የኬኩ ዙሪያ ታዳሚዎች ፊት ላይ ጸጸት ይሉት አይነበብም።ሁሉም በተለየ ደስታና ፌሽታ እየቦረቁ የኬኩን መቆረስ ይናፍቃሉ።በእኔ ግምት በተጻፈው መልዕክት ላይ ተቃውሞ አቅራቢዎች እንደሌሉ ግልጽ ነው። በእያንዳንዱ ቃላት ላይ የስምምነት ሀሳባቸውን እንዳጸደቁ ይሰማኛል።

ምንአልባት የትዳሩ ‹‹እንኳን ቀረብሽ›› ኬክ የሚታጀበው በሻምፓኝና በሻማዎች ብቻ ላይሆን ይችላል። የፍቺው ደስታ ላሰባሰባቸው ታዳሚዎች የተዘጋጀ ምሳ፣ አልያም የራት ግብዣ አይጠፋም።

በእርግጠኝነት ይህ ዕቅድና ድርጊት በተለይ ከሴቷ ዘመድና ቤተሰቦች ይደገፍ አይመስለኝም። የትዳርን ክቡርነት የሚያውቁ፣ ልጃቸውን ለወግ ማዕረግ ያበቁ ወላጆች ለዚህ መሰሉ ዕቃዕቃ መሰል ጨዋታ እውቅናን አይሰጡም። እርግጥ ነው፣ በትዳር ዓለም ባልናሚስት አይጋጩም፣ አይጣሉም ማለት አይደለም።ጠብ ጭቅጭቅና ምሬት በትክክል ይኖራል። ጎጆ ባለመስማማት ሲፈተን ግን ለመፍትሄው የራሱ ወግና ሥርዓት አለው፡፡

ትዳር መሀል ንፋስ በገባ፣ ቅያሜ በመጣ ጊዜ ‹‹አንተም ተዉ፣ አንቺም ተይ›› ብሎ የሚዳኝ ሽማግሌ አይጠፋም።ባልና ሚስቱን በእኩል አስቀምጦ የሚዳኝ አስታራቂ ደግሞ ባብዛኛው በለስ ይቀናዋል።ትዳር እንዳይፈረስ፣ ጎጆ እንዳይፈታ፣ ልጆች እንዳይበተኑ የሚደረገው ማስማማት ተስፋ ባስቆረጠ ጉዳይ ላይ ፍሬ ይዞ ዓመታትን ሊቀጥል ይችላል፡፡

በትዳር መሀል የሚፈጠሩ ችግሮች በዚህ መልኩ ሲፈቱ ‹‹እሰዬው›› ነው።ይህ አልሆን ብሎ የታሰበው ካልተሳካ ግን ትዳሩን በስምምነት አፍርሶ፣ ፍቺውን በፍርድቤት አጽድቆ በሰላም መለያየቱ አዲስ አይደለም፡፡

አንዳንዴ በስምምነት የሚቋጩ ፍቺዎች ውሎ አድሮ ቤተሰባዊነት ይፈጥራሉ። እንዲህ ሲሆን ትናንት በ‹‹አንተ ትብስ፣ እኔ›› የተጋመደው አብሮነት ዛሬን በእህት ወንድምነት ተጣምሮ ትርጉም ያለው ሕይወት ይሰጣል፡፡

ትዳር ከነ ችግሩም ቢሆን ሲፈርስ ቅር ያሰኛል። በእርግጥ እንከንና ችግር የዋጠው ሕይወት በይሉኝታ ብቻ ይቀጥል ላይባል ይችላል። መታወቅ ያለበት ግን ባብዛኛው መፍትሄ የሌለው ችግር አለመኖሩን ነው። ውሎ አድሮ ደግሞ ሁኔታዎች ሊለወጡ ይችላሉ።ዕድሜ ለመልካሞቹ ሽማግሌዎች ይሁንና ከባዱን አቅልለው፣ ቋጠሮውን የሚፈቱ ልበ ቀና አስታራቂዎች ሞልተዋል።

እኛ እስከዛሬ የምናውቀው፣ በሌሎችና በራስ ጥረት ጎጆ እንዲቆም ጥረት መኖሩን ነው። እኛ የምናውቀው ትዳር እንዳይፈረስ፣ ቤተሰብ እንዳይበተን ትግል መደረጉን ነው።ይህ አልሆን ብሎ ፍቺ ቢፈጸም ደግሞ የሌሎች ፈንጠዝያና ደስታ ታይቶ አይታወቅም። ‹‹እሰይ እነ እንትኔ ተፋቱ፣ ተለያዩ›› ብሎ ጭፈራና ዕልልታ የለም።ለዛውም በገሀድ፡፡

ዘንድሮ ግን ነገር ሁሉ ተቀይሯል።ለፈረሰ ትዳርና ጎጆ ከማዘን፣ ከማሰብ ይልቅ ለፍቺው ገሀዳዊ ዕውቅና ይሰጥ ይዟል። ዕውቅናው እኮ በተገቢው አካል ተችሮ ቢሆን አይደንቅም።በጥንዶቹ ልቦና ብቻ ቢቀርም እሰዬው ነው።ፍቺው ኬክ ተቆርሶለት፣ ሻምፓኝ ተከፍቶለት፣ በአጀብ ደምቆና በይሁንታ ጸድቆ ደስታን መፍጠሩ ግን እንደኔ በእጅጉ አሳዛኝ ያስብላል። ለዛውም ‹‹ትዳሩ እንኳንም ቀረብሽ፣ አበጀሽ›› እየተባለ፡፡

እስካሁን ከባህላችን ውጪ የሆኑና ለእኛነታችን የሚጠቅሙ በርካታ ልማዶችን ከነጮቹ ወስደናል።እንዲህ ማድረጋችን እስከዛሬ ለኖርንበት ሕይወታችን ሲጠቅመን መኖሩን መካድ አይቻልም። አይበጁንም ባልናቸው መጤ ባህሎች ላይ ግን ዓይን አንስተን፣ እጅ መሰብሰባችን ቢጠቅመን እንጂ አልጎዳንም ። ይህ ዓይነቱን ማህበራዊ እሴት የሚቃረን ጉዳይን ደግሞ ፈጽሞ ልንላመደው የማይገባ ተግባር ነው።ይህ ጅማሬ አጉል ልማድን ያጋባል።የትዳር ክቡርነትን ያቀልላል፡፡

እኔ በግሌ ፍቺን አስመልክቶ በሚሰጠው የዕልልታ ዕውቅና ላይ መስማማትን አልሻም።ትዳር ሲፈታ፣ ጎጆ ሲበተን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ‹‹እሰይ፣ጎሽ›› አያሰኝም።ለዛውም የሴትነት ወጉን አጣጥሎ፣ የነበረን ሙያ አንቋሾ ‹‹ቢቀር ዳቦ፣ ቢረሳ ጠላው›› እየተባለ። እስቲ ልቦና ይስጠን ።አበቃሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ምስጢራዊ ሰነዶችን አሾልኮ ያወጣው የ21 ዓመት ወጣት በቁጥጥር ሥር ዋለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የአሜሪካን እና አጋሮቿን ምስጢራዊ ሰነዶች ይፋ ያደረገው የአገሪቱ አየር ኃይል ብሔራዊ ዘብ አባል የሆነ የ21 ዓመት ወጣት በቁጥጥር ሥር ዋለ።

ምስጢራዊ ሰነዶቹን በበይነ መረብ ጨዋታ (ጌም) ጽሑፍ መላላኪያ ገጽ ላይ ያሰራጨው ጃክ ቴሼራ በአሜሪካ ፍትሕ ቢሮ በስለላ ክስ ይመሰረትበታል ተብሏል።

ወጣቱ ማሳቹሴትስ ግዛት ውስጥ ከሚገኘው ከወላጆቹ መኖሪያ ቤት በቁጥጥር ሥር ሲውል የሚያሳይ ምስል ይፋ ተደርጓል።

ቴሼራ ይፋ ያደረጋቸው ሰነዶች በዩክሬን እየተካሄደ ስላለው ጦርነት ምስጢራዊ ጉዳዮችን ይፋ ከማድረጉም በላይ አሜሪካ በአጋሮቿ ላይ ስለላ ስለማድረጓ አጋልጧል። ወጣቱ ትናንት ቦስተን በሚገኝ ፍርድ ቤት ቀርቧል፡፡

ሲቢኤስ ወጣቱ እአአ 2019 ላይ በሠራዊቱ መቀጠሩን እና የነበረው የሥራ እርከን የጀማሪ መሆኑን ከይፋዊ ሰነዶች ላይ መመልከቱን ዘግቧል።

የአሜሪካ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሜሪክ ጋርላንድ ወጣቱ በቁጥጥር ስር መዋሉን ይፋ ቢያደርጉም፣ ምስጢራዊ ሰነዶችን አሾልኮ ለማውጣት ምን እንዳነሳሳው ያሉት ነገር የለም።

በሌላ መግለጫ ደግሞ የመከላከያ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ብርጋዲዬር ጄኔራል ፓር ራይደር ድርጊቱ «ሆን ተብሎ የተፈጸመ ወንጀል ነው» ብለዋል።

ይህን መሰል ምስጢራዊ ሰነድ እንዴት ገና በወጣትነት ዕድሜ እና በታችኛው እርከን ባለ ሠራተኛ እጅ ላይ ሊገባ ቻለ ተብለው የተጠየቁት ብርጋዲዬር ጄኔራሉ፤ በአሜሪካ ጦር ውስጥ ሠራተኞች «ገና በወጣትነት ዕድሜ ከፍተኛ ኃላፊነት ይጣልባቸዋል» ሲሉ መልሰዋል።

ጃክ ቴሼር እአአ 2019 ሥራ ይጀምር እንጂ በማሳቹሴትስ ከሚገኘው የትውልድ ከተማው ኖርዝ ዳይተን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀው በ2020 ነው።

የማሳቹሴትስ የአየር ኃይል ብሔራዊ ዘብ የደኅንነት ክንፍ ባልደረባ የሆነው ወጣቱ፣ የሥራ ድርሻው የአሜሪካ አየር ኃይል ዓለም አቀፍ ኮሚዩኒኬሽን ነበር። ጃክ ቴሼር እስካሁን ድረስ ለሥራ ተብሎ ከአገሩ አሜሪካ ወጥቶ አያውቅም።

ምስጢራዊ ሰነዱ በተጋራበት የጽሑፍ መልዕክት መላላኪያ ቡድን ውስጥ አባል የሆነ አንድ ወጣት ጃክ ቴሼርን «ስለ ጦር መሣሪያ ጽኑ ፍላጎት ያለው ወጣት» ሲል ገልጾታል።

ከቴሼር ጋር በአንድ ክፍል አብሬው ተምሬያለሁ ያለው የ22 ዓመቱ ኤዲ ሶውዝ ደግሞ ቴሼር በዚህ የወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ በቁጥጥር ሥር መዋሉን ማመን አልቻልኩም ሲል ለሮይተርስ የዜና ወኪል ተናግሯል።

«በጣም ጥሩ ልጅ ነው። ችግር ፈጣሪ አይደለም። ዝምተኛ ነው። ሁኔታው በአጋጣሚ የተሠራ ቀሽም ስህተት ዓይነት ይመስለኛል» ሲል ተናግሯል።

በኢንተርኔት አማካይነት ጌም በሚጫወቱ ሰዎች ዘንድ ዝነኛ በሆነው እና ዲስኮርድ በተባለው ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ከወራት በፊት ከ100 በላይ ምስጢራዊ ሰነዶች ተለቀው ነበር።

ሰነዶቹ በዩክሬን እየተደረገ ስላለው ጦርነት ምስጢራዊ ጉዳዮችን ይፋ አድርጓል። በመላው ዓለም ስላሉ አገራት ስለላም መረጃ ይዟል።

ሰነዶቹ የምዕራባውያን አገራት ልዩ ኃይሎች በዩክሬን ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ስለመሆናቸው አሳይቷል። ዩናይትድ ኪንግደም፣ አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ላቲቪያ እና ኔዘርላንድስ ልዩ ኃይሎችን ወደ ዩክሬን መላካቸውን አጋልጧል።

ግብፅ በምስጢር ለሩሲያ ሮኬቶችን ለማቅረብ ስለመዘጋጀቷም አጋልጧል። ዋሽንግተን ፖስት ምስጢራዊ ሰነዱን ከተመለከተ በኋላ ግብፅ በድብቅ 40 ሺህ ሮኬቶችን አምርታ ለሩሲያ ልታቀርብ ነው ብሏል።

እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጌቴሬዝ የሩሲያን ፍላጎት ለማሟላት ፍላጎት አላቸው ብላ አሜሪካ እንደምታምን ሰነዶቹ አጋልጠዋል።

## ሰሜን ኮሪያ እስካሁን ያልታየ አዲስ አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል ሞከረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




አዲስ አበባ፡- ሰሜን ኮሪያ እስካሁን ከሞከረቻቸው አህጉር አቋራጭ ተወንጫፊ ሚሳኤሎች ሁሉ «በጣም ኃያል» ያለችውን አዲስ ሚሳኤል መሞከሯን አስታወቀች።

የአገሪቱ መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ሐሙስ ዕለት የተደረገውን የሚሳኤል ሙከራ «ተዓምራዊ ስኬት» ሲሉ አሞካሽተውታል።

ይህ ሚሳኤል አረሩን ለማስወንጨፍ ጠጣር ነዳጅ መጠቀሙ ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል። ሚሳኤሉ ፈሳሽ ነዳጅ ከሚጠቀሙት በፈጠነ ሁኔታ የመተኮስ አቅም ያለው ሲሆን፣ በፀረ ሚሳኤል ለመከላከልም አዳጋች ነው ተብሏል።

ነገር ግን የሰሜን ኮሪያ ጎረቤቷ ደቡብ ኮሪያ እንደምትለው ሰሜን ኮሪያ ይህንን አዲስ ዓይነት አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል ሠርታ ጥቅም ላይ ለማዋል ገና ረጅም ጊዜ ያስፈልጋታል ብላለች።

እንደ ቢቢሲ ዘገባ፣ ሰሜን ኮሪያ በጠጣር ነዳጅ የሚተኮሱ የአጭር ርቀት ሚሳኤሎችን ለዓመታት ስትሞክር ከቆየች በኋላ ነው፣ ይህንን የረጅም ርቀት ሚሳኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ሞክራለች።

ባለሙያዎች ይህ የሚሳኤል ሙከራ በሰሜን ኮሪያ የመሣሪያ ግንባታ መርሃ ግብር ውስጥ ታላቅ እመርታ መሆኑን በመግለጽ፣ ሚሳኤሉ በድንገት ያለምንም ማስጠንቀቂያ አሜሪካንን ለመምታት ያስችላታል ብለዋል።

የደቡብ ኮሪያ መከላከያ ሚኒስቴር ግን የሚሳኤል ቴክኖሎጂው አዲስ አለመሆኑን በመግለጽ፣ የሰሜን ኮሪያ አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል ሙሉ ለሙሉ ያልተጠናቀቀ በሂደት ላይ ያለ ነው ብሏል።

በሙከራው ላይ ከሴት ልጃቸው፣ ከባለቤታቸው እና ከእህታቸው ጋር የተገኙት የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን፣ የአዲሱ የሚሳኤል ሙከራ ጠላቶቻቸውን «በከፍተኛ ፍርሃት እና ጭንቀት ውስጥ ይከታል» ብለዋል።

ህዋሶንግ-18 የተባለው የሚሳኤል ሙከራ በሰሜናዊ ጃፓን ውስጥ ግራ መጋባትን በመፍጠር ነዋሪዎች ከቤታቸው እንዲወጡ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ምክንያት ሆኗል።

በዚህም ሳቢያ በጃፓኗ ሆካይዶ ደሴት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርት ዘግይቶ የተጀመረ ሲሆን፣ አንዳንድ የባቡር አገልግሎቶችም እንዲቋረጡ ተደርጎ ነበር።

የሰሜን ኮሪያው መሪ ሠራዊታቸው ጠላቶቻቸው አገራቸውን ከማጥቃት እንዲታቀቡ በሚያደርጉ ወታደራዊ ተግባራት ላይ እንዲያተኩር ካዘዙ ከቀናት በኋላ የተደረገውን ይህንን ሙከራ፣ የጃፓን፣ የደቡብ ኮሪያ እና የአሜሪካ ባለሥልጣናት አውግዘውታል።

ተንታኞች እንደሚሉት ይህ የሰሜን ኮሪያ አዲስ እና ኃያል የሚሳኤል ሙከራ በድንገት የተከሰተ ሳይሆን ለዓመታት በአጭር ርቀት ሲደረግ የቆየው ሙከራ ውጤት ነው።

ሰሜን ኮሪያ ባለፉት ዓመታት ያሏትን የኑክሌር ጦር መሣሪያዎች ለማሳደግ እና እጅግ የረቀቁ የጦር መሣሪያዎችን ለመገንባት ስትሰራ ቆይታለች።

በተጨማሪም ጎረቤት ደቡብ ኮሪያ ከአሜሪካ ጋር የምታደርገውን ወታደራዊ ልምምድ በአካባቢው ያለውን ውጥረት የሚያባብስ ነው በማለት ስትቃወም ነበር።

ይህ ሳምንት የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ሥልጣን ከያዙ 11ኛ ዓመት የሚከበርበት በመሆኑ፣ ጊዜውን አገሪቱ የደረሰችበትን ወታደራዊ ደረጃ ለማሳየት ልትጠቀምበት ትችላለች ተብሏል።

የአሁኑ የሚሳኤል ሙከራ የተደረገው በሰሜን ኮሪያ ውስጥ ከሚከበሩት ብሔራዊ በዓላት መካከል ትልቁ የሆነው የአገሪቱ መሥራች ከኪም ኤል ሱንግ ልደት ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ የተደረገ ነው።

## መጋቢ አዕምሮ

# ውሳኔ ብቻውን ውሳኔ አይደለም!



**አስናቀ ፀጋዬ**

የሰዎች የእለት ተእለት ክዋኔ በውሳኔ የተሞላ ነው። በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያቸው ውስጥም ሰዎች የተለያዩ ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ። ከዚህ አንፃር ውሳኔ የሰው ልጅ አንዱ የሕይወት አካል እንደሆነ ይቆጠራል። የሰውን ልጅ ከፍና ዝቅ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥም የመወሰን አቅሙ እንደሆነ ይነገራል። ለዛም ነው ውሳኔን በራስ፣ በኑሮና በሕይወት ላይ ማስተላለፍ እጅግ ቁልፍ ጉዳይ ነው የሚባለው።

ውሳኔ አንድን ነገር የማድረግና ያለማድረግ ምርጫ ነው። አንድን ነገር ለማድረግና ላለማድረግ በመምረጥ ሂደት ግን ማመንታት፣ ለመወሰን መቸገር፣ ቸኩሎ አልያም ደግሞ ዘግይቶ መወሰን፣ ለመወሰን ከራስ ጋር ሙግት መግጠምና ሌሎችም መሰል እንቅፋቶች ያጋጥማሉ። ዋናው ቁም ነገር ግን የተሻለ ውሳኔ መወሰን ውጤቱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ መረዳት ያሻል። በተለይ ደግሞ ከውሳኔ በፊት የውሳኔውን ውጤት በጥልቀት መረዳት የተሳሳተ ውሳኔ ከማሳለፍ ይታደጋል።

ለምሳሌ አንድ ሰው በቀን አንድ ገፅ መጽሐፍ ለማንበብ ወስኖ ያለውን ካደረገ አዕምሮውን ለማሳደግ ቆርጦ ተነስቷል። በየቀኑ ለተወሰኑ ደቂቃዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ ከወሰነ የአካል ብቃቱን እያሳደገ ነው። ይህ ሲባል እግረ መንገዱን የሰውነቱን ጤና ከመጠበቅ በዘለለ ትንፋሹን፣ ፅናቱንና ነገሮችን የመቋቋም አቅሙን እያጎለበተ ነው። ይህ ሁሉ የሚመጣው ታዲያ በውሳኔ ነው።

በጣም ለሚወደው ነገር ትልቅ ትኩረት ለመስጠት የወሰነ ሰው የገንዘብ ስኬት ወደሚሰጠው ነገር ራሱን እየወሰደ ነው። የማኅበረሰብ ወይም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ የተወሰነ ግዜ ለመስጠት የወሰነና ያለውን የሚፈፀም ሰው የሕሊና እርካታ ወደሚሰጠው ነገር እየተጓዘ ነው። ለሚወዳቸው ሰዎች፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለጓደኞቹ፣ ለፍቅረኛው ግዜ ለመስጠት የወሰነ ሰው ስሜታዊ እርካታ ለሚሰጠው ነገር እየጣረ ነው። ታዲያ አንተስ መቼ ነው በአካል፣ በፋይናንስ፣ በሥነ-ልቦና፣ ለስሜትና ደስተኛ ለሚያደርጉ ነገሮች ግዜ ለመስጠት የምትወስነው?

አንዳንድ ሰዎች ‹‹ደስተኛ ወይም ስኬታማ ያልሆንኩት የምፈልገው ነገር ስላልተሟላልኝ ነው፤ በቤተሰቦቼ ምክንያት ነው፤ በዙሪያዬ ባሉ ጓደኞቼ ምክንያት ነው ወይ ደግሞ በምኖርበት ሀገር ድህነት ምክንያት ነው›› ሊሉ ይችላሉ። እነርሱ እነዚህን እንደምክንያት ቢዘረዝሩም ታዲያ ምክንያታቸው ውሃ የሚቋጥር አይደለም። ምክንያቱም መወሰን ስላልቻሉ ነው። እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር በእጃቸው ለማስገባት ቢወስኑ ኖሮ ለዛ ነገር የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለው ማሳካት አያቅታቸውም ነበር።

አንድ ጀልባ ቀዛፊ የልጅነትና አብሮት የተማረ ጓደኛው ከሀገሪቱ ንጉሥ ቀጥሎ ትልቅ ሥልጣን የሚባለውን ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ሁሌም እንቆቅልሽ ይሆንበታል። እሱ ከኔ ምን የተለየ ነገር ቢኖረው ነው እኔ እዚህ ውሃ ለውሃ ጀልባ ለመቅዘፍ እየተንከራተትኩ እሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆነው ብሎ ሁሌም አምርሮ ይቀናና ይናደድ ነበር።

በአንድ አጋጣሚ የሀገሪቱ ንጉሥ ከባድ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያደርጉትን ስብሰባ ለማካሄድ ካቢኔያቸውን ሰብስበው ያንን ወንዝ መሻገር ነበረባቸውና የዚህን ሰው ጀልባ ይሳፈራሉ። ጀልባውን ተሳፍረው ወንዙን ከተሻገሩ በኋላ ንጉሡና ካቢኔያቸው ማታ ከወንዝ ማዶ ጊዜያዊ ድንኳን አዘጋጅተው ባረፉበት ወቅት ሌሊት ላይ ለቅሶ ያዘለ ከባድ ጩኸት ይሰማሉ። ከዛም ባለጀልባውን አስጠርተው ጩኸቱ ምን እንደሆነ ይጠይቁታል።

ባለጀልባውም ቆይ አረጋግጬ ልምጣ ብሏቸው ትንሽ ቆይቶ ተመልሶ ይመጣና ድመት እንደጮኸች ይነግራቸዋል። ‹‹የጫካ ናት ወይስ የቤት ድመት?›› ብለው ሲጠይቁት ‹‹ቆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ›› ብሎ ተመልሶ ሄዶ አረጋግጦ ይመጣና ‹‹የቤት ድመት ነች ለማዳ ናት›› ብሎ ይመልሳል። ‹‹አሃ! ምን ሆና ነው ግን የጮኸችው›› ብለው ይጠይቁታል። አሁንም ‹‹ንጉሥ ሆይ አሁንም ሄጄ አረጋግጬ ልምጣ›› ብሎ ተመልሶ ሄዶ ይመጣና ሙጭሊቶች በምትወልድበት ጊዜ እንደጮኸች ይነግራቸዋል። ንጉሡም ‹‹ስንት ልጆች ወለደች?›› ብለው ይጠይቁታል። ‹‹ቆይ ንጉሥ ሆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ›› ይላቸውና አሁንም ደርሶ ይመለስና አራት ሙጭሊቶች እንደወለደች ይነግራቸዋል።

**በየቀኑ የምታደርጋቸው ትናንሽ ውሳኔዎች ሕይወትህን እስከመጨረሻው ይቀይሩታል። አስተውል ትልቁን መርከብ የሚያሰምጠው ማዕበል ብቻ አይደለም። ከታች በትንሽዬ ቀዳዳ ውሃ መግባት ከጀመረ የግዜ ጉዳይ ነው እንጂ መርከቡ መስጠሙ አይቀርም። ስለዚህ አንተም የምትወስናቸው ውሳኔዎች በሙሉ ሕይወትህን ሊቀይሩት ይችላሉ። እነዚህ ትናንሽ ውሳኔዎች ላይ ብልጥ ከሆንክ፣ ጥበበኛ ከሆንክ ትላልቆቹ ውሳኔዎች ሲመጡ መወሰን አይከብድህም። ምክንያቱም በትናንሾቹ ጥሩ በራስ መተማመን ይሰማሃልና**

ንጉሱ አሁንም መልሰው የሙጭሊቶቹ ቀለማቸው ምን አይነት እንደሆነ ይጠይቁታል። እርሱም አሁንም አረጋግጬ ልመለስ ይላቸውና ደርሶ ይመለሳል። ሁለት ጥቁር ሁለት ነጭ ሙጭሊቶች እንደወለደች ይነግራቸዋል። ‹‹እንዴ እናትዬዋስ ቀለሟ ምን ይመስላል›› ብለው ንጉሡ ሲጠይቁት ንጉሥ ሆይ እሱንም አረጋግጬ ልምጣ ይላቸውና ተመልሶ መጥቶ የእናትዬዋ ቀለም ነጭ በጥቁር እንደሆነ ይነግራቸዋል።

በዚህ ግዜ ንጉሡ ታዲያ ለድመቷ ምን አደረክላት ብለው ጀልባ ቀዛፊውን ይጠይቁታል። እርሱም ንጉሥ ሆይ ቆይ አንድ ነገር አድርጌላት ልምጣ ብሎ ሊሄድ ሲል ቆይ ቆይ አንተ እዚሁ ጋር ቆየኝ ብለው እዛው በቆመበት የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ካረፈበት ድንኳን አስጠርተው ‹‹የሆነ ጩኸት ሰምቼ ነበር እስኪ ምን እንደሆነ አጣራ›› ብለው ይልኩታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም እሺ ብሎ ከአፍታ ቆይታ በኋላ ይመለሳል።

ጩኸቱ የተሰማው አንድ ጥቁር በነጭ ቀለም ያላት የቤት ድመት አራት ሙጭሊቶች በወለደች ቅፅበት እንደሆነና የወለደቻቸው ሙጭሊቶችም ሁለት ነጭ ሁለት ጥቁር ሲሆኑ ለእናትዬዋ ምግብና ወተት እንደተሰጣት እርሷና ሙጭሊቶቿ ለማዳ የቤት ድመት በመሆናቸው የዱር አውሬ እንዳያጠቃቸው አስተማማኝ በሆነ አጥር እንደከለሏቸው ይናገራል።

ንጉሱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላቀረበላቸው ሪፖርት አመስግነው ካሰናበቱት በኋላ ወደጀልባ ቀዛፊው ዞረው እንዲህ አሉት። ‹‹ጀልባህን ተሳፍረን ስንመጣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እያየህ ሲሰማህ የነበረውን የቅናት ስሜት አስተውዬው ነበር። የኔና የእርሱ ልዩነት ምንድን ነው ብለህ ለራስህ ስጠይቅ እንደነበረም እገምታለሁ። አንተ ብዙ ግዜ ተመላልሰህ ሁኔታውን ተመልክተህ ያልወሰንከውን ውሳኔ እርሱ በአንድ ምልከታ ወጥቶ ወስኖ ነገሮችን አስተካክሎ መጣ።››

እንግዲህ በሕይወታችን ውስጥ ወደተለያየ አቅጣጫ የእኛን በሳል ውሳኔዎች ሊጠይቁ የሚችሉ ወቅቶች ይመጣሉ። እነዛን ወቅቶች ግን የምናልፋቸው ወይም የምንወስናቸው በየትኛው ጥበባችን ነው? በሕይወታቸው ላይ አስገራሚ ለውጥ ያመጡ ሰዎች ከባድ ውሳኔዎችን ወስነው እዛ እንደደረሱ አስብ። አንተ ራሱ አሁን የደረስክበትን ደረጃ የወሰነልህ ከዛሬ አምስትና አስር ዓመት በፊት ታደርጋቸው የነበሩ ነገሮች ናቸው። ታነባቸው የነበሩ መጽሐፍት፣ ታያቸው የነበሩ የቴሌቪዥን ሾዎችና ፊልሞች፣ ትሰማቸው የነበሩ ዘፈኖች፣ በዙሪያህ ይሰበሰቡ የነበሩ ጓደኞችህ፣ አብረሃቸው የምትውላቸው ሰዎች ናቸው ዛሬ የቆምክበትን የወሰኑልህ።

ታዲያ አንድ ነገር አስተውል። የዛሬ አምስት ዓመት የሚኖርህንም ሁኔታ የሚወስኑት አሁን የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ በቶሎ ወስን። ሚዛን ወደምትፈልገው አቅጣጫ እንድታጋድል ከፈለክ ያን አቅጣጫ ጫን አድርገህ መያዝ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ። ስለዚህ አንተም የዛሬ አምስትና አስር ዓመት መሄድ ወደምትፈልግበት አቅጣጫ ሚዛን እንድታጋድል አሁኑኑ ወስንና ውሳኔህን ተግባራዊ ለማድረግ ወስን። ውሳኔ ከዚህ በላይ ምንም አይጠይቅም። ሕይወት ቀያሪ ነገር ነው ተጠቀምበት። ነገር ግን ደግሞ ትክክለኛ ውሳኔ በትክክለኛው ቦታና ሰዓት ለመወሰን ከፈለክ የሚከተሉትን ስድስት ነጥቦች ተከተል።

### 1ኛ. ችግሩን ጠንቅቆ ማወቅ

ምንም ሰው አንድ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት መሰብሰብ ያለበትን መረጃዎች ሁሉ መሰብሰብ ይኖርበታል። ማወቅ ያለበትን ነገር ሁሉ ማወቅ አለበት። ይሁንና ስለሚወስነው ነገር በቂ መረጃ ከሌለው ግራ ይጋባል። ይሁንና መረጃ መሰብሰብ ሲጀምር በቂ እውቀት ኖሮት እርግጠኝነትና ልበ ሙሉነት ይሰማዋል። እንዲያም ሆኖ ከመጠን በላይ መረጃ ከተሰበሰበ ደግሞ መልሶ ግራ መጋባት ይመጣል። ስለዚህ በቂ መረጃ ሲኖር መወሰን የግድ ይላል።

እዚህ ጋር በቂ መረጃ እንዳለ እንዴት ሊታወቅ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ መልስ ባይኖርም በቂ መረጃ ሲኖር እርግጠኝነት ይሰማል። ለእርግጠኝነት የቀረበ ስሜት ሲሰማ ደግሞ መወሰን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ያኔ በቂ መረጃ ተይዟል ማለት ነው።

### 2ኛ.የሚወሰነው ውሳኔ ከሕይወት ዓላማ ጋር አብሮ መሄድ አለበት

ለዛሬ ወይም ለጊዜያዊ ጥቅም ብለን ቀላል ውሳኔ መወሰን የለብንም። ዘላቂውን ጥቅም ማስቀደም አለብን። ነገ ምን ሊፈጠር ይችላል፤ ምን ላገኝ እችላለሁ፤ ምን ልጎዳ እችላለሁ ብለን ማሰብ አለብን። ምንም ነገር ከመወሰናችን በፊት ነገን ማሰብ ይኖርብናል። ውሳኔያችን ከሕይወት ዓላማችን፣ ከነገው ፍላጎታችን፣ ከመዳረሻችን፣ ከማንነታችን ጋር አብሮ እንደሚሄድ እርግጠኛ መሆን አለብን።

### 3ኛ. ሌላ ሰው እንደምንመክር አስበን መወሰን

እንደምታውቁት ለሌሎች ሰዎች መምከር እንችልበታለን። ሰዎች ምን ቢያደርጉ ምን እንደሚሳካላቸው እናውቅበታለን። ለራሳችን ነው የማናውቀው። ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ይባላል። እኛም ብንሆን ብዙ ግዜ ለሰው እንጂ ለራሳችን አናውቅም። ስለዚህ ራሳችን የገጠመን ችግር ሌላ ሰው እንደገጠመው አስበን ራሳችንን መምከር ያስፈልጋል። እንደሁለተኛና ሦስተኛ ወገን አይተን ራሳችንን ‹‹እንዲህ ብታደርግ እንዲህ ይፈጠራል፤ እንዲህ ብታደርግ ይሄ ነው መፍትሔው›› እያልን ራሳችንን መምከር ይገባል። ያኔ ከጫና እንወጣለን። ምክንያቱም እኔ አይደለሁም ችግር ውስጥ የገባሁት እንላለን። ያኔ ብዙ መፍትሔ ይመጣል። ከመፍትሔዎቹ መካከል ጥሩውን መርጠን መወሰን ነው።

### 4ኛ.ውጤቱን ማነፃፀር

አንድ ነገር ከመወሰናችን በፊት ‹‹ያ የምንወስነው ውሳኔ ምን ሊያስከትል ይችላል፤ እንዲህ ብማር ነገ ደስተኛ ላልሆን እችላለሁ፤ እንዲህ ብሠራ ሥራው ላያድግ ይችላል፤ ይህን ቢዝነስ ብጀምር እኮ መጨረሻ ላይ ሄዶ ሄዶ እዚህ ጋር ሊያቆም ይችላል›› ብለን ብዙ ነገር አስበን ውጤቱን አሰላስለንና አወዳድረን መወሰን ያስፈልጋል። እንደዛ ካላደረግን መጨረሻ ላይ የሚመጣው ውጤት ከባድ ይሆናል። ምክንያቱም አሁን ያለንበት ጋር ቆመን ብቻ ማየት የለንበትም። ስለዚህ አንድ ነገር ከመወሰናችን በፊት ውጤቱን ማሰብና አስቀድሞ መተንበይ አለብን። ከዛ በኋላ የሚጎዳ ከሆነ መተው፤ የሚጠቅም ከሆነ ደግሞ መቀጠል ነው።

### 5ኛ. በየቀኑ የምንወስናቸው ትናንሽ ውሳኔዎች ላይ መለማመድ

በቀን ውስጥ በጣም ብዙ ውሳኔዎችን እንወስናለን። ጠዋት ስንት ሰዓት ልነሳ፣ ሥራ ልግባ አልግባ፤ ምን ልብላ፤ ከማጋር ልዋል፤ ምን ሳደርግ ልዋል፤ ምን ላድርግ፤ በምን ልዝናና፤ ምን ስሠራ ላምሽ፤ ምን ልጠጣ፤ ምን ልብላ .... ወዘተ ብዙ ውሳኔ አለ። እነዚህ ውሳኔዎች ግን ሕይወታችንን እስከመጨረሻ ድረስ ሊቀይሩት ይችላሉ። ምክንያቱም የዛሬ አምስት ዓመት በፊት ታደርጋቸው የነበሩ ነገሮች፣ አብርሃቸው ትውላቸው የነበሩ ሰዎች፣ ታያቸው የነበሩ የቴሌቪዥን ፊልሞች ፣ ድራማዎች፣ ታነባቸው የነበሩ መጽሐፍቶች፣ አብረሀቸው ትሰበሰባቸው የነበሩ ሰዎች በሙሉ ዛሬ የደረስክበትን ደረጃ ወስነዋል። ዛሬ የምታደርጋቸውም ነገሮች የዛሬ አምስትና አስር ዓመት የምትደርስበትን ይወስናሉ። የዛሬ አምስት ዓመት ያደረከው ከዛሬው ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የዛሬም አምስት ዓመት አሁን ያለህበት ቦታ ነው የምትኖረው።

ስለዚህ በየቀኑ የምታደርጋቸው ትናንሽ ውሳኔዎች ሕይወትህን እስከመጨረሻው ይቀይሩታል። አስተውል ትልቁን መርከብ የሚያሰምጠው ማዕበል ብቻ አይደለም። ከታች በትንሽዬ ቀዳዳ ውሃ መግባት ከጀመረ የግዜ ጉዳይ ነው እንጂ መርከቡ መስጠሙ አይቀርም። ስለዚህ አንተም የምትወስናቸው ውሳኔዎች በሙሉ ሕይወትህን ሊቀይሩት ይችላሉ። እነዚህ ትናንሽ ውሳኔዎች ላይ ብልጥ ከሆንክ፣ ጥበበኛ ከሆንክ ትላልቆቹ ውሳኔዎች ሲመጡ መወሰን አይከብድህም። ምክንያቱም በትናንሾቹ ጥሩ በራስ መተማመን ይሰማሃልና።

### 6ኛ. ከውሳኔ በኋላ ማመንታት የለብንም

ይህ ወሳኝ ነጥብ ነው። ከውሳኔ በኋላ ማመንታት የለብንም። አንዳንድ ግዜ ጥሩ ውሳኔ እንወስንና ቆይ እስኪ ይህን ነገር ባደርገው ብለን ማመንታት ከጀመርን ሌላ የማይረባ ውሳኔ ይከተልና እሱን ወስነን የማይረባ ነገር ይፈጠራል። ስለዚህ በደምብ አስበን ከወሰንን በኋላ ወደ ድርጊት መግባት አለብን። እርግጥ ወሰንን ማለት ወደ ድርጊት ገባን ማለት አይደለም።

ስለዚህ ከላይ የተቀመጡት አምስት ትክክለኛ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚረዱ ነጥቦችን ከተጠቀማችሁ መወሰን አለባችሁ። መወሰን ግን ብቻውን በቂ አይደለም ወደገደለው ወደ ድርጊት መግባት ይኖርባችኋል። ያ ማለት ስድስተኛውን ነጥብ ልብ ማለት ይገባል።

**ከቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም**

# የሆስፒታሉ አመሰራረት እና የአእምሮ ሕክምና በኢትዮጵያ

**አብዩ የኔአለም**

አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ በአንድ የአዕምሮ ሃኪም ብቻ ሲሠራ የቆየ ነበር። የዓለም የጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር የነበሩትና የስዊዝ ዜግነት ያላቸው ፕሮፌሰር መሃለር (Prof. Mehaler) የተባሉ ግለሰብ ናይጄሪያዊ ከሆነው ምክትላቸው ፕሮፌሰር አደዌ ኤላምቦ ጋር እ.ኤ.አ በ1985 ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቋሙን ጎበኙ። በዚህ ወቅት በአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ከ30 በላይ የአዕምሮ ህሙማን ታጉረው በመመልከታቸው እንዲሁም በተቋሙ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩን በመገንዘባቸው የተለያዩ የአዕምሮ ህክምና ባለሙያዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉና አገልግሎት እንዲሰጡ ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ።

በዚህም የአማኑኤል ሆስፒታል ከምሥረታው ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰባዎቹ መጀመሪያ ድረስ በውጭ አገር ሐኪሞች ሲመራ ከቆየ በኋላ ቀስ በቀስ በኢትዮጵያውያን መተካት ጀመረ። ያኔ ዕድል ፊቷን ስታዞር በወቅቱ የነበረው የጉብኝት ውጤት መንግስትን ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተወሰነ መልኩ ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ አስችሏል። በዚህም የተቋሙ የህክምና ባለሙያዎችን በኮሚቴ በማዋቀርና ዕቅድ በማዘጋጀት ቤተ ህክምናውን የማሳደግና የመለወጥ ትግል ተጀመረ። ከዚህ በኋላ የጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስቴር የሆኑት ዶክተር ጌታቸው ታደሰ እና በሀገራችን የመጀመሪያው የአዕምሮ ሃኪም (ሳይካትሪስት) በሆኑት በዶክተር ፍቅረ ወርቅነህ የሚመራ የአዕምሮ ጤና ክብካቤ የድርጊት ግብረ-ሃይል የሚባል ማህበር ተቋቋመ።

ይህ ማህበር ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የነርቭ ህክምና ክፍል፣ ከማረሚያ ቤት፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴር ወዘተ ባለ ድርሻ አካላትን ያካተተና ባለሙያዎች ያሉት ፈፃሚ ግብረ-ሃይል አቋቋመ። የዚህ ግብረ-ሃይል ተቀዳሚ ተግባርም የወደፊት የአእምሮ ጤና ክብካቤ አቅጣጫ ምን መሆን እንደሚገባውና ምን መሠራት እንዳለበት ለመተለም የታሰበ ነበር። ለዚህም መሳካት በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ዘመናዊ የአእምሮ ህክምና ትምህርት በቀዳማዊ ኃይለስላሴ የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል ያስጀመሩት የሆላንድ ዜግነት ያላቸው ፕሮፌሰር ሮበርት ጊልን ጨምሮ የተለያዩ ባለሙያዎች ትልቅ ስራ ሰርተው አልፈዋል።

በዚህም በአጭር ጊዜ ዕቅድ ላይ በሀገሪቱ ውስጥ የአእምሮ ጤና ህክምና የነርስነት ስልጠና እንዲጀመር፣ በየክፍለ ሀገሩ (ክልሎች) ዋና ከተሞች የአእምሮ ጤና አገልግሎት የሚሰጥበትን መንገድ መንደፍ፣ ለአእምሮ ህክምና የሚረዱ መድሀኒቶች አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፣ በህክምናው ዘርፍ ባለሙያዎች ወደ ውጭ ሀገራት ሄደው ተጨማሪ ትምህርቶችን እንዲያገኙ ማስቻል የሚሉት የተካተቱ ሲሆን በረጅም ጊዜ ዕቅድ ደግሞ የሀገሪቱን የአእምሮ ጤና ክብካቤ ማጎልበት እንዲቻል ያልተማከለ የአዕምሮ ጤና አገልግሎትና በየሆስፒታሉ የተዋሃደ (የተቀናጀ) የጤና አገልግሎት መስጠት፣ የአዕምሮ ህክምና ትምህርትና ምርምርን በሀገር ውስጥ መጀመር፣ ታካሚዎችን በቅርበት ለመርዳት እና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት በክልል ከተሞች ላሉ ባለሙያዎች የአእምሮ ጤና ህክምና ነርስነት ስልጠና በመስጠት የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል የዕቅዱ አካል ስለነበር በ1979 ዓ.ም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ሰፊ ስልጠናዎች መሠጠት ተጀመረ።

በዚህ አንጋፋ የህክምና ተቋም ባለፉት 80 ዓመታት በብቸኝነት በሚሰጣቸው የአዕምሮ ህክምናዎች ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል አገልግሎት አግኝቶበታል እያገኘም ይገኛል። በዚህም የተለያዩ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ ሠዓሊያን፣ ገጣሚያን፣ ደራሲያንና ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎች ህክምና ወስደውና አገግመው ወጥተው ወደ ማህበረሰቡ በመቀላቀል መደበኛ ኑሮአቸውን እየመሩ ይገኛሉ።

በአሁኑ ጊዜ ይህ አንጋፋና በሀገሪቱ ብቸኛ በመሆን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የአዕምሮ ህክምና መስጫ ተቋም የህዝብ ቁጥር መጨመርና የአገልግሎት ፈላጊ ዜጎች መብዛትና አለመመጣጠን ተከትሎ መንግስት በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ምክንያት ተጨማሪ የህክምና ተቋም ማስፋፊያ ስራ ስታንዳርዱን የጠበቀ የሳይካትሪ ህክምና መስጠት የሚያስችል የህንፃ ግንባታ በ2015 ዓ.ም የሚጀመር ይሆናል። ሆስፒታሉ እስከ 2013 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ የአእምሮ ህክምናን ለአዋቂዎች ብቻ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን አሁን ላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተመላላሽ የህፃናት የአእምሮ ህክምና በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህም ህክምናው ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ እንዲሆን አድርጎታል።

በቀጣይም ሆስፒታሉ የህፃናት የተኝቶ የአእምሮ ህክምና ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል። ሆስፒታሉ ከተመሰረተበት ከ1930 ዓ.ም ጀምሮ ለበርካታ የአእምሮ ህሙማን በተኝቶ፣ በተመላላሽ፣ በድንገተኛ ህክምና፣ በጭንቅላት ምርመራ (EEG) ፣ የኤሌክትሪክ ንዝረት ህክምና (ECT)፣ ከህግ ጋር የተያያዙ የአእምሮ ህክምናና ምርመራ (ፎረንሲክ)ና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የነርቭ ህክምና እየሰጠ የሚገኝ አንጋፋ ሆስፒታል ሲሆን ከህክምና አገልግሎቱ ጎን ለጎን በማህበራዊ አገልግሎቱም የአንበሳውን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል። በዚህም የአእምሮ ጤና አገልግሎቱ ባልተማከለ ሁኔታ በሁሉም ጤና ተቋማት መስጠት ይቻል ዘንድ ሆስፒታሉ የተቀናጀ የማህበረሰብ የአእምሮ ጤና አገልግሎቱን ከ28 ጤና ጣቢያዎች ጋር (20 ከአዲስ አበባ፣ ስምንት በአዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን) የባለሙያ እገዛ በማድረግ አገልግሎቱን እንዲጀምሩ አድርጓል። በተጨማሪም በመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን፣ በጌርጌሴኖን የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል እንዲሁም በሰዋሰው ገነት የህፃናት፣ አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ተቋማት ላይ ባለሙያ መድቦ በማሰራትና የመድሃኒት ድጋፉንም ጨምሮ ማህበራዊ አገልግሎቱን እየተወጣ ይገኛል።

አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በአሁኑ ወቅት የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ለማቀላጠፍና ለማሻሻል በሚሰራው ሥራ ውስጥ 492 አራት መቶ ዘጠና ሁለት የአስተዳደር ሠራተኞች እና 370 የጤና ባለሙያዎች ከእነዚህም ውስጥ ዘጠኝ የአእምሮ ስፔሻሊስት ሃኪሞች (ሳይካትሪስት) ሲሆኑ በአጠቃላይ 862 ሠራተኞችን ይዞ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በአጠቃላይ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተጠሪነቱ ለኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር ሆኖ ውስጣዊ መዋቅሩ በበላይነት የቦርድ አባል ያለው ሆኖ በአንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚመራ፣ በውስጡ ስድስት ቡድኖችን በያዘ የምርምርና ስልጠና ሥራውን የሚያካሂድ የአካዳሚክና ምርምር ዳይሬክቶሬት ያለው፣ በ11 የተለያዩ የክሊኒካል አገልግሎቱን የሚሰጡ ዳይሬክቶሬቶችን በአቀፈ አንድ ዋና ክሊኒካል ዳይሬክተርና እንዲሁም በ11 የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬቶችና አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ተደራጅቷል።

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም**

**አፍሪካዊቷ መልህቅ**

# የአዲስ አበባ የቱሪዝም መለያ ተምሳሌት

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

አዲስ አበባ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ፣ ከኒውዮርክ ከጄኔቭ ከተማ ቀጥሎ የብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ኤምባሲዎች ያለባት ነች። የኢትዮጵያ አየር መንገድም መነሻ መሆኗም ብዙ ተሰብሳቢዎች እና ትራንዚት የሚያደርጉ ማለትም (አርፈው በማግስቱ በሁለት ቀን ወይም በሦስት ቀን ወደ ሌላ አገር ከተማ) የሚሄዱ ሰዎች ይመጡባታል። ቱሪስቶች መዲናዋን ባላቸው በአጭር ጊዜ ለማስጎብኘት፣ ገፅታዋን ለመገንባት፣ በሆቴሎቹ ተዝናንተው እንዲወጡ የሚያስችሉ ተስፋ ሰጪ ጅማሬዎች በቢሮው እየታዩ ነው።

ቱሪስቶችም በመዲናችን ተዝናንተው ዶላራቸውን አፍሰው ሊሄዱ የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸት መረባረብ ይገባል። አየር መንገዱን ጨምሮ ሆቴሎች፣ የአርት ጋለሪዎች፣ ቤተ መዘክሮች፣ ባህላዊ ምግብ ቤቶችና ዘፈንና ውዝዋዜ ቤቶች፣ ባህላዊ አልባሳት መሸጫ እና የፋሽን ባለሙያዎች ተነቃቅተው በጋራ ሊሠሩ የሚችሉበት ነው። የውጭ ምንዛሪ ይስባሉ፣ ገቢ ያገኛሉ።

ቢሮው አዲስ አበባን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ከሚያስችለው ሥራ መካከል፣ የ Discover Addis Ababa ማለትም አዲስ አበባን ይጎብኙ አርማ አንዱ ነው። ባለፈው ሳምንት በመዲናዋ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙዚየም በተካሄደ የግማሽ ቀን ዐውደ ጥናት የተወሰነውን ማቅረባችን ይታወሳል። ለዛሬ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአለፈለገ ሰላም የስዕል ትምህርት ቤት የዲዛይን ዲፓርትመንት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን ታፈሰ አርማውን አስመልክቶ የሰጡትን ሙያዊ አስተያየት ቀንጭበን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ካካሄዳቸው ጥናቶች ውስጥ ብዙ ውይይት ተደርጎበት ‹‹አፍሪካዊቷ መልህቅ›› የሚለው ከተማውን ሊመጥን ይችላል ተብሎ ተመረጠ። ቢሮው ‹‹አፍሪካዊቷ መልህቅ›› የሚለውን መለያ ቃል ወደ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለፈለገ ሰላም የስዕል ትምህርት ቤት አምጥቶ ወደ ምስል እንዲቀየርላቸው አስበው ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም ሀብት በተለያዩ አካላት ማቀፍ እንዲቻል ሠሩ።

በከተማው ውስጥ የተለያዩ የቱሪዝም ሀብቶች አሉ። ቆየት ያሉ ታሪካዊ ሕንፃዎች፣ ኪነ ሀብቶች፣ ሙዚየሞች፣ በቅርቡ የተገነቡ ሰፋፊ ፓርኮች አሉ። የስዕል ትምህርት ቤቱ የዲዛይን ዲፓርትመንት ኃላፊ ተስፋሁን እንደተናገሩት፣ አፍሪካውያን ባይተዋርነት እንዳይሰማቸውና የቤተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው፣ መዲናዋን ከተማችን ናት እንዲሉ፣ ምን ዓይነት መልክ፣ ቅርፅ እንስጠው በሚል ተጠንቶ፣ ስሜቱ፣ ሁሉንም እንዲይዝ አረንጓዴ ተደርጓል። በተለይ ደግሞ የአፍሪካ ሀገራትን አማካይ ቀለማቸው በማየት፣ የአፍሪካ ኅብረት መለያ ምልክት ከምን ተነስተው እንደሠሩት ተጠንቶ አርማውን ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

አክለውም፣ መዳረሻ መንገዱ (ፓዙ) የአፍሪካዊነት ስሜት እንዲያመጣ የተሳለው ነው። የመዳረሻ መንገዱን በመዘርጋት ይህንን አፍሪካዊነትን ስሜትን እንዲያመጣ የማድረግ ሥራ ነው። የአፍሪካ ካርታ የሚመስል ጥበብ ነው፣ እንጂ የአፍሪካ ካርታ አይደለም ሲሉ አቶ ተስፋሁን ይናገራሉ።

አደይ አበባው የአፍሪካ ቅርጽ በሚመስል ፓዝ ላይ የተሳለ ነው። የኢትዮጵያ የተለየ አበባ ነው። ስምንት ኮከባማ ቅጠል፣ ዘለላ ወይም ዘርፍ አሉት። አደይ አበባ በተለያዩ ሁኔታዎች የሰው ልብ ውስጥ በትዝታ የሚሰርፅ ነው። አደይ አበባ አዲስ ዓመት ሲከሰት መስኩን የሚያውቡት፣ የሚያፈኩት የአዲስ ዘመን ጌጥና ምልክት፣ የምስራች ናቸው። እናም የአደይ አበባን ምልክት መጠቀሙ ጎብኚዎችንም ለመሳብ ይረዳል በሚል እንደ አርማው የተመረጠ ነው።

የአደይ አበባ በዜጋው ሁሉ ኅሊና ውስጥ ያለ ነው። በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች፣ በሕፃናቱ በአዛውንቱ፣ በተማሩት ባልተማሩት፣ በኮረዳዎቹ በጎረምሶቹ፣ በመበለቱ በባልቴቱ፣ በወታደሩ፣ በወዛደሩ፣ በከተሜው፣ በገጠሬው የተለያየ ፍልስፍና ባለውና በሌለው፣ በድሀውና በሀብታሙም ዘንድ በሙሉ ይታወቃል። አደይ አበባ ሲነሳ መልካም ዕሳቤ አለ። ከአሮጌው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን፣ ከክረምት ጨለማ ወደ መጸው ብርሃን የምንሸጋገርበት ምልክት ነው።

ከዚያ በተጨማሪ በአገራችን እንግዶችን ስንቀበል በተለይ ዲፕሎማቶችንና የውጭ ባለሥልጣኖችን ቀይ ምንጣፍ የነበረው የእንግዶች መቀበያ አረንጓዴና አደይ አበባ ምስሎች ያሉበት ምንጣፎች አንጥፈው ሲቀበሉ እየታየ ነው። ለአደይ አበባ የሰጠነው ክብር እየሰፋ ነው። መዲናችንም ስሟ አዲስ አበባ ነው። አደይ አበባ ደግሞ በአዲስ ዘመን የሚበቅል አዲስ አበባ ነው። ስዕሉ ከመዲናችንም ስም ጋርም አብሮ ይሄዳል። በየቤቱም ለአዲስ ዓመት አደይ አበባ ከቄጠማዎች ጋር ተደርገው ይጎዘጎዛሉ። በተጨማሪም አደይ አበባዎች ሰብስቦ አንድ ላይ በማሰር በብርጭቆ ውሃ አድርጎ ለሁለት፣ ለሦስት ቀን የአዲሱ ዓመት የቤት ጌጥ ውበት እንዲሆኑም ይደረጋል። ከቱሪዝም ጋር የሚመጡ እንግዶችን የሚቀበል ጥሩ ወካይ ምልክት ነው በሚል የተመረጠው ነው።

በአርማው ላይ የአደይ አበባው አቀማመጥ ግማሽ ጐኑ ምሥራቅ አፍሪካ ላይ ሲሆን፣ ቀሪው ደግሞ አፍሪካን ተሻግሮ የሚያልፍ ነው። ይሄም የቱሪዝም ሀብታችንን ለተለያዩ ዓለማት፣ የመጐብኘት ፍላጐት ላላቸው ኢትዮጵያን መመርመር ለሚፈልጉ አካላት ሁሉ ሦስቱ ኮከቦች ከአፍሪካ ውጪ፣ የአበባዎች ዘለላዎች በሙሉ ወደ ውስጥ አንድ ነጥብ ስር የሚሰባሰቡ ናቸው። በመሀል ያለውም የአበባው ፍሬ ወይም እምብርት መነሻ የኢትዮጵያ የቱሪዝም መለያ The Land of Origin ላንድ ኦፍ ኦሪጅን (ምድረ ቀደምት) የሚለውን ይወክላል። አደይ አበባዋ ከዚህ ወካይ ምስል መካከል አንዷ ናት።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ዜጎች የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ መደላድል የፈጠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች

**መላኩ ኤርሴ**




በግንባታ ላይ የሚገኘው ቤቴል የግብርና ምርቶች መሸጫና ማከማቻ ማዕከል

የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲናዋ፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት ዋና መሥሪያ ቤት መገኛዋ አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስና ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ፣ ምቹ ለመሆን መሥራቷን አጠናክራ ቀጥላለች፤ ለእነዚህ አገልግሎቶች ብቁ የከተማ ቁመና እንዲኖራት ለማድረግ በብርቱ እየተጋች ትገኛለች።

በተለይ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ የግሉ ዘርፍ ከሚያደርጋቸው ግንባታዎች በተጨማሪ የከተማዋ አስተዳደር የከተማዋን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ለማሳለጥ የላቀ ትርጉም የተሰጣቸው የበርካታ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ማካሄዱን ተያይዞታል።የከተማ አስተዳደሩ ይህን የሚመራ የግዙፍ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት አቋቁሞም ነው ሥራውን እያካሄደ ያለው። ከተማዋ ከፕሮጀክቶቹ መካከልም ጥቂት የማይባሉትን አጠናቃ ለአገልግሎት አብቅታለች፤ አብዛኞቹን ደግሞ አጋምሳለች፤ አዳዲሶቹንም ጀምራ ግንባታቸውን እያጣደፈች ትገኛለች፡፡

ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ሥራ የገቡት ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገፅታ ከመቀየርና ውብ ከማድረግ ባለፈ ለነዋሪዎቿ ዘመናዊ እና ምቹ አገልግሎት እየሰጡም ይገኛሉ።ሌሎቹም ይህንኑ የሚከተሉ ይሆናሉ።

ፕሮጀክቶቹ ለነዋሪዎቿና እንግዶቿ ከሚሰጡት አገልግሎት ባለፈ፤ በፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ዜጎች የሥራ ዕድል ከፍተዋል።ከዚህም ባሻገር በጉልበት ሥራ ተቀጥረው የሚሠሩ ዜጎች የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፤ ወጣቶች በጉልበት ሥራ ተቀጥረው በሚሠሩባቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች የእለት ጉርሳቸውን ከማግኘት አልፈው በግንበኝነት፣ በፌሮ ሥራ፣ በአናፂነት፣ በግንባታ ማሽን አንቀሳቃሽነትና መሰል ሌሎች በርካታ የሥራ ዘርፎች ላይ የሙያ ባለቤት የሚሆኑበት እና የተሻለ ገቢ ማግኘት የሚችሉበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል።ይህም የፕሮጀክቶቹ ሌላው ሰው ተኮር ገፅታቸው ነው።

የዝግጅት ክፍላችንም በከተማዋ ተግባራዊ እየሆኑ ባሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በመዘዋወር ዜጎች በኮንስትራክሽን ሥራው ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ መረዳት ችሏል።በጉልበት ሥራ ተቀጥረው ከሚሠሩ የቀን ሠራተኞች መካከል ወጣት ደምሴ ዋቤ አንዱ ነው።ወጣት ደምሴ የግብርና ምርቶች ማከማቻ እና መሸጫ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ድርጅት ውስጥ የጉልበት ሠራተኛ ሆኖ ሠርቷል።አሁን ደግሞ በግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል የግንባታ ሥራዎች በተፈጠረለት እድል ተጠቅሞ በጠራቢነት እየሠራ በቀን 200 ብር እያገኘ መሆኑን ጠቁሟል።

“በዚህ ሳይት በቀን ሠራተኛነት ስሠራ በሙያ ተቀጥረው ለሚሠሩት ሰዎች ክፍያው ከፍ ያለ ስለሆነ አንድ ሙያ ማወቅ አለብኝ ብዬ በማሰብ የጠራቢነት ሥራ የሚሠሩ ሙያተኞች ረዳት ሆኜ በመሥራትና ሙያውን ለማወቅ ባለኝ ጉጉት በአጭር ጊዜ ውስጥ ልምድ መውሰድና ሥራውን በደንብ መሥራት ችያለሁ›› ሲል ወጣቱ ይገልጻል።የሙያ ባለቤት መሆን የቻልኩትም ሥራውን ቶሎ ለመማር ካለኝ ፍላጎት ባሻገር በዋናነት አብሬያቸው የምሠራቸው ሙያተኞችና የሥራው ተቆጣጣሪዎች ባደረጉልኝ የሙያ ድጋፍና ማበረታቻ ነው ይላል፡፡

ወጣት ደምሴ ቀደም ሲል በኮንትራክሽን ሥራዎች ድርጅት በቀን ሠራተኝነት ሲሠራ የፌሮ ሥራ ሙያተኛ በመሆን አገልግሏል።በዚህም በቀን 150 ብር ይከፈለው ነበር።አሁን ደግሞ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ባገኘው ልምድ በጠራቢነት የሙያ ባለቤት በመሆን በቀን የ200 ብር ተከፋይ መሆን ችሏል።

ሌሎች በርካታ ግለሰቦችም በተለያዩ የከተማዋ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመረጃ ሰብሳቢነት፣ በአናፂነት፣ በግንበኝነት እና በሌሎች የሙያ ዘርፎች ጥሩ የሚባል ልምድ መቅሰም መቻላቸውን እና በኑራቸውም ጥሩ መሻሻል እንዳመጡ ሀሳባቸውን አጋርተውናል፡፡

በግንባታ ፕሮጀክቱ በተፈጠረው የሥራ እድል የቀን ሠራተኞች የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችል የሙያ ሥልጠና ይሰጥ እንደሆን ለማወቅ በአቪድ ኮንስትራክሽን የኮልፌ ቀራኒዮ የግብርና ምርቶች መሸጫ እና ማከማቻ ማዕከል ግንባታ መሐንዲስ ኢንጂነር ሙሉጌታ ጠየቅናቸው።እሳቸው እንዳሉት፤በኮልፌ ቀራኒዮ ሳይት ለ33 ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል ተፈጥሯል።ለቋሚዎቹ ረዳት ሆነው ለሚሠሩ 35 ወጣቶች ተጨማሪ ጊዜያዊ የሥራ እድል ተፈጥሯል።በቀን ሠራተኝነት ደግሞ ለ330 ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሯል።

**ከተማዋ ከፕሮጀክቶቹ መካከልም ጥቂት የማይባሉትን አጠናቃ ለአገልግሎት አብቅታለች፤ አብዛኞቹን ደግሞ አጋምሳለች፤ አዳዲሶቹንም ጀምራ ግንባታቸውን እያጣደፈች ትገኛለች**

ከሥራ እድል ፈጠራው ጎን ለጎን በተለይም የቀን ሠራተኞች ሙያቸውን እንዲያሳድጉ እገዛ እየተደረገላቸው መሆኑን ይገልጻሉ።በዚህም እንደየሙያ ዘርፉ በደንብ የሚንቀሳቀሱ የጉልበት ሠራተኞችን ረዳት በማድረግና ሥልጠና በመስጠት ወደ ፌሮ፣ ግንበኛ፣ ማሽን ኦፕሬተርና ሌሎች ሙያዎች የማሳደግና ወደ ተለያዩ ሙያዎች የማሠማራት ተግባር እንደሚከናወን ኢንጂነር ሙሉጌታ ገልጸዋል፡፡

ሙያውን እንዲያሳድጉ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር የሥራ ባሕልን ለመቀየር በትኩረት እየተሠራ ነው የሚሉት ኢንጂነር ሙሉጌታ፤ ከዚህ ቀደም በዋናነት የተለመደው የሥራ ሰዓት ስምንት ሰዓት ነው።አቪድ ኮንትራክሽን ግን የግብርና ምርቶች ማከማቻ እና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ በቀን በፈረቃ እስከ 16 ሰዓት እያሠራ ነው።በዚህ ሂደት ውስጥ በፕሮጀክቱ ውስጥ እየሠሩ ያሉ ተቋራጮችም ሆኑ የቀን ሠራተኞች የሥራ ባሕላቸው እየተቀየረ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላት ፕሮጀክት አስተባባሪ መሐንዲስ ኢንጂነር ጉርሜሳ ረታ እንዳሉትም፤ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላት በከተማዋ በሦስት ቦታዎች እየተገነቡ ባሉ የግብርና ምርቶች መሸጫና ማከማቻ ማዕከላት የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ዜጎች በቀን ሠራተኝነት ከመሥራት ባሻገር ሙያቸውን እንዲያሳድጉ፣ እውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመጣ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው፡፡

ከቢሊዮን ብር በላይ በጀት የተያዘለት የትልቅ ማዕከል ግንባታ ለሀገር በቀል የኮንትራክሽን ድርጅት የተሰጠበት ዋነኛው ዓላማም የሀገር በቀል ድርጅቶችን አቅም ማሳደግ፣ በስሩ የሚሠሩ ሠራተኞችን የሙያም፣ የእውቀትም አቅም ለማሻሻል ነው ያሉት ኢንጂነር ጉርሜሳ፤ ሀገር በቀል ኮንትራክተሮችን አቅም ለማሳደግ በሚል የተላለፈው ውሳኔ ፍሬያማ መሆኑን ጠቅሰዋል።ሀገር በቀል ድርጅቶች ትላልቅ ፕሮጀክቶች የመገንባት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል ይላሉ፡፡

የውጭ ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ ከሥራቸው የሚሠሩ ንዑስ ተቋራጮችን ከራሳቸው ሀገር የማምጣት ልምድ እንደነበራቸው የሚጠቅሱት ኢንጂነር ጉርሜሳ፤ በዚህም ሀገር በቀል የግንባታ ተቋራጮች ተጎጂ ነበሩ ይላሉ። አንዳንድ የውጭ ተቋራጮች ሠራተኛም ጭምር ከውጭ ሀገራት አምጥተው ያሠራሉ።ይህም ሀገሪቱ ላይ ከሚያሳድረው ኢኮኖሚያዊ ጫና ባሻገር በቀጣይ አቅም ያላቸው ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እንዳይፈጠሩ የሚያደርግ ነው ነው ሲሉ ያብራራሉ። የግብርና ምርቶች መሸጫና ማከማቻ ማዕከላትን እየገነባ ያለው ተቋራጭ ግን በስሩ ሌሎች ሀገር በቀል ንዑስ ተቋራጮችን ቀጥሮ ለአነስተኛ ሀገር በቀል ተቋራጮችም አቅም እየፈጠረ፣ እርስ በርሳቸው እየተማማሩ፣ ቴክኖሎጂዎችን እያላመዱ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

እንደ ኢንጂነር ጉርሜሳ ማብራሪያ፤ ሀገር በቀል ድርጅቶች በቀጣይ እጅግ ግዙፍ ፕሮጀክቶችንም ለመገንባት የሚያስችል ደረጃ ላይ እየደረሱ ነው።ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያንን ቀጥሮ እያሠራ ነው።በዲዛይኑም፣ ፕሮጀክቱን በመምራትም፣ በግንባታም ኢትዮጵያውያን ናቸው እየሠሩ ያሉት።በመሆኑም በፕሮጀክቱ ግንባታ እየተሳተፉ ያሉ ሠራተኞችም እውቀትና ቴክኖሎጂዎችን እየቀሰሙ ነው።የማያውቁትን እንዲማማሩ፣ አቅም እንዲያሳድጉ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

ሠራተኞች ሙያቸውን እንዲያሳድጉ የሚደረገው ጥረት ከግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት ፕሮጀክት በተጨማሪ በሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች ውስጥም በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የፕሮጀክቶቹ ሥራ አስኪያጆች ገልጸዋል።

በዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ማስተዋል ኃይለክርስቶስ እንደተናገሩት፤ ድርጅታቸው በፕሮጀክቱ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ በትኩረት እየሠራ ነው።በቀን ሥራ የሚገቡ ሠራተኞች ወደ ሚያዘነብሉበት ሙያ እንዲያተኩሩ ይበረታታሉ።ከዚህም ባሻገር በየጊዜው ሙያቸውን እያሳደጉ እንዲሄዱ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል።አሁን ባሉበት ፕሮጀክት ላይ ተቀጣሪ ሆነው እየሠሩ ቢሆንም በቀጣይ የራሳቸውን ሥራ መሥራት እንዲችሉ እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አዲስ አረጋይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ባለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ የሥራ እድሎች ተፈጥረዋል።በ2013 ዓ.ም ለ2ሺ 016 ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሯል።በ2014 ደግሞ ለ2ሺ.836 ሰዎች በ2015 ደግሞ ከ4ሺ ለሚበልጡ ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።በአጠቃላይ ባለፉት ሦስት ዓመታት 8ሺ.380 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል።እነዚህ የሥራ እድሎች በተቋራጮቹ እና በአማካሪዎች የተፈጠሩ ሙያዊ እንዲሁም በመለስተኛ ደረጃ በማሽኖች ኦፕሬተርነት፣ በግንበኝነት፣ በለሳኝነት፣ በቀለም ቀቢነት፣ በፌራዮ፣ በጥበቃ፣ በፈታሽነት የሥራ መስኮች የተፈጠሩ ናቸው።

ከተጠቀሰው 8ሺ.380 የሥራ ዕድል በተጨማሪ በግንባታ አካባቢዎች ኢ-መደበኛ የሥራ እድሎችም ተፈጥረዋል።የመኪና ማቆሚያ የፓርኪንግ አገልግሎቶችን በመስጠት፣ በተላላኪነት፣ በሊስትሮነት፣ በፕሮጀክት አካባቢዎች ተጠግተው የሚሠሩ በርካቶች መኖራቸውንም ጠቅሰዋል።ፕሮጀክቶቹ ሳይመረቁ በሂደት ላይ እያሉ እንኳ የፈጠሩት የሥራ እድል ከፍተኛ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አዲስ፤ ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ደግሞ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል የመፍጠር አቅም እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የሥራ እድል ከመፍጠራቸው ባሻገር በፕሮጀክቱ ተሳታፊ የሆኑት በርካቶች ከቀን ሠራተኝነት ተነስተው የሙያ ባለቤት መሆናቸውን አቶ አዲስም ገልጸዋል።በርካታ የቀን ሠራተኞች ከአሠሪዎቻቸው እውቀት እየቀሰሙ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የቀሰሙትን እውቀት ተጠቅመው ከቀን ሠራተኝነት ወደ አናጺነት፣ ፌራዮነት፣ ለሳኝነት ተሸጋግረው የተሻለ ገቢ ማግኘት የቻሉ ዜጎች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።ሠራተኞቹ ሙያቸውን እንዲያሳድጉ አሠሪዎቻቸው ተገቢውን ክትትል እንዲያደርጉ ጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል እንደሚያደርግም ጠቁመዋል፡፡

የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ለማድረግ ተቀጥረው በሚሠሩት ዜጎች ላይ ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ፕሮጀክቱ ቦታ ድረስ በመምጣት ፕሮጀክቶቹን እንዲጎበኙ እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ



## ትንሳዔን በመተሳሰብና በመረዳዳት መንፈስ!

የትንሳኤ በዓል በመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ነገ ይከበራል። ኢትዮጵያውያን የመረዳዳት ባህል አለን፣ የተቸገረን መደገፍና የታመመን የመጎብኘትም ልምድ አለን፣ ለበጎ ሥራ ደግሞ በቀዳሚነት የሚያስፈልገው መልካም ልብ ብቻ ሲሆን በጎነት ለራስ ጤንነት የሚሰጥ፤ በፈጣሪ ዘንድም ውድ ዋጋ ያለው ክቡር ተግባር ነው። የትንሳኤ በዓልም ይህ አኩሪ ባሕላችን ጎልቶ ከሚወጣባቸው አጋጣሚዎች አንዱና ትልቁ ነው።

በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውን ይህን በዓል በማስመልከትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ባለፉት ቀናት ለአቅመ ደካሞች፣ የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብር አካሂደዋል። የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤም የፋሲካ እና የዒድ አልፈጥር በዓላትን ምክንያት በማድረግ ማዕድ አጋርተዋል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ አቅም የሌላቸውን በመርዳት፣ያለው ለሌለው በማካፈል መንፈስ በዓሉን ሊያከብረው እንደሚገባም በማዕድ ማጋራት መርሐ ግብሩ ወቅት ተናግረዋል።

ሕዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን በሚያከብርበት ወቅት በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተፈናቅለው ለችግር ለተጋለጡ ወገኖችን በማሰብና ድጋፍ በማድረግ ከጎናቸው ሊቆም ይገባል። ከአጠገቡ ያሉ አቅም ያነሳቸውና ኑሮ የከበዳቸው ጎረቤቶቹን እንዲጠይቅና እንዲያግዝም ጥሪ ቀርቧል።

እውነት ነው ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው እንደሚባለው ሁሉም የአቅሙን ያህል የተቸገረን ቢጎዳ የብዙዎች ችግር ይቃለላል፤ ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነትም ያብባል።በተለይም ወጣቶች የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ ለተቸገሩ ማዕድ በማጋራትና በመሳሰሉት በጎ ተግባራት በዓሉን ሊያከብሩ ይገባል። በአንዳንድ አካባቢዎች በነበረው የሰላም ዕጦት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖች በችግር ውስጥ እንደመሆናቸው፣ እነዚህን ወገኖችን በዚህ ታላቅ በዓል በመመገብ፣ በማጠጣት እና በማልበስ ከጎናቸው ልንቆም ይገባል። ይህንንም በማድረግ የትንሳዔን ዓላማ ማሳካትና በሰማይም በምድርም መልካም ዋጋ ማግኘት ይቻላል።

በክርስቶስ ትንሳኤ ሁሉም ሰው ክፋትን ከልቡ በማስወገድ በክርስትና ሕይወቱ ውስጥ ክርስቶስን መምሰል አለበት። ከተበላሸ ሕይወት በመጽዳት የክርስቶስን አብነት መከተልና የሰላም አባት መሆን ያስፈልጋል።

እንደ ክርስትና ተከታዮች እምነት ትንሳዔ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ታዛዥነትን ንጽሕናን ለሰዎች መስዋዕት መሆንን በተግባር የገለጠበት ትልቅ በዓል ነው።ስለሆነም ምዕመኑ የትንሳኤ በዓልን በመተሳሰብና በፍቅር ሊያከብርና የተቸገሩና አስታዋሽ ያጡትን ማሰብና መርዳት ይጠበቅበታል። ወንጌልን ከቃል ባለፈ በተግባር በማሳየትም እርስ በርስ ተከባብሮና ተረዳድቶ በፍቅርና በሰላም መኖር ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው መከራና ስቃይ ለሁሉም በመሆኑ የትንሳኤ በዓል ደጋፊ የሚያሻቸውን በማሰብና በመርዳት ሊከበር ይገባል። ኢየሱስ ክርስቶስ በኑሮው ገልጦ ለሐዋርያት ካስተማረው ትምህርት አንደኛው ለራስ ሳይሆን ለሌሎች መኖርን ነው። በመሆኑም በዓሉ ሲከብር እርስ በእርስ መረዳዳትና በመተሳሰብ ማሳለፍ ይገባል!

ትንሳኤ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሠው ልጆች ሲል ብዙ መከራ ተቀብሎ ይቅርታ እና ፍቅርን ያስተማረበት በዓል በመሆኑ ምዕመናን በዚህ ተምሳሌት መተሳሰብ እና በጎ ተግባርን ማጠናከር ይገባቸዋል። ትንሳኤ ለሰው ልጆች ሁሉ ከመከራ የመነሳት የተስፋ ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ እኛም አሁን የገጠሙንን የውስጥና የውጭ ችግሮች ተቋቁመን ፈተናዎችን በፅናት ለመሻገር መነሳት ይኖርብናል። እንደ ሀገር የገጠሙንን ፈተናዎች ለማለፍ ትለቅ አቅምና ምሳሌ ይሆነናል ።

ትንሳዔ አሁን ላይ እንደሃገር የገጠሙንን ፈተናዎች አልፈን የምንሻገር እንድንሆን ተስፋን የምንሰንቅበት በዓል ነው። በሀገራችን አልፎ አልፎ እያየን ያለነው ጥላቻ እና መገፋፋት የኢትዮጵያውን መለያ አይደለምና በትንሣዔ በዓል ፍቅርን እና አንድነትን በመስበክ ጥላቻንና መከፋፈልን ልናስወግድ ይገባናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# የመረዳዳት ባህል ከበዓላት ሰሞን እንዲሻገር…

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

በበዓላት ሰሞን በመገናኛ ብዙኃን ከምንሰማቸው ወሬዎች መካከል «… ሕዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ ሊሆን ይገባል … ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር አቅም የሌላቸው ወገኖችን በመርዳት ሊሆን ይገባል …» የሚሉት አገላለፆች ይገኙበታል።ከቀናት በኋላ የሚከበሩትን የትንሳኤ (ፋሲካ) እና የኢድ-አልፈጥር በዓላትን ምክንያት በማድረግ እነዚህን ጥሪዎች/ምክሮች መስማታችን አይቀርም።

ዘንድሮ በኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያኑ የዐቢይ ፆምን፣ ሕዝበ ሙስሊሙ ደግሞ የረመዳን ፆምን በተመሳሳይ ወቅት ፆመዋል። ታዲያ እነዚህ ዐበይት የፆም ጊዜያት በአማኞች ዘንድ ልዩ ስፍራና ክብር የሚሰጣቸው መንፈሳዊ ተግባራት ናቸው።አማኞች የሥጋ ምኞታቸውን ቀንሰው ስለትናንት፣ ስለዛሬና ነገ በፆም፣ በፀሎትና በስግደት ፈጣሪያቸውን በሚማጸኑባቸውና በሃይማኖቶቹ አስተምህሮዎች የሚታዘዙ ሌሎች ተግባራትንም በሚፈፅሙባቸው በእነዚህ የፆም ወራት፤ ሕዝቡ የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት እንዲሁም ለሀገር ሰላምና እድገት የሚጠቅሙ መልካም ተግባራትን በማከናወን ማሳለፍ እንደሚገባው ቀደም ብለው አሳስበዋል።

እርግጥ ነው፣ ሕዝበ ክርስቲያኑም ይሁን ሙስሊሙ በዓላትን ሲያከብሩ የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት እንዳይዘነጉ መንገር ተገቢና አስፈላጊ ምክር ነው። መረዳዳት የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነና የእርስ በእርስ ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን አጠንክሮ የኖረ ተግባር ነው።መረዳዳት ባይኖር ኖሮ አሁናዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አሁን ካለው የተለየ ይሆን ነበር።

ታዲያ እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ነጥብ የማኅበረሰቡ የመረዳዳት ባህል ከበዓላት ሰሞን መሻገር እንዳለበት ማስታወስና ይህ እንዲሳካ ለሚስችሉ ተግባራት ትኩረት መስጠት ሊሆን ይገባል።በበዓላት ወቀት ሕዝቡ መረዳዳት እንዳለበት ከማስታወስ በተጨማሪ ከበዓላት ውጭ ባለው ጊዜም የመረዳዳት ተግባሩን አጠንክሮ መቀጠል እንዳለበት ማስገንዘብም ተገቢ ይሆናል። ይህ የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው የመረዳዳት ባህል በበዓላት ሰሞን ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ለማድረግ የመረዳዳት ባሕልን ከአንድ ሰሞን ኹነት የተሻገረ ተግባር አድርጎ መመልከት ያስፈልጋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአንድ ወቅት ‹‹ያለንን ማካፈል የባሕላችን አንድ አካል ሆኖ የዘለቀ ዕሴት ነው። እጦት ለገጠማቸው ማካፈል አሥር እጥፍ መልሶ የሚያስሸልም ተግባር ነው። ከበዓል ሰሞን ባሻገር በቀጣይነት የመስጠት ተግባራችንን ማስፋት በእኩልነት ተደራሽ የሆነ ማኅበረሰብን ለመፍጠር ከሚያስችሉ ግብዓቶች አንዱ ነው። በተለያየ የኑሮ ደረጃ የምንገኝ ሁሉ ማዕድ ማጋራትን እንዲያሰፉ አበረታታለሁ›› የሚል መልዕክት አስተላልፈው ነበር። አዎ፣ የመረዳዳት ባሕልን ከአንድ ሰሞን ድርጊት አሻግሮ ዘላቂ ለማድረግ ‹‹ያለንን የማካፈል›› መርሕን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።ያለንን በማካፈል መርሕ የምናምን ከሆነ የተቸገሩ ወገኖችን ለማገዝ የበዓላትን ሰሞን መጠበቅ አያስፈልገንም።ያለውን በማካፈል መርሕ የሚያምን ሰው መተጋገዝ ጊዜና ቦታ የማይገድበው በጎ ተግባር እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል።

ዛሬ በሌሎች የተረዳና የተደገፈ ነገ ሌሎችን መርዳቱና መደገፉ አይቀርም፤ዛሬ ያለውን ያካፈለ ሰው በእርሱ ማካፈል የሌሎች ችግር እንዲቃለል ከማድረጉ በተጨማሪ ሌሎችም ያላቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ትምህርት ይሰጣል።ያለንን የማካፈል መርሕ እንዲህ ዓይነት አካሄዶችን በመገንባት መረዳዳትን ዘላቂ ለማድረግ ያስችላል።

የመረዳዳት ባሕል ትርጉም የሚኖረውም ውስን ጊዜያት እየተጠበቁ በሚከናወኑ የመተጋገዝ ሥራዎች ሳይሆን፣ ቀጣይ በሆኑ የመደጋገፍ ተግባራት ነው።ዘላቂ የሆነና ያለንን በማካፈል መርሕ ላይ የተመሠረተ የመረዳዳት ተግባር ወንድማማችነትን/እህትማማችነትን ያጎለብታል፤መተማመንንና መከባበርን ያዳብራል፤በጋራ ለማደግ ጠንካራ መሠረት ይሆናል።እነዚህ እሴቶች ለሀገር ሰላም ትልቅ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ።በአጠቃላይ ዘላቂ የሆነ የመረዳዳት ባሕልና ተግባር በመተማመንና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ሀገር እንዲኖር ትልቅ ሚና ይጫወታል።

**መረዳዳት የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነና የእርስ በእርስ ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን አጠንክሮ የኖረ ተግባር ነው። መረዳዳት ባይኖር ኖሮ አሁናዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አሁን ካለው የተለየ ይሆን ነበር**

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን በበርካታ ችግሮች ውስጥ ይገኛሉ።የሰላም እጦት ያስከተላቸው ምስቅልቅሎች፣ የዋጋ ንረት፣ የተፈጥሮ አደጋዎችና ሌሎች ችግሮች የመረዳዳትን አስፈላጊነት በእጅጉ ከፍ ያደርጉታል።የዋጋ ንረት አልቀመስ ባለባቸው የዘወትር ቀናትስ ያለው የመረዳዳት ባሕላችን እንዴት ነው? ‹‹እኔ በልቼ፣ ወገኔ ፆም ማደር የለበትም›› ብለን እየተረዳዳን ነው? እንደሚታወቀው ወቅታዊው የኑሮ ውድነት የኅብረተሰቡን የመኖር አቅም በእጅጉ እየፈተነው ነው።የዋጋ ንረት በየጊዜው ማሻቀብ እንጂ ዝቅ ማለት አልሆነለትም።የዋጋ ንረቱ እንኳን ቅናሽ ማሳየት ይቅርና ባለበት መቀጠልም አልቻለም።አሁን ያለው የዋጋ ንረት ከእስካሁኑ ሁሉ የከፋ እንደሆነ እየታየ ነው፤ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎች ካልተወሰዱ ነገም ከዛሬውም የባሰ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።አልፎ አልፎም ቢሆን በመገናኛ ብዙኃን የሚደመጡ የነዋሪዎች አስተያየቶችና አቤቱታዎች በምሬቶች የተሞሉ አሳዛኝና አሳሳቢ ቅሬታዎች ናቸው።ስለሆነም የኑሮ ውድነቱ የሚፈጥረውን ጫና ለመቋቋም ማኅበራዊ መስተጋብሮቻችን በማጠናከር መልካም እሴቶችን ለክፉ ጊዜ ማለፊያነት መጠቀም ይገባል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የምትገኝ በመሆኗ የመረዳዳት ባህል ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አስፈላጊ ነው።‹‹ሀገር ማለት ሰው ነው›› በሚባለው ብሂል ከተግባባን ሰው የሌለበት ኑሮ ደግሞ ከሀገር እንደሚያጎድል እንስማማለን።ስለሆነም ገንዘብ ያለው ሲበላና ሲጠጣ፤ ገንዘብ የሌለው ደግሞ እየተራበና እየተጠማ እንደሆነ ማስታወስ አለበት።ብዙ ወገኖቹ እየተቸገሩ ብቻውን በልቶ ብቻውን እየኖረ ያለ ሰው ‹‹ሀገር ማለት ሰው ነው›› ብሎ ቢናገር ንግግሩ ከቀልድና ሹፈት የዘለለ ትርጉም አይኖረውም።የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነውን የመረዳዳት ባሕል ከበዓል ሰሞን ቀናት በማሻገርና ዘላቂ በማድረግ የመረዳዳት ባሕላችን ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ያስፈልጋል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# አዛውንቷ ሎተሪ አዟሪ

ሠሳማዊት ውቤ

ተወልደው ያደጉት ‹‹ዶሮ ማነቂያ›› ከተባለ ሰፈር ነው። ዛሬም ኑሯቸው በዚሁ መንደር ቀጥሏል። የ73 ዓመት አዛውንት ቢሆኑም ለእርጅና እጅ አልሠጡም።ቤት መቀመጥ፣ ከቤተክርስቲያን ደጃፍ እየለመኑ መኖርን አልሞከሩም።አቅም ጉልበት ሲደክም አማራጭ መፈለግ ያለ ነው።እሳቸው ግን እንዲህ መሆኑን አይፈቅዱም፡፡

እማማ ፀሐይ ኃይሉ መቼም ቢሆን በሰው እጅ ወድቀው ተጧሪ መሆንን አይሹም። ራስን ችሎ መንቀሳቀስን በነፃነት ያዩታል። ወዲያ ወዲህ ብሎ አየር ማግኘቱ ለእሳቸው እንደ ስፖርት ነው።ጤናን እንደ መንከባከብ ይቆጥሩታል።እየተዘዋወሩ በስተእርጅና ሎተሪ ሸጦ ማደር እንጀራቸው ሆኗል።ሎተሪን ራሳቸውን በመደጎም ሕይወታቸውን ይመሩበታል።ቀልጣፋነታቸውን የወረሱት ተወልደው ካደጉበት አካባቢ መሆኑን ይናገራሉ።ቀጭን ሰውነታቸው ደግሞ ሮጦ ለማደር አግዟቸዋል፡፡

ለየዕለት ሥራቸው ሥፍራን ይመርጣሉ።መገናኛ አካባቢ ግርግርና ኪስ ዳበሳ በመኖሩ ምርጫቸው አይደለም። አራት ኪሎ ፤ፒያሳ፤ ስድስት ኪሎ፤ቴዎድሮስ አደባባይ ፤ብሔራዊ ቲያትር ፤መርካቶና ተክለ ሃይማኖት ከሎተሪያቸው ጋር አይታጡም።

የሎተሪ ሽያጭ ጊዜ አይሰጥም።በእጅ ያለን ሸጠው ካልጨረሱ ለኪሳራ ይጥላል።አንዳንዴ እማማ ፀሐይ በዚህ ገጠመኝ ያልፋሉ።ሎተሪ በመጨረሻው ምሽት ሊወጣ ጥቂት ሰዓታት ሲቀረው በእጃቸው ካሉ የሎተሪ ቅጠሎች ጋር ይፋጠጣሉ።ይህኔ ቀሪውን ለመሸጥ መላ አያጡም፡፡

‹‹ከማለዳ ጀምሬ ቀኑን ሙሉ ያዞርኳቸው ሎተሪዎች ሊያከስሩኝ ነው›› እያሉ በልመና መንገደኞችን ይማጸናሉ።ብዙዎች አይጨክኑባቸውም።የቀሩትን ሰብስበው ይገዟቸዋል።እንዲህ አይነቶቹ አጋጣሚዎች ሥራቸውን መልካም አድርጎላቸው እስከዛሬ ያለ ኪሳራ ዘልቀዋል።

እናት ፀሐይ በዶሮ ማነቂያ ተወልደው ይደጉ እንጂ እናታቸው ገና በ10 ዓመት ዕድሜያቸው በመመንኮሳቸው ወደሚኖሩበት ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሊሄዱ ግድ ነበር።እስከ አሥር ዓመታቸው በአባታቸው እጅ ያደጉት ልጅ እናታቸው ከአባታቸው ተለያይተው ለመመንኮስ የበቁበትን ምስጢር ዛሬም ድረስ አያውቁትም።

ፀሐይ ለአንድ ዓመት በደብረሊባኖስ በኖሩ ጊዜ በ11ዓመት ዕድሜያቸው በአንድ ሰው ተጠልፈው ይወሰዳሉ።የዛኔ አስራ አንድ ዓመታቸው ነበር።ጠላፊው ያለ ፍላጎትና ፍቃዳቸው በር ቆልፎ ሚስት አድርጎ ያስቀምጣቸዋል።ይህን የሰሙ ቤተሰቦቻቸው በድርጊቱ በመበሳጨት ከሰውዬው እጅ ሊያላቅቋቸው ብዙ ጥረዋል።ቢሆንም ሰውዬው ባለጊዜና ባለ ገንዘብ ነበርና ሳይሳካላቸው ቀርቶ ሴት ልጅ ያረግዛሉ፡፡

በወቅቱ ሰውነታቸውም ሆነ ዕድሜያቸው ለአቅመ መውለድ ባለመድረሱ በሰላም መገላገል አልቻሉም።ልጃቸው ሆዳቸው ውስጥ ይሞታል።እሳቸውም ብዙ ደም ይፈሳቸውና ለወራት ካልጋ ይውላሉ።በሕመም ተሰቃይተውም ከሞት ይተርፋሉ።

እንዲያውም ሆኖ ሰውዬው በቀላሉ የሚለቃቸው አልነበረም።መልሶ ቤቱ ወሰዳቸው ያለፍቃዳቸውም ሚስት እንዲሆኑ አስገደዳቸው።ቤተሰቦቻቸው ተሰባስበው በሃይማኖት አባቶችና ተሰሚነት ባላቸው የአገር ሽማገሌዎች አስለመኑት።‹‹በጄ›› አላለም።ረግመው እንዳስረገሙት አወቀ።ምርጫ አልነበረውም ሚስት ያደረጋቸውን ፀሐይን ለቀቃቸው።

ከዚህ በኋላ ቀድሞውኑም ብቻቸውን ያሳደጓቸው አባታቸው ቀድሞ ይኖሩበት ወደነበረና ወደ ተወለዱበት ዶሮ ማነቂያ አመጧቸው። ከሳቸው ጋር ብዙ ከቆዩ በኋላ እንደፊቱ ተገደው ሳይሆን ወድደውና ፈቅደው ባል በማግባት ወደ መርካቶ አቀኑ።መርካቶ ከባለቤታቸው ጋር አንዲት ልጅ በማፍራት ለረጅም ጊዜ በትዳር ቆዩ።ልጃቸው በተራዋ ሴት ልጅ ወልዳ ወግ አሳየቻቸው።ይህ ደስታቸው ግን ብዙ አልዘለቀም፡ አንድዬ ልጃቸውን በሞት ተነጠቁ።



‹‹ሳይደግስ አይጣላም ›› እንዲሉ እሷ ስታርፍ የሦስት ዓመት ሕጻን የነበረችውን የልጅ ልጃቸውን አሳደጉ።ዛሬ ደግሞ ዘራቸውን አብዝታ ቅድመ አያት ሆነዋል።ዛሬም ግን ፀሐይ ከብቸኝነት ጋር ናቸው።የልጅ ልጃቸው ከአባቷ ወገኖች ጋር በማደጓ ልጆቿ ጭምር አጠገባቸው የሉም፡፡

‹‹ብቻዬን ነው የምኖረው ጧሪም ቀባሪኝ የለኝም››የሚሉት እናት ባለቤታቸውም ሆነ አባታቸው ከሞቱ በኋላ ወደ ተወለዱበት ዶሮ ማነቂያ ተመልሰው አባታቸው ይኖሩበት በነበረ የቀበሌ ቤት እየኖሩ ይገኛሉ።በየወሩም 10 ብር የወር ኪራይ ይከፍላሉ።

አኗኗራቸው ከመንደሩ ነዋሪዎች በእጅጉ የተለየ እና የተገላቢጦሽ ነው።እሳቸው ጿሚ ቆራቢ፣ ከብዙ ዓለማዊ ድርጊቶች የተቆጠቡ ናቸው።ዶሮ ማነቂያ ደግሞ የበግም፤ የፍየሉ፣ የበሬ ሥጋ ታጥቶ አያውቅም።ቀን ከሌት ሥጋ ይቆረጥበታል።ከካቲካላ ጀምሮ እስከተፈለገው መጠጥ ማወራረጃ አይጠፋም። ብዙዎቹ የዶሮ ማነቂያ ነዋሪዎች ዛሬ የሥራ መስካቸውን ለውጠዋል። ቀደም ባሉት ዓመታት ትልቅ ካፒታል ከሚጠይቀው ሥጋ ቤት ውጪ በመጠጦች ሽያጭና በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ ነበሩ፡፡

የ73 ዓመቷ እናት ፀሐይ የተወለዱበትና የሚኖሩበት ዶሮ ማነቂያ ዛሬም እንደ ድሮው ከበርቻቻ አልተለየውም።እንደ ፊቱ አይብዛ እንጂ አሁንም በቀደመው ሕይወት የሚተዳደሩ አይጠፉም።መንደሩ ሌብነቱ፤ ማጭበርበሩ፣ዝሙቱ፤ ስድቡ እንደበፊቱ ሳይለየው አብሮት እየኖረ መሆኑን እማማ ፀሐይ ይናገራሉ፡፡

እማማ ፀሐይ በሌቦች ሁለት ሶስቴ ተጎድተዋል። ቢሆንም በመጨረሻ እንደተሰረቁት ዓይነት ስርቆት የከፋ አልነበረም።ሰርክ ቤተክርስቲያን የሚሄዱት ገና ጨለማው ሳይገፍ ማልደው ነው።ይህን ደግሞ ድፍን የዶሮ ማነቂያ ነዋሪ ያውቀዋል።እናም አንድ ማለዳ እነዚህ ውስጥ አዋቂዎች እማማ ፀሐይን ጉድ ሰሯቸው።“ከቤተክርስቲያን ስመለስ በሬ ወለል ብሎ ተከፍቷል ትልቁ የልብስ ሣጥኔና ሌሎች ዕቃዎቼ በመወሰዳቸው አናውን ነበር ያገኘሁት” ሲሉ ያስታውሱታል።ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ የበር ቁልፋቸው ተጠምዝዞ መዘረፋቸውን ቢናገሩም ሌቦቹ ሊያዝኑላቸው አልቻሉም።ከዚህ በኋላ ኑሮ ከበዳቸው።አቅማቸው ተፈተነ። በቀበሌ ምሳ እንዲፈቀድላቸው ምክንያት ከሆነው አንዱም ይሄው ችግር ነበር፡፡

በመንደሩ በሚስተዋሉ እኩይ ሥራዎች ፍፁም ተሳትፈው የማያውቁት እማማ ፀሐይ ተወልጄ አደኩበት ብለው አያማርሩትም።የእዛ መንደር ሕይወት ከእርሳቸውና ከባሕርያቸው ጋር የማይሄድ ቢሆንም እንደማይጠሉት ግን ይናገራሉ።በብዙዎቹ፤ በተለይም ከገጠር እየመጡ በሴት አዳሪነት በሚሰማሩበት ታዳጊዎች ሕይወት ሁሌም ያዝናሉ፣ እንባ አውጥተውም ያለቅሳሉ።

ወደ ደጃ ሰላም ሲሄዱ ፈጣሪ የተሻለ ኑሮ እንዲሰጣቸው እንደሚፀልዩላቸውም ይናገራሉ።ፀሐይ ዛሬ ወደሚሠሩት የሎተሪ ማዞር ሥራ ከመግባታቸው በፊት ይሠሩት የነበረም ሥራ በዚሁ ሁሌ በሚማፀኑት ደጃ ሰላም ዙሪያ ላይ የተመሠረተ ነበር። ለብዙ ዓመታት በጧፍ ሽያጭ ተሰማርተው ቆይተዋል።ከዓመት በፊት ግን በቤተክርስቲያን ደጃፍ ጧፍ በመሸጥ የሚተዳደረው ሰው ቁጥር ተበራከተ።ድሆችን መርዳት ዓላማዋ ያደረገችው ቤተክርስቲያን ከኑሮ ውድነቱ በተያያዘ በሚያገኙት ጥቂት ትርፍ ይቋቋሙታል በሚል ነፍሰ ጡርና ሕፃናት ልጆች ያሏቸው ሴቶች ለስለት የገባውን ጧፍ እየወሰዱ እንዲሸጡና ትርፉን እንዲወስዱ ፈቀደች፡፡

ልጅ በጀርባቸው ያዘሉና ሁለት ሦስት ልጆች የሚጎትቱ ሴቶች በሙሉ ግር ብለው መጥተው በጧፍ ንግድ ተሰማሩ።ቦታ ጠፋ።አስፋልት መሐል ሲገቡ ፖሊስና ደንብ አስከባሪ ማስነሳት ጀመረ።በዚህ ላይ ጧፍ ተወደደ።ፀሐይ 75 ሳንቲም ገዝተው አንድ ብር በመሸጥ ያገኙዋት የነበረችውን የ25 ሳንቲም ትርፍ መጠኑ ሳይጨምር ዋጋው አምስት ብር ገባ፡፡

በተወደደው ጧፍ ምክንያት ገበያ በመጥፋቱ ዕድሉን ጠበበ።እንዲህ የሆነው ጧፏ ከቤተክርስቲያን በሦስት ከሀምሳ በመውጣቷ ምክንያት ነበር።ይሄን ቢችሉትና የእሳቸው ትርፍ ከፍ ቢልም ተቀምጠው ጧፍ የሚሸጡበትን ቦታ በቀላሉ ማግኘት አልቻሉም።ሻጮቹ በመበራከታቸው ቦታቸው እየተያዘባቸው በብርቱ ሲቸገሩ ቆዩ።‹‹በስተመጨረሻ ለምን አልተውላቸውም ብዬ ጧፍ ሽያጬን ተውኩት›› የሚሉት እናት እንዳወጉን ታዲያ ከእጅ ወደ አፍ የሆነችው ጥቂት ሳንቲም በመቋረጧና ከተፈፀመባቸው ዘረፋ ጋር ተዳምሮ ብርቱ ችግር ሲፈትናቸው ቆየ።የሚኖሩበት ቀበሌ በደሀ ደሀ መልምሎ ምሳ ባያስፈቅድላቸው ኖሮ ዛሬን በሕይወት የመቆየታቸው ነገር ያጠራጥራል፡፡

‹‹ጧፍ ንግዱን ከተውኩ በኋላ ብቻዬን ቁጭ ብዬ ምን ሠርቼ በመኖር ቀሪ ሕይወቴን ልገፋ እንደምችል አሰብኩ።ፈጣሪዬንም በፀሎት ጠየቅኩ›› ይላሉ።በዚህ መሐል ሰው ሎተሪ ሲሸጥ ያያሉ።ሥራው የወንድና የሴት ነው፤ የአረጋውያን ነው የወጣቶች አይልም።

‹‹እኔስ ታዲያ ለምን ሎተሪ አላዞርም›› በማለት ፈጣሪያቸውን ጠየቁ።ፀሎታቸው ተሰማ።ሎተሪ የማዞር ሥራውን ጀመሩት።ፀሐይ ወደ ሎተሪ ሥራው የገቡት የዛሬ ዓመት መሆኑን ይናገራሉ።ከዛ በፊት ግን በቤተክርስቲያን ደጃፍ ተቀምጠው ጧፍ በመሸጥ እየተዳደሩ ረጅም ጊዜ ሕይወታቸውን ሲገፉ ቆይተዋል፡፡

‹‹ሰው ኑሮውን የሚገፋው በብዙ መልኩ ነው።እኔ ደግሞ ቀሪ ሕይወቴን ሎተሪ በማዞር እንድገፋ አማኑኤል ፈቅዶልኛል።ስለዚህ ሥራውን በፀጋ ተቀብየዋለሁ።ደስ ብሎኝ ነው የምሠራው›› ይላሉ።እሳቸው እንዳወጉን ሥራውን ለመጀመር ግር አላላቸውም።ብሔራዊ ሎተሪ እሳቸው የሚኖሩበት ዶሮ ማነቂያ ፒያሳ ውስጥ እንደሚገኝ አሳምረው ያውቁ ነበር። ከፈጣሪያቸው ፈቃዱን እንዳገኙ ፈጥነው ወደዚያው አመሩ።

‹‹ሠራተኞቹ በጣም ጥሩዎች ናቸው።ሎተሪ ከነሱ እየወሰድኩ ለመሸጥ ማሰቤን ስነግራቸው በጥሩ ሁኔታ አስተናገዱኝ›› ይላሉ።እንደውም እንዲጠነክሩና ጎብዘው ሥራቸውን እንዲሠሩ ‹‹አይዞሽ›› እያሉ አበረታቷቸው።ሎተሪ እንዴት እንደሚታይ፤መቼ እንደሚወጣና እስከመቼ እንደሚቆይ ማወቅ የሚያስችላቸውን ግንዛቤም በስልጠና አስጨብጠዋቸዋል፡፡

ወደ ሥራው ከገቡ በኋላም ከሰዎች የሚታዘቧቸውን ለሥራው እንቅፋት የሆኑ አንዳንድ ትዝብቶችን ሲነግሯቸው ዝም ብለው ሥራቸውን እንዲሠሩ፤ ቦታ እንዳይሰጧቸውና በሥራው እንዲገፉበት መክረዋቸዋል።ሎተሪው በወጣ ማግስት ማውጫ ይሰጧቸዋል።በዕድሜ ጫና ዓይናቸው የደከመው እናት ሳይማሩ ቁጥሮችን እንዲለዩ የገለፀላቸውን አምላክ ያመሰግናሉ።

ከብሔራዊ ሎተሪ ያገኙትን ግንዛቤ መሠረት እያደረጉ የተወሰኑትን ደንበኞች የወጣ ሎተሪ ዕጣ እያመሳሰሉ ያያሉ።ብዙዎች ግን ማውጫውን ተቀብለዋቸው ራሳቸው የሚያስተያዩበት አጋጣሚ ስላለ እንደማይቸገሩ ይናገራሉ። ብሔራዊ ሎተሪ ብቻ ሳይሆን ደንበኞቻቸውም ጭምር ያበረታቷቸዋል።

ሰው በዚህ ዕድሜ ቀርቶ ገና ጉልበቱ ሳይደክም በወጣትነቱ ጭምር ከሥራ ራሱን አግሎ ሲለምን በሚስተዋልበት ከተማ እርሶ ሎተሪ መሸጥዎት የሚበረታታና ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው እያለ ያበረታታቸዋል።‹‹የ10 ብር ሎተሪ ገዝቶ 100 ብር ቲፕ(ጉርሻ) የሚሰጠኝ ሁሉ አለ›› ሲሉም አውግተውናል።አንድ ሊገዛ የነበረው አምስት ወይም አራት የሚይዘውን በሙሉ የሚገዛቸውም አይጠፉም።እሳቸው ሎተሪ ሳይሸጥላቸው ቀርቶ፣ የሚወጣበት ቀን ደርሶባቸው በፍፁም ከስረው አያውቁም። ማንነታቸውን በማየት ብቻ ሎተሪ የመግዛት ፍላጎት የሚያድርበትና የሚያበረታታቸው ደንበኛ ብዙ ነው።

ሁሌም ለእማማ ፀሐይ ጉርሻ (ቲፕ) የሚሰጣቸው ሞልቷል። ብዙ ሎተሪ የሚገዙ ደንበኞችም አሏቸው። ‹‹ያያቸው ሁሉ ያወድስና ያጀግናቸዋል። በዚህ ሎተሪ በማዞር ሕይወታቸውን መግፋት ከጀመሩ በመጋቢት ላይ ድፍን ዓመታቸውን አስቆጥረዋል ።ከነደ ብርቱዋ ፣ አይበገሬ እማማ ፀሐይ ኃይሉ።

ኢኮኖሚ

ስኬት

# ስኬታማው የወተት ከብት እርባታ ጉዞ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ግብርና የኢትዮጵያውያን ሕልውና ነው፤ አርሶና አርብቶ አደሩ ደግሞ ሕልውናን የሚያረጋግጥ የዘርፉ ቀኝ እጅ። ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብርናው ዘርፍ ተሰማርቶ ሕይወቱን የሚመራ ከመሆኑም በላይ ለከተሜው ፍላጎት መሟላት የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። በዚህ ምክንያት በግብርናው ሥራ ላይ ከተሠማራ ዜጋ ላቅ ያለ ትጋትና የሥራ ተነሳሽነት ይጠበቃል። ድርብ ኃላፊነትን መወጣትና ትጉህ መሆን ደግሞ የራስ ፍላጎትን ከማሳካት ባለፈ አድናቆትና ስኬትን የሚቸር ፀጋን ከሌላኛው ወገን ያላብሳል።

የእለቱ የስኬት ገጽ እንግዳችን በመግቢያው ላይ ያነሳነውን ሃሳብ የሚያጠናክሩ የትጋት ተምሳሌት ናቸው። እኚህ እንግዳችን ከትጉህ አርሶ አደር ቤተሰብ የተገኙና የግብርና ሥራን ከልምድ ባሻገር በትምህርት አስደግፈው በከብት እርባታ ሥራ የተሠማሩ አርብቶ አደር ናቸው።

የግብርና ሥራ እጅግ አድካሚና አስቸጋሪ ቢሆንም ከዘርፉ የሚገኘው ውጤት ያማረና የመንፈስ እርካታን የሚሰጥ በመሆኑ ዘርፉን አጥብቀው ይወዱታል። እንግዳችን አቶ ከፍያለው ወርቁ ይባላሉ። ተወልደው ያደጉት በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ገለምሶ አካባቢ ነው። በግብርና ሥራ ከሚተዳደር ቤተሰብ የተገኙ በመሆናቸው ከግብርና ጋር በጥብቅ ቁርኝት አድገዋል።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን “ገለምሶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት” ተከታትለዋል። በአካባቢው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለመኖሩ አሰበ ተፈሪ ሄደው እንዲማሩ የግድ ቢላቸውም ከአስረኛ ክፍል በላይ ግን መቀጠል አልቻሉም። በወቅቱ ቤተሰቡ ችግር ገጥሞት እንደነበር ያስታወሱት አቶ ከፍያለው፤ ጎበዝ፣ጠንካራና ታታሪ ተማሪ እንደነበሩም አጫውተውናል። በገጠማቸው እክል ምክንያት አስኳላውን መቀጠል የሚያስችሏቸው ምቹ ሁኔታዎች ባይኖሯቸውም በልባቸው ግን እድሉ የሚፈጠርበትን መንገድ ያሰላስሉ ነበር።

ይህን ከፍተኛ ጉጉታቸውን በውስጣቸው ሸሽገው በወቅቱ ያገኙትን የሥራ ዕድል ተጠቅመዋል። ቡናና ሻይ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የሥራ ዕድል በረዳት የልማት ሠራተኝነት በትውልድ አካባቢያቸው ገለምሶ ተቀጥረው መሥራት ጀመሩ። በዚሁ ሥራ ላይ ለሁለት ዓመታት እንደቆዩ ደግሞ እንደ ትምህርታቸው ሁሉ በሥራቸውም ጎበዝ ነበሩና ታታሪ ሠራተኛ ተብለው “ሲፒ” ወደተባለው ፕሮጀክት ተዘዋወሩ። ደመወዛቸው ሰማንያ /80/ ብር፣ 127 ብር እያለ ወደ ሲፒ ፕሮጀክት ሲገቡ ደግሞ ከፍ ብሎ 167 ብር ደርሶ እንደነበር ያስታውሳሉ።

አቶ ከፍያለው የ167 ብር ደመወዝተኛ በሆኑ ጊዜ በአካባቢያቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከፍቷል። አጋጣሚው ትምህርት መማር ለሚሹ እንደ አቶ ከፍያለው አይነት ተማሪዎች መልካም አጋጣሚ በመሆኑ ያቋረጡትን ትምህርት ማስቀጠል ችለዋል። ትምህርቱ የሚሰጠው በግማሽ ቀን በመሆኑ ሥራቸውንም ሳይለቁ የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ለዲፕሎማ የሚሆን ነጥብ ማስመዝገብ ችለዋል።


የዲፕሎማ ትምህርታቸውንም በሀዋሳ ጁኒየር ኮሌጅ ለሁለት ዓመታት ተከታትለው በእጽዋት ሳይንስ በዲፕሎማ ተመርቀዋል። በወቅቱ መንግሥት ሥራ ይመድብ ነበርና ግብርና ሚኒስቴር ተወልደው ባደጉበት በሐረርጌ አውራጃ ቀጥሯቸው በተለያዩ አካባቢዎች በልማት ሠራተኝነት፣ በወረዳ ቡድን መሪነትና በሌሎች የሥራ ኃላፊነቶች ተመድበው ለ10 ተከታታይ ዓመታት አገልግለዋል።

አቶ ከፍያለው በግብርና ሚኒስቴር ማገልገላቸው በከብት እርባታ እንዲሠማሩ መሠረት የጣለላቸው መሆኑን ይናገራሉ። በግብርና ሚኒስቴር የነበራቸውን ቆይታ በገዛ ፈቃዳቸው አቋርጠው መንግሥታዊ ባልሆነው የሰዎች ለሰዎች ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ በተመሳሳይ የግብርና ሥራ ገጠር ውስጥ ሠርተዋል። ድርጅቱ ግብርና ላይ የሚሠራው ሥራ ሲዘጋ በተመሳሳይ ሐረር ከተማ ውስጥ በሥልጠና ላይ ይሠራ ነበርና ወደ ሥልጠና ተቋሙ ተዘዋውረው አገልግለዋል።

ሥልጠናውም ከግብርና ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለአርሶ አደሩና ለልማት ሠራተኞች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት በማስተማር ሥራ የቆዩት አቶ ከፍያለው ለትምህርት ጥልቅ ፍቅር ያላቸው በመሆኑ በትርፍ ጊዜያቸው በዓለማያ ዩኒቨርሲቲ እየሠሩ በመማር በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በአግሪካልቸራል ኤክስቴንሽን የመጀመሪያ ዲግሪ በሩራል ዴቨሎፕመንት እና አግሪካልቸራል ኤክስቴንሽን የማስተርስ ዲግሪያቸውን ማግኘት እንደቻሉ ነግረውናል።

እየሠሩ በተማሩበት መንግሥታዊ ባልሆነው በሰዎች ለሰዎች ድርጅት ውስጥ ለ28 ዓመታት ሲቆዩ እርሳቸውን ጨምሮ አራት ልጆቻቸውንም ማስተማር የግድ ያላቸው አቶ ከፍያለው፤ ለትምህርትና ለሌሎች በርካታ ፍላጎቶቻቸው ደመወዝ ብቻ በቂ ሆኖ አላገኙትም። በደመወዝ መተዳደር እንደከበዳቸው ሲረዱ ተጨማሪ ሥራ ጎን ለጎን ለመሥራት ሲያስቡ ከግብርና ሥራ ውጭ ማሰብ አልቻሉም።

እናም የወተት ከብት እርባታን አንድ ብለው ጀመሩ። በወቅቱ የሚሠሩ ሳይሆን የሚበሉ እጆች እና ብዙ ፍላጎቶች ያሏቸውን የልጆቻቸውን ፍላጎቶች ማሟላት ያልቻለው የወር ደመወዛቸው በወተት ከብት እርባታ እንዲደጎም አስበው በአንዲት ጊደር የወተት ከብት እርባታ ሥራን የጀመሩት አቶ ከፍያለው፤ አንድ ብለው የጀመሩትን ሁለት ሦስት እያሉ በማሳደግ ዛሬ 65 ከብቶች ማድረስ ችለዋል። በጉዟቸው ሁሉ ባለቤታቸው ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው የሚናገሩት አቶ ከፍያለው፣ አሁንም አብረው እየሠሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ።



አቶ ከፍያለው ወርቁ

**‹‹አንድን ጊደር መግቦና ተንከባክቦ ውጤት መስጠት እስክትጀምር ረጅም ጊዜ የሚወስድ አድካሚና ትዕግስትን የሚጠይቅ ሥራ ነው››**

‹‹ከአርሶ አደር ቤተሰብ የተገኘ ማንኛውም ሰው የእርሻ ሥራውንም ሆነ ከብት እርባታውን በሚገባ ያውቀዋል›› የሚሉት አቶ ከፍያለው፤ ሰዎች ከሥር መሠረቱ የሚያውቁትን ቢሠሩ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉም ይናገራሉ። የግብርና ሥራ ከፍተኛ ውጣ ውረዶች ያሉት ቢሆንም፣ ከብዙ ድካምና ትዕግስት በኋላ የሚገኘው ፍሬ እጅግ ጣፋጭና እርካታን የሚሰጥ መሆኑን ይገልጻሉ። ስለዚህ ዘርፉን የሚያውቅ ሰው በትዕግስት ጠንክሮ ውጤታማ መሆን ይችላል የሚል እምነት አላቸው።

አቶ ከፍለው፤ ከልጅነት እስከ ዕውቀት በሚያውቁት የግብርና ሥራ ተቀጥረው ከመሥራት በተጨማሪ የገቢ ምንጫቸውን ለማሳደግ የጀመሩት የወተት ከብት እርባታ አንድ ሁለት እያለ መስፋት ችሏል። ያኔ የርሳቸው ዕድሜ ለጡረታ ቀረበና የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ ተቀጥረው ከሚሠሩበት የሰዎች ለሰዎች ድርጅት በጡረታ ተሰናብተው ወጥተዋል። በጡረታ ከተሰናበቱ ወዲህም የሙሉ ጊዜ ሥራቸውን በወተት ከብት እርባታ ሥራ ላይ ማድረግ የቻሉት አቶ ከፍያለው፤ በአሁኑ ወቅት ቆፍጣና ገበሬ መሆን ችለዋል። በአንድ ጊደር የተጀመረው የወተት ከብቶች ልማት ዛሬ በረቱ በከብቶች ተሞልቷል።

በሐረር ከተማ በከብት እርባታ የተሰማሩት ቆፍጣናው አርሶ አደር በከብት እርባታው የመጀመሪያ ጥቅማቸው ወተት አምርተው በመሸጥ የሚያገኙት ገቢ አንዱ ሲሆን ከወተት በተጨማሪም ከብቶቹ ራሳቸው ሃብት እንደሆኑ ይናገራሉ። ወይፈኖችን ለተወሰነ ጊዜ አሳድገው ይሸጣሉ፤ የወተት ላሞቹም ቢሆኑ የወተት ምርታቸው እየቀነሰ ሲሄድ ለገበያ ይቀርባሉ፤ እነዚህም ሌሎች የገቢ ምንጮቻቸው እንደሆኑ አቶ ከፍያለው ይናገራሉ።

ይሁንና ባሏቸው የከብቶች ቁጥር ልክ የወተት ምርት ማግኘት እየቻሉ እንዳልሆነ የሚናገሩት አቶ ከፍያለው፤ ለዚህም አንዱ ምክንያት እንደ ሀገር ያለው የመኖ እጥረት መሆኑን ይጠቁማሉ። በዚህ የተነሳም የወተት ምርት በስፋት ማቅረብ አልቻሉም። ያም ቢሆን ያለውን ችግር ተቋቁመው በቀን ከ100 እስከ 150 ሊትር ወተት ማግኘት እንደሚችሉ ጠቅሰው፣ ወተቱንም ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። የአንድ ሊትር ወተት ዋጋም በአማካኝ ከ50 እስከ 60 ብር ሲሆን ይህንን ዋጋ በቀን በ150 ሊትር ብዜት ገቢ ማስገኘት ችሏል። ገቢው በግርድፉ የሚገኝ ቢሆንም ለከብቶቹ ከሚቀርበው መኖ ጀምሮ በርካታ ወጪዎችንና ድካም የሚጠይቅ ዘርፍ እንደሆነ አቶ ከፍያለው ይናገራሉ።

በመንግሥት ሥራ የወር ደመወዝ ጠብቆ ከመኖር ይልቅ ሰዎች በተለይም የሚያውቁትን ሥራ በግላቸው ለመሥራት ጥረት ቢያደርጉ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻሉ የሚያስገነዝቡት አቶ ከፍያለው፤ እሳቸው አንድ ብለው የጀመሩት የወተት ከብት እርባታ የከብቶቹ ቁጥር 65 መድረስ የቻለ ቢሆንም፣ ከዚህ በበለጠ ቁጥራቸውን ለማበራከት ቦታ የገደባቸው መሆኑንም አልሸሸጉም። በአሁኑ ወቅትም የቦታ ጥያቄያቸውን ለመንግሥት አቅርበው ምላሹን እየተጠባበቁ እንደሆነ በመግለጽ በቀጣይ የቦታ ጥያቄያቸው ሲፈታ ሰፊ ቁጥር ያላቸውን የወተት ከብቶች በማርባት በሐረር ከተማ ያለውን የወተት እጥረት ለመፍታት የሚሠሩ መሆኑን ይናገራሉ።

የከብቶቹን ቁጥር ከፍ በማድረግ በሐረር ከተማ ያለውን የወተት ፍላጎት ለማሟላት እሠራለሁ የሚሉት አቶ ከፍያለው፤ በከተማዋ ሁሌም የወተት እጥረት መኖሩን ይገልጻሉ። የፍላጎቱን ያህል በቂ ወተት ማምረት ሲችሉ በቀጣይ ደግሞ እሴት በመጨመር ወተት ወደማቀነባበር የመግባት ሀሳብ እንዳላቸውም ተናግረዋል።

በሥራ ዓለም ጀምረው እንዲሁም ከጡረታ በኋላ ሙሉ ለሙሉ የወተት ከብት እርባታ ሥራን የተቀላቀሉት አቶ ከፍያለው፤ ከብቶቹን የሚያረቡት በሐረር ከተማ ኖክ ዲፖ በሚባል ነዳጅ ማደያ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው አቅራቢ ነው፤ የወተት ምርቱንም በብዛት ተደራሽ የሚያደርጉት በአካባቢው በሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለሚገኙ ሕጻናት ነው። ወደ ካፍቴሪያና ሻይ ቤቶች የሚሄደውም በጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ሕጻናት ሲተርፍ እንደሆነ ነው አቶ ከፍያለው ያስረዱት።

የሥራ ዕድልን በተመለከተ በቋሚነት ለአራት ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻሉ ሲሆን ለከብቶቹ መኖ በሚሰበሰብበት ጊዜ ከ20 እስከ 25 ሰዎች በመኖ ማሰባሰብ ሥራ ላይ በጊዜያዊነት የሚሠማሩ ይሆናል። መኖ የሚሰበሰበውም ጥቅምት፣ ኅዳር፣ ታኅሣሥ፣ ጥርና የካቲት ድረስ በመሆኑ በዓመት ውስጥ ከአራት እስከ አምስት ወራት ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ይፈጠራል። ከዚህ በተጨማሪም በራሪ በሆኑ ሥራዎች ጥቂት ለማይባሉ ዜጎች ወቅታዊ የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

‹‹አንድን ጊደር መግቦና ተንከባክቦ ውጤት መስጠት እስክትጀምር ረጅም ጊዜ የሚወስድ አድካሚና ትዕግስትን የሚጠይቅ ሥራ ነው›› የሚሉት አቶ ከፍያለው፤ ሥራው አድካሚና ትዕግስት የሚፈልግ ከመሆኑ ባሻገር ከእንስሳት ጋር መኖር እጅግ አስደሳች እንደሆነ ነው የሚናገሩት። ከእንስሳቱ የሚገኘው ውጤት በከፍተኛ ልፋትና ድካም እንዲሁም በትዕግስት የሚገኝ በመሆኑ ከዘርፉ የሚያገኙት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እጅግ እንደሚያስደስታቸውም ይገልጻሉ።


በከፍተኛ ትጋት ወተት አቅርቦ ሕጻናት ወተት እንዲያገኙ ማድረግ በራሱ ትልቅ ደስታ የሚሰጥ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ከፍያለው፤ በአካባቢያቸው የሚገኙ ከ100 የሚበልጡ ሕጻናት ወተት እንዲያገኙ ምክንያት መሆን መቻላቸው አንዱ ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት መሆኑን ይገልፃሉ። ለአካባቢያቸው አቅመ ደካሞችም ድጋፍ ያደርጋሉ። መንግሥት ለሚያደርገው ማንኛውም የድጋፍ ጥሪም አቅማቸው በፈቀደ ተሳትፎ እንደሚደርጉ ነው የሚገልጹት።

ወተት በተለይም ለሕጻናት እድገትና ለአረጋውያን መጦሪያ እጅግ ወሳኝ ምግብ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ከፍያለው፤ ይህንን ጠቃሚ ምግብ ግን ኢትዮጵያውያን በተፈለገው መጠን እያገኘን እንዳልሆነ ጥናቶች ማመላከታቸውን ይናገራሉ። ይህም በዘርፉ መሠራት የሚገባቸው የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው አመላካች መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሃብት ከአፍሪካ ቀዳሚ እንደሆነች በስፋት የሚነገር ቢሆንም ከዘርፉ መጠቀም አልተቻለም። ለዚህም መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት ያመላክታል ይላሉ። ከመንግሥት በተጨማሪም በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች ጭምር ሰፊ ርብርብ በማድረግ ለሕጻናትና ለአረጋውያን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ወተት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሁም በስፋት ማቅረብ የግድና ወሳኝ እንደሆነም አስገንዝበዋል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቷ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ በተለይም በግብርና ዘርፍ የሰለጠኑ ብዙ ወጣቶች እየመጡ እንደሆነም አቶ ከፍያለሁ ይገልጻሉ፤ እነዚህ ወጣቶች መንግሥት ሥራ እስኪሰጣቸው መጠበቅ እንደሌለባቸው በመግለጽ በግብርናው ዘርፍ በተለይም በእንስሳት እርባታ፣ በንብ ማነብ፣ በዶሮ እርባታ እንዲሁም በዕፅዋት ዘርፍ አትክልትና ፍራፍሬ ወዘተ ልማት ተሰማርተው ቢሰሩ ባለሙያዎች እንደመሆናቸው ትርጉም ያለው ለውጥ በማምጣት ራሳቸውንም አገርን መቀየር ይችላሉ የሚል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ስፖርት





## ለአፍሪካ ታዳጊና ወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን በተያዘው ዓመት ከሚያካሂዳቸው ውድድሮች መካከል አንዱ አህጉር አቀፉ ከ18 እና 20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ቻምፒዮና ነው።ኮንፌዴሬሽኑ ከዚህ ቀደም በየፊናቸው ይካሄዱ የነበሩትን እነዚህን ውድድሮች በማጣመር ማካሄድ ከጀመረ ይህ ሁለተኛ ጊዜው ሲሆን፤ ከሁለት ሳምንት በኋላም ይጀመራል።የመም እና በሜዳ ተግባራት ፉክክሮችን የሚያካትተው ይህ ውድድር በርካታ ወጣት አትሌቶችን ወደ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የማሸጋገር ከፍተኛ ሚና አለው።

ከትምህርት ቤቶችና የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ተቋማት የሰለጠኑ አትሌቶች አቅማቸውን ለመፈተሽ እንዲሁም የውድድር ልምድ እንዲያገኙ ከአገር ውስጥ ውድድሮች ባለፈ መሰል በዕድሜ ገደብ የሚደረጉ ውድድሮች ላይ ተካፋይ እንዲሆኑ ተደርጓል። አሁን ላይ ለእውቅና የበቁ አትሌቶችም መነሻቸውን ያደረጉት በእነዚህ ቻምፒዮናዎች ላይ ነው።ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮናው ዘንድሮ ለ15ኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከ18 ዓመት በታች ቻምፒዮናው ደግሞ ለ4ኛ ጊዜ ይከናወናል።ተተኪና ወጣት አትሌቶችን ማፍራትን ዓላማው ያደረገው ይህ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ የተከናወነው ኮትዲቯር አቢጃን ላይ ከአራት ዓመት በፊት ነበር።

የሁለተኛውን ቻምፒዮና አዘጋጅነት ተራ ዛምቢያ ሲሰጣት አስቀድሞ ውድድሩን ለማድረግ የተመረጠችው ከተማ ሉሳካ ብትሆንም፤ የቦታ ለውጥ በማድረግ ከሉሳካ 350 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው ናዶላ ከተማ የቀየረ መሆኑን አዘጋጆቹ አስታውቀዋል።አገሪቷ ዝግጅቷን ያጠናቀቀች ሲሆን፤ በውድድሩ ላይ 50 አገራት አትሌቶቻቸውን ከ18 ዓመት በታች በ40 እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች በ44 የውድድር ዓይነቶች የሚያካፍሉም ይሆናል።ከሁለት ሳምንት በኋላ ለሚካሄደው ለዚህ ውድድርም ኢትዮጵያን ጨምሮ የኮንፌዴሬሽኑ አባል አገራት ወጣት አትሌቶቻቸውን በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ።



ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ባለፉት ሁለት ሳምንታት ዝግጅት እያደረጉ ይገኛሉ፣

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንዳስታወቀው፣ በቻምፒዮናው ኢትዮጵያን የሚወክለው የታዳጊና ወጣት ቡድን ከሳምንት አስቀድሞ ሆቴል በመግባት ልምምድ እና ዝግጅት ተጀምሯል። ከ30 የማያንሱ አትሌቶች በሁለቱም ጾታ እና የዕድሜ እርከኖች የተመረጡ ሲሆን፤ ከ800 ሜትር ጀምሮ እስከ 10 ሺህ ሜትር ድረስ ባሉ የውድድር ርቀቶች ተካፋይ ይሆናሉ።ቡድኑ ከአትሌቶች ባሻገር ከ9 አሰልጣኞችን እንዲሁም 4 የሚሆኑ የህክምና ቡድን አባላትን ያካተተ መሆኑም ታውቋል፡፡

ቡድኑ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ልምምዱን አጠናክሮ የቀጠለ ይሁን እንጂ፤ በአዲስ አበባም ሆነ ሌሎች የአገሪቷ ክፍሎች ከፍተኛ የመም እጥረት መኖሩ ዝግጅቱን አዳጋች አድርጎታል።በተለያዩ ቻምፒዮናዎች በሩጫ ውድድሮች ብቻ የሚካፈለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በመም ውድድሮች ውጤታማ መሆኑ ይታወቃል።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የመም አለመኖር ለመሰል ልምምዶችም ሆነ ውድድሮች እጅግ ፈታኝ እየሆነ ይገኛል። ይህም ውጤት ላይም የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሰ መሆኑ ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም ለዚህ ችግር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ችግሮችን በመፍታት ለሁለተኛ ጊዜ በሚካሄደው የአፍሪካው የ18 እና 20 አመት በታች የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ተከታታይ የሆነ ጠንካራና ከፍተኛ ዝግጅቱን እያደረገ እንደሚገኝ በድረገጹ አስነብቧል።

በአፍሪካ የሚካሄዱ የዕድሜ ገደብ ያላቸው ውድድሮች ላይ በቀዳሚነት የሚነሳው ችግር የዕድሜ ማጭበርበር መሆኑ ይታወቃል።ኮንፌዴሬሽኑም አገራት ከ18 ዓመት በታች ውድድር ላይ እአአ በ2006 እና 2007 ወዲህ የተወለዱ እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች እአአ ከ2004 እና 2005 ወዲህ የተወለዱ አትሌቶችን ብቻ እንደሚያሳትፍ አስታውቋል።


## SECOND TIME INVITATION FOR NATIONAL BID

1. Oromia Construction Authority invites interested bidders for Supply Different types of Electronics and data center civil work /hardware and software/ under National Competitive Bidding -NCB).

| S. No | Item Description | Bid Reference Number | Bid to be submitted before | Bid Close time | Bid Open time | Bid type |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Supply electronics | 004/2015 | 15 working days from the date of announcement | 4:00 AM | 4:30 AM | NATIONAL |

2. A complete set of Bidding Document can be obtained from Procurement team office which is found in the New building of Oromia Bureaus 4th floor room No. 409 with non-refundable fee of Ethiopian Birr 200.00 (two hundred birr only) for each Bid Reference Number at procurement, Finance and resource management Directorate found in OCA, sub-basement floor during office hours (Monday to Friday 8:30-12:30 A.M and 01:30- 05:30 P.M).
3. All Bids must be accompanied by bid security 0.5 % and the winner must engage performance bond 10% of the Total Bid Price in the form of CPO or Bank Guarantee.
4. Bidders shall present copy of their renewed trade license for the 2015 E.C, main registration trade license, Tax Identification Number (TIN), Tax clearance certificate, VAT registration certificate, and Supply list registration certificate.
5. Bids shall be submitted in the tender Box prepared for this purpose on /before the above indicated table date and the closing is on the same date, time shows in the above table. The bid number should be indicated in the bid document.
6. Bid opening shall be held on the days and time indicated in the above table in the presence of bidders and/or their representatives who wish to attend.
7. Failure to comply any of the conditions from (3) to (5) above shall result in automatic rejection.
8. The winner shall configure and install the electronic materials as per the client's requirement at OCA head office located in Addis Ababa city Nefas silk lafto sub city woreda 04 Sarbet in the compound of Oromia regional state sectorial office by their own transport.
9. OCA reserves the right to accept or reject any or all bids at any time.
10. The bidder must submit financial proposal, technical proposal and bid security in separate envelop signed wax sealed.
11. The bidders must fill financial proposal on given bill of quantity sheet.
12. Bidders may get further information at the following address:

Oromia Construction Authority, Property Financial and procurement management Directorate, 4th floor, office No.409 Sarbet. In the compound of Oromia Regional State Sectorial Office, Addis Ababa, Ethiopia

Telephone No. +251-11-8-22-06-49

E-mail Address: Gareict2022@gmail.com

**Oromia Construction Authority**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 125/130 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0003437987 አብዲሳ ለሜሳ በዳሳ ከተመዘገበኩበት ቂርቆስ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ከቁጥር 001 እስከ 040 የተሰራበት፣ ከቁጥር 041 እስከ 050 ያልተሰራበት እና ከቁጥር 051 እስከ 150 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ቂርቆስ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም አብዲሳ**
**ለሜሳ በዳሳ**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 047 ሲኒማ ራስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0004359852 አሚና ሽኩሪላ ሀሰን በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር መርካቶ ቁጥር 1 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 401 እስከ 450 የተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት መርካቶ ቁጥር 1 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም አሚና**
**ሽኩሪላ ሀሰን**